## ‹‹የዓባይ ግድብ ቀድሞ የነበረውን የኢትዮጵያውያንን አንድነት የመለሰ ነው››

- ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ

በአ.አ.ዩ. ዩኒቨርሲቲ መምህርና የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪ



ገጽ 7

## ዓመታዊ ምርመራና ጠቀሜታው

ገጽ 18


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

81ኛ ዓመት ቁጥር 365 ጳጉሜን 5 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!










# አዲስ ዓመት በተበሰረ ቁጥር የኢትዮጵያም ተስፋ ይበሰራል

- ዐቢይ አህመድ(ዶ/ር)

የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር



በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- አዲስ ዓመት በተበሰረ ቁጥር የኢትዮጵያም ተስፋ እየተበሰረ እንደሆነ እያሰብን መሥራት አለብን ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ገለጹ፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ዐቢይ አሕመድ "መከታ" በተሰኘው የመከላከያ ሠራዊት መጽሔት ላይ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት የመከላከያ ሠራዊት አባላት የመጪዋ ኃያል ሀገር የመከላከያ ሠራዊት አባላት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ተስፋ ጠባቂ መሆናቸውን አውቀው ሊሰሩ ይገባል፡፡

አዲስ ዓመት በተበሰረ ቁጥር የኢትዮጵያም ተስፋ እየተበሰረ እንደሆነ እያሰብን መሥራት አለብን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የኢትዮጵያ ተስፋ እውን የሚሆነውና ሕልውናዋ በዘላቂነት ሊረጋገጥ የሚችለው መከላከያ "በማንኛውም ጊዜ ለጦርነት ሲዘጋጅ" ብቻ ነው፤ ይህ ሲባል ግን ሠራዊቱ ጠብ አጫሪ ይሆናል ማለት አይደለም ብለዋል።

ጠብ አጫሪነት በታሪካችን የለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ "ደፍሮ የመጣን ኃይል አሳፍረን እንመልሳለን እንጂ በማን-አለብኝነት በሌላ ሉዓላዊ ግዛት ላይ የኃይል ጥቃት የመሰንዘር ታሪክ አናውቅም" ሲሉም አውስተዋል።

ጠላቶቻችን አርፈው የሚቀመጡት በሁሉም ዘርፍ ብቃት ላይ መገኘታችንን ሲረዱ፣ በስትራቴጂ፣ በቁሳቁስና በቴክኖሎጂ አቅም በልጠው ሊያሸንፉን እንደማይችሉ ሲያውቁ ብቻ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ በጦር ሜዳ ብዙ ጀብዱዎችን የፈጸሙ፣ ጦር ሰብቆና ድንበር ጥሶ የመጣ ጠላትን አንገት አስደፍተው የመለሱ፣ ለሀገር ሉዓላዊነትና ለዜጎች ነፃነት መስዋዕትን እንደ ክብር የሚቆጥሩ ጀግኖችን አፍርታለች።

ከጥንታውያኑ የግሪክ አፈታሪኮች እስከ ዓድዋው ዘመን የአውሮፓ ጋዜጦች የኢትዮጵያውያን ጀግንነት መወደሱን ያወሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ "የዛሬ

አዲስ ዓመት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል











ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሴ

## በመጪው ዓመት በበጋ መስኖ 40 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማምረት ታቅዷል

ገጽ 6

## " የትግራይ ወጣት ለአሸባሪው ሕወሓት ቀቢጸ ተስፋ ጦርነት ህይወቱን እንዳይገብር እምቢተኝነቱን ማሳየት አለበት"

አረጋዊ በርሄ (ዶ/ር)

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር



ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- የትግራይ ህዝብ በተለይ ወጣቱ የሕወሓት ቀቢጸ ተስፋ ጦርነት ህይወቱን እንዳይገብር በግልጽ እምቢተኝነቱን ማሳየት አለበት ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አረጋዊ በርሄ (ዶ/ር) ጥሪ አቀረቡ፡፡

ዶ/ር አረጋዊ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ የሕወሓት የአሁኑ ጦርነት ትርጉም

" የትግራይ ወጣት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









ገጽ 6

## የጥላቻ ትርክቶች አንድነትን በሚያጠነክሩ አዳዲስ ትርክቶች ሊተኩ ይገባል



ዜና

# ሁሉም የግል ድርጅት ሠራተኞች ከአዲሱ ዓመት ጀምሮ በጡረታ ዕቅድ ውስጥ ይገባሉ

**ዳንኤል ዘነበ**



አዲስ አበባ፡- ሁሉም የግል ድርጅት ሠራተኞች ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ ዕቅድ ውስጥ እንደሚገቡ የኢ.ፌ. ዲ.ሪ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር አስታወቀ። 2019 የግል ድርጅቶች እና 71 ሺህ የግል ድርጅት ሠራተኞች ይመዘገባሉ ተብሎም ይጠበቃል።

የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ገመቹ ወዩማ ለመገናኛ ብዙሀን ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ የግል ድርጅት ሠራተኞች ከፕሮቪደንት ፈንድ ወደ ማኅበራዊ ዋስትና ጡረታ አቅዱ የሚሸፈኑበት መመሪያ ፀድቋል። በመሆኑም በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዕቅድ ያልተሸፈኑ ሁሉም የግል ድርጅት ሠራተኞች ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ ዕቅድ ውስጥ ይገባሉ ።

ከሐምሌ 2003ዓ.ም በፊት በተቋቋመ የግል ድርጅቶች በነበራቸው ፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ በሚጠራ የማህበራዊ ዋስትና ዕቅድ ተጠቃሚነታቸውን ለመቀጠል ወስነው የቀጠሉና በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዕቅድ ያልተሸፈኑ የግል ድርጅት ሠራተኞችን ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ ዕቅድ እንደሚሸፈኑ ገልጸው፤ በአዋጅ ቁጥር 1268/2014 መሠረት ይህ መመሪያ ፀንቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ የተጠራቀመ የፕሮቪደንት ፈንድ ገንዘብ ለግል ድርጅት ሠራኞች ጡረታ ፈንድ ገቢ በማድረግ አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን እንዲታሰብለት ማድረግ ይችላል ብለዋል ።

ነገር ግን በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዕቅድ ለሚሸፈን የግል ድርጅት ሠራተኛ ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም አስቀድሞ የፈፀመው አገልግሎት ለጡረታ አበል አወሳሰን ሊታሰብ የሚችለው ያጠራቀመውን ገንዘብ እስከ የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ብቻ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ያደረገ እንደሆነ ብቻ መሆኑን አመልክተዋል።

የአስተዳደሩ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ደረጄ ውቤ በበኩላቸው ፤ ፕሮቪደንት ፈንድ ከበርካታ የማህበራዊ ዋስትና ማረጋገጫ መንገዶች አንዱ ነው ። ነገር ግን በዘላቂነት ለሰራተኛው ዋስትና የሚሰጥ አይደለም። ሁሉም በግሉ ዘርፍ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች በጡረታ ዕቅድ ውስጥ መካተታቸው ለጡረታ ሲደርሱ ተገቢውን እና ዘላቂ ማህበራዊ ዋስትና እንዲያገኙ የሚያስችል ይሆናል ብለዋል ።

በግሉ ዘርፍ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ዘላቂ የማህበራዊ ዋስትናን ያረጋግጣል ተብሎ የሚጠበቀው መመሪያም ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚደረግ ጠቅሰው ፤ በዚህም ሁለት ሺህ 19 የግል ድርጅቶች እና 71 ሺህ የግል ድርጅት ሠራተኞች ይመዘገባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል ።

ፕሮቪደንት ፈንድ ማለት ከሠራተኛውና ከአሠሪው በየወሩ የተወሰነ መቶኛ እየተዋጣ በሠራተኛው ስም የሚቀመጥና ሠራተኛው በጡረታ ጊዜ ወይንም በሥራ በማናቸውም ምክንያት ሲለቅ ተጠራቅሞ በአንድ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ነው።



ጋዜጠኛ አዩብ አደም



ጋዜጠኛ ሃና ዳባ



ጋዜጠኛ ውብሸት አበራ

# ሚዲያዎቹ ሰላምና ግብረ ገብነት ላይ በትኩረት ይሰራሉ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ዕውቅና ያገኙና በዕውቅና ሂደት ላይ ያሉ የተለያዩ ሃይማኖቶች ሚዲያዎች የትውልድ ሰላምና ግብረ ገብነት ቀረፃና ግንባታ ላይ አተኩረው እንደሚሠሩ አስታወቁ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቴሌቪዥን፣ የሜምበር ቴሌቪዥን እና የማርሴል ቴሌቪዥን የሃይማኖት ሚዲያዎች ኃላፊዎችና ጋዜጠኞች የትውልድ ሰላምና ግብረ ገብነት ቀረፃና ግንባታ ላይ አተኩረው እንደሚሠሩ አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቴሌቪዥን የፕሮግራም አስተባባሪ ጋዜጠኛ ውብሸት አበራ፣ ቴሌቪዥኑ በተለይ በሰላምና በግብረገብነት ግንባታና ቀረፃ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ ተናግሯል።

የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቴሌቪዥን ሃይማኖታዊና ማሕበራዊ አስተምህሮ በጥምረት የሚሰጡ ፕሮግራሞች አሉት ያለው ጋዜጠኛ ውብሸት፣ ከማሕበራዊ አስተምህሮ ደግሞ አንዱና ትልቁ ዕሴት የሰላም ግንባታ ነው። የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በሰላም ግንባታ እና ግብረገብነት ዙሪያ በትኩረት ታስተምራለች፤ ቴሌቪዥኑም በተመሳሳይ በሰላምና የወጣቶች ሥነ ምግባር ግናባታ ላይ እንዲሁም በግብረ ገብነት ቀረፃ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል ሲል አብራርቷል።

እንደ ጋዜጠኛ ውብሸት ገለፃ፣ ሀገሪቱን ካለችበት ሁኔታ ወደ ሰላም መመለስ የሚቻለው የሃይማኖት ተቋማትና የሃይማኖት ሚዲያዎች በርብርብ በሚሠሩት ሥራ ነው። ምዕመኑ ከመፀለዩ ባሻገር በሰላም ላይ የራሱን ሚና እንዲጫወት ማድረግ የሚቻለው በሃይማኖት ሚዲያዎች በሚከናወኑ መርሐ ግብሮች ነው። ለዚህ ሲባልም የተለያዩ ፕሮግራሞችን በኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተቀርፀው በቴሌቪዥን እየተላለፉ ይገኛል።

ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋርም ውይይት የማድረግ መርሐ ግብር መጀመሩን የገለፀው ጋዜጠኛ ውብሸት፤ ይህ ለሰላም ትልቅ አስተዋፅዖ የሚኖረው ነው ሲል አክሏል።

የሜምበር ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ አዩብ አደምም በተመሳሳይ ጣቢያው ሰላምና ግብረ ገብነት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ ተናግሯል።

የሃይማኖት ሚዲያዎች ዋነኛው ተልዕኳቸው ሰላምን ለሰው ልጆች ማላበስ ነው የሚለው ጋዜጠኛ አዩብ፣ መንግሥት ለሃይማኖት ሚዲያዎች አወንታዊ አመለካከት ይዞ እየሠራ በመሆኑ የሃይማኖት ሚዲያዎች የተሻለ ነገር እንዲያበረክቱ የሚያደርግ አካሄድ መፈጠሩን ገልጿል።

አገር ሰላም ሲሆን ነው ሚዲያው የሚኖረውም ሆነ ወጥተን ልንገባ የምንችለው፤ ስለዚህም በትውልድ ምግባር ቀረፃ እና በሰላም ላይ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው የምንገኘው ሲልም አክሏል።

እንደ ጋዜጠኛ አዩብ ገለፃ፤ የሁሉም ሃይማኖቶች ስብከት ሰላም እስከሆነ ድረስ የሃይማኖት ሚዲያዎችም ከዚህ የዘለለ ዓላማ ሊኖራቸው አይገባም። ትኩረት መደረግ ያለበትም ግለሰባዊ ግብረ ገብነትን በመቅረፅ ግለሰባዊና ሃገራዊ ሰላምን መገንባት ላይ ነው። ይህንን ታሳቢ በማድረግ ሜምበር ቴሌቪዥን ትንሽ ጠብታም ቢሆን ለሰላም የሚደረግ አስተዋፅዖ ውጤቱ ብዙ እንደሆነ አምኖ እየሠራ ነው።

ሜምበር ቴሌቪዥን ሰላምና አብሮነትን እንደ መርህ ይዞ የሚሠራ የሃይማኖት ሚዲያ ነው ያለው ጋዜጠኛ አዩብ፣ በሙስሊሙ መካከል ሰላምና መግባባት እንዲኖር እንዲሁም ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋርም በተመሳሳይ ሰላም እንዲኖር እየሠራን ነው ይምንገኘው ብሏል።

ሃና ዳባ የማርሴል ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ናት። የጣቢያውን የሰላምና ግብረ ገብነት ሥራ አስመልክቶ ተመሳሳይ ሥራዎች እንደሚሠሩ ተናግራለች።

የሃይማኖት ተቋማት በሰላም ጉዳይ ላይ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ መሆኑን ያወሳቸው ጋዜጠኛዋ፤ የሃይማኖት ሚዲያዎችም በተመሳሳይ የሰላም ጉዳይ ጉዳያቸው አድርገው መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብላለች።

እንደ ጋዜጠኛ ሃና ገለፃ፤ በሀገሪቱ ብዙ አማኝ ባለበት ሁኔታ ችግሮች እየታዩ መጥተዋል። እንዲህ ዓይነት ችግሮችን ለመፍታት የሃይማኖት ተቋማትም ሆነ የሃይማኖት ሚዲያዎችን ርብርብ የሚጠይቅ ነው።

የሃይማኖት ሚዲያዎች ስለመቻቻል፣ ስለፍቅር ስለህብረትና ሌሎችም ቀና መንገዶችን ለተከታዮቻቸው በማስተማር ሀገሪቱን ወደ ቀደመ ሰላሟ ማምጣት ይቻላል ያለችው ሃና፣ ማርሴል ቴሌቪዥን እንደ መልካም ወጣት ዓይነት ፕሮጀክቶች ተቀርፀው በወጣቶች ምግባር ቀረፃ ላይ ከፍተኛ ሥራ እየሠራ ነው ብላለች።

በፕሮግራሙ ወጣቶች በሁለንተናዊ ሁኔታ ጥሩ ስብዕና ይዘው እንዲቀረፁ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሳ፤ በማኅበረሰባዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበለፀጉና መልካም የሆኑ ወጣቶች መፍጠርን ራዕይ አድርጎ እየሠራ መሆኑን ገልፃለች።

ወጣቶች በሥነምግባር የታነፁና ሌሎች ላይ ጥገኛ ያልሆኑ ሆነው እንዲቀረፁ ያስፈልጋል ያለችው ጋዜጠኛ ሃና፣ ለሀገራቸው እና ለሚከተሉት እምነት ሰላም ከፍተኛውን ሚና እንዲወጡ ለማድረግ በቴሌቪዥኑ ፕሮግራሞች እንሠራለን ብላለች። ከዚህ በፊት በተሠሩ መሰል ሥራዎችም ተስፋ ሰጪ ምልክቶች መታየታቸውን አክላ ገልፃለች።

# 80 ማህበራት ምርቶቻቸውን ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች እያቀረቡ ናቸው

**መሳኩ ኤርሴ**

አዲስ አበባ ፡- 80 የሚሆኑ ማህበራት ካለፈው ዓርብ አንስቶ የግብርና እና ኢንዱስትሪ ምርቶቻቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በተለያዩ አካባቢዎች ማቅረብ መጀመራቸውን የኦሮሚያ ህብረት ሥራ ኤጀንሲ አስታወቀ።

የኤጀንሲው የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ፊሮምሳ አበራ ለኢፕድ እንዳሉት፤ ህብረት ሥራ ማህበሩ የ2015 አዲስ ዓመት በዓልን ምክንያት በማድረግ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማቅረብ ሰፊ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል።

በኤጀንሲው ለከተማው ገበያ እየቀረቡ ያሉት ምርቶች የግብርናና የኢንዱስትሪ መሆናቸውን አቶ ፊሮምሳ ጠቅሰው፣ ከግብርና ምርቶች መካከል ጤፍ እና የቁም እንስሳት እንደሚገኙበት አስታውቀዋል። የግብርና ምርቶችም ሆነ የኢንዱስትሪ ምርቶቹ በገበያ ከሚቀርብበት ዋጋ አንጻር ሲታይ ሰፊ ልዩነት መኖሩንም ነው የጠቀሱት።

በአዲስ አበባ በሚገኙ በመደበኛ ገበያዎች የአንድ በሬ መሸጫ ዋጋ ከ80ሺህ እስከ 120 ሺህ ብር መድረሱን ጠቁመው፤ ኤጀንሲው ግን ከ45 ሺህ ብር ጀምሮ በሬዎችን እያቀረበ መሆኑን አመልክተዋል። አቶ ፊሮምሳ በገበያ ከሚቀርብበት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በአንድ በሬ ላይ እስከ 20ሺ ብር ልዩነት እንደሚታይም ተናግረዋል።

የጤፍ ዋጋ በገበያ ከስድስት ሺህ ብር በላይ መድረሱን አስታውቀው፤ ህብረት ሥራ ኤጀንሲው ግን ጥራት ያለው ጤፍ በአምስት ሺህ ብር እያቀረበ ይገኛል ብለዋል። ከግብርና ምርቶች በተጨማሪ የተለያዩ የኢንዱስትሪ ምርቶችም እየቀረቡ መሆናቸውን ጠቁመው፣ ከነዚህ ምርቶች መካከል ዱቄት እና መሰል የኢንዱስትሪ ምርቶች እንደሚገኙበት ተናግረዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ህብረት ሥራ ኤጀንሲው ከበዓል ጋር ተያይዞ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በተጋነነ የዋጋ ጭማሪ ምክንያት እንዳይጎዱ ምርቶቹን ለገበያ እያቀረበ ነው። ምርቶቹ በአዲስ አበባ ውስጥ በኦሮሞ ባህል ማዕከል፣ ቦሌ፣ ጀሞ እና ሳርቤት ፑሽኪን አደባባይ አካባቢዎች ቀርበዋል።

ኤጀንሲው አምና ሙሉ ዓመት እሁድ እና ቅዳሜ ለከተማው ነዋሪዎች ምርቶችን ሲያቀርብ እንደነበር አስታውሰው፣ ለበዓላትም እንዲሁ ሲያቀርብ እንደነበር ጠቅሰዋል። ዘንድሮ አምና ይቀርብ ከነበረው በተጨማሪ በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ እና እንቁላል ጭምር ማቅረቡ ልዩ እንደሚያደርገው ይጠቁማሉ።

የበዓል ገበያው እስከ በዓል ዋዜማ ይቆያል ያሉት አቶ ፊሮምሳ፣ አዲስ ዓመት ካለፈ በኋላ ለመስቀል በዓል በተመሳሳይ የግብርና እና ኢንዱስትሪ ምርቶችን ለከተማው ነዋሪዎች ለማቅረብ እቅድ መያዙንም ይጠቁማሉ። በቀጣይ ለመስቀል በዓል ከአራት ቦታዎች በተጨማሪ በሌሎች የከተማዋ አካባቢዎችም ለማቅረብ መታቀዱን ገልጸዋል።

# የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት የአሰራር ማሻሻያዎች እየዘረጉ ነው

## - የአገልጋይነት ቀን በተለያዩ ሁነቶች ተከብሯል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በአገልግሎት አሰጣጥ ዙርያ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የአሰራር ማሻሻያዎችን እየዘረጋ መሆኑን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስታወቀ። ኮሚሽኑ የአገልጋይነት ቀንን በተለያዩ ሁነቶች አክብሯል።

በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ዋና ዳይሬክተር አቶ መሀመድ ሰይድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በአገሪቷ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ናቸው ተብለው ከሚጠቀሱት ጉዳዮች አንዱ የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ ሲሆን፤ ይህም ዜጎችን ለእንግልት እየዳረገ ይገኛል። በመሆኑም ይህንን ችግር ለመፍታት ኮሚሽኑ በአገልግሎት አሰጣጥ ዙርያ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የአሰራር ማሻሻያዎችን እየዘረጋ ይገኛል።

ዋና ዳይሬክተሩ፤ አገልግሎት አሰጣጡ ለዜጎች ፈጣን፣ ተገማችና ዘመኑን የዋጀ ካለመሆኑ የተነሳ የመልካም አስተዳደር ችግር በተለያዩ ቦታዎች እንደሚስተዋሉ ጠቁመዋል። በአንዳንድ ተቋማት አገልግሎትን በገንዘብ የሚሸጥበት ሁኔታ ጭምር እንዳለ ጠቅሰዋል።ይሄንና መሰል የአገልግሎት አሠጣጥ ችግሮችን ለመፍታት ኮሚሽኑ የመሪ ተቋም ኃላፊነት ወስዶ የተለያዩ የአሰራር ማሻሻያዎችን እየዘረጋ ይገኛል ነው ያሉት።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ሲቪል ሰርቪሱ ለዜጎች የሚሰጠውን አገልግሎት ተገማች የማድረግ ኃላፊነት አለበት። የሚሰጡ አገልግሎቶች ለዜጎች ቀድመው መታወቅ አለባቸው። ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን ይገባቸዋል። በጊዜ፣ በመጠን፣ በጥራትና በወጪ ደረጃ ወጥቶላቸው ዜጎች እንዲያውቁ ተደርጎ ጉድለት ሲያጋጥምም ዜጎች ቅሬታቸውን የሚገልጹበትና አገልጋዮችን ተጠያቂ የሚያደርጉበት ሥርዓት እየተዘረጋ ይገኛል።


ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

በሌላ በኩል ተቋማት የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ዘመኑን የዋጀ እንዲሆን በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ እየተሰራ መሆኑንም ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል። ዜጎች ባሉበት ቦታ ሆነው እንዲገለገሉ ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ታግዘው መስጠት አለባቸው በሚል ታስቦ እንቅስቃሴ ውስጥ ተገብቷል ነው ያሉት። በዚህም በአደረጃጀትም ሆነ በአሰራር ከሚሽኑ ራሱን እያደሰ እንዳለ ጠቁመዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኮሚሽኑ በአገልግሎት አሰጣጡ የፌዴራል ተቋማቱንም የአገልግሎት ማሻሻያ የመከታተል፣ የመደገፍና የመገምገም ሥራ እያከናወነ ነው ብለዋል።

የአዲስ ዓመት መሸጋገሪያ አምስቱ ቀናት በመንግሥት ደረጃ በተለያዩ ዝግጅቶች እንዲከበሩ ከተወሰኑት ውስጥ የአገልጋይነት ቀን አንዱ መሆኑን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ ኮሚሽኑ ዕለቱን በተለያዩ ሁነቶች እንዳከበረ አስታውቀዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ለተገልጋዮች ቅርብ ለመሆንና ተገልጋዮች ባሉበት ቦታ ሆነው ያለ እንግልት እንዲገለገሉ የማድረግ ሥራን ጨምሮ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ዕለቱ ተከብሯል። በዚህም ተገልጋዮች የትራንስፖርት ችግር እንዳይገጥማቸው ቤታቸው ድረስ የመሸኘት ሥራ ተከናውኗል። ከዚህም ባሻገር የኮሚሽኑ ሠራተኞች የፅዳት ሥራን አከናውነዋል።

“ተግባራቱ በዛሬው ዕለት ብቻ ተከውነው የሚያልፉ አይደለም” ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሲቪል ሰርቪስ የህዝብ አገልጋይ እንደመሆኑ ህዝብን በማገልገል ኩራት ይሰማኛል በሚል፤ በመንፈስም ሆነ በተግባር መግለጽ እንደሚያስፈልግ በመጠቆም፤ “ሠራተኛው የአገልጋይነት ስሜቱን በላቀ ሁኔታ የሚያስቀጥልበትን ሁኔታ እየፈጠርን ነው” ብለዋል።


ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

## “አገልጋይነት ለሰራዊቱ እስከ ሕይወት መስዋዕትነት የሚደርስ የዓላማ ጽናት ነው"

- ሜጀር ጄነራል ጥሩዬ አሰፌ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ራያ ቆቦ፡- ለጀግናው መከላከያ ሰራዊት አገልጋይነት ማለት እስከሕይወት መስዋዕትነት የሚደርስ ጽናት ነው ሲሉ ሜጀር ጄነራል ጥሩዬ አሰፌ ተናገሩ።

ሜጀር ጄነራል ጥሩዬ አሰፌ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ ሁሉም በሙያው አገልጋይ ነው፤ መከላከያ ሰራዊትም ሕይወቱን ጭምር በመገበር አገሩን እያገለገለ የሚገኝ የሕዝብ አለኝታ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አገልጋይነት ማለት ለመከላከያ ሰራዊቱ በመስዋዕትነት አገርን መጠበቅ ነው ያሉት ሜጀር ጄነራል ጥሩዬ፤ ሕይወት አይተካም፤ ሰራዊቱ ግን በአገሩ ጉዳይ ሕይወቱንም ለመስጠት ዝግጁ ሆኖ በዱር በገደሉ እየተዋደቀ ይገኛል ብለዋል።

ሰራዊቱ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ለሰላም ሲል ደሙን እያፈሰሰ አገር ለማጽናት ሁሌም ዝግጁ ሆኖ ይጠብቃል ሲሉ ገልጸዋል።

ቤተሰብ፣ ዘመድ አሊያም ሌላውንም ትቶ አገር ትቀድማለች በሚል ከልብ የመነጨ ስሜት ግንባር ላይ የሚፋለመው ሰራዊት አገልጋይነት ምን ማለት ነው የሚለውን ትርጉም በአግባቡ የሚገልጽ እንደሆነ ገልጸዋል።

ሜጀር ጄነራል ጥሩዬ እንዳስታወቁት፤ ሰራዊቱ ሌትም ቀንም የአገርን ህልውና ለማስከበር እና ሰንደቋን ላለማስደፈር ይዋደቃል። ለአገር ክብርና ለህዝብ ደህንነትም እስከመጨረሻው ትግል ያደርጋል። ይህንን ደግሞ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያሉ የኢትዮጵያን ሰላም የማይመኙ አካላት ጠንቅቀው ያውቁታል።

በተለያዩ ጊዜያትም ወራሪዎች ሲመጡ የህዝቡን ሰላም ለማስጠበቅ አስፈላጊውን ሁሉ መስዋዕትነት የከፈለው የመከላከያ ሰራዊት ፤ ይህን አገራዊ ስሜቱን ደግሞ በተግባርም በተለያዩ ጊዜያት በግልጽ አሳይቷል ብለዋል።

እንደ ሜጀር ጄነራል ጥሩዬ ገለጻ፤ መከላከያ ሰራዊት ሕዝብን ሲያገለግል ለአካሉ ሳይሳሳ አጥንቱን ከስክሶ ደሙንም አፍስሶ ነው፤ ይህን ደግሞ ዓለምም ያውቀዋል። በየግንባሩም የሚታየው ይህ ሃቅ ነው።

በየግንባሩ የተሰለፈው መከላከያ አገርን ለማዳን ሥራውን የሚያከናውነውና ሕዝብን የሚያገለግለው ለነብሱም ሳይሳሳ ነው፤ ይህን ከልብ የመነጨ የአገር ፍቅር ስሜቱን ደግሞ ማንም ሊወስድበት አይችልም ብለዋል።

ኢትዮጵያን የጀግኖች አገር ያስባለው የሰራዊቱ ጥንካሬና የድል ውጤት ነው፤ ይህንን የአገልጋይነት መንፈስ በተጠናከረ ሁኔታ ለማስቀጠል የሚደረገው ጥረት አልተቋረጠም ሲሉ ሜጀር ጄነራል ጥሩዬ ተናግረዋል።

ለዚህ አገልጋይ ለሆነ ሰራዊት የየአካባቢው ህብረተሰብ የሚደረገው ድጋፍ አስደሳች ነው ያሉት ሜጀር ጄነራል ጥሩዬ፤ መላው ኢትዮጵያውያን ለሰራዊቱ የሚያቀርቡት ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

# የበዓል ገበያው ሲቃኝ

**ሳሙኤል ወንደሰን እና በኃይሉ አበራ**

አዲስ ዓመት ገበያው ደርቷል። የበጉ፣ የቄጤማው፣ የዶሮው፣ የሽንኩርቱና መሰል የበዓል ገበያዎች ሞቅ ደመቅ ብለዋል።ገዥውም አንዱ ከአንዱ እያማረጠና ዞር ዞር ብሎ እየጠየቀ እየገዛ ይሄዳል።ሌላ ገዥም ይመጣል።

በሰሜን ማዘጋጃ አካባቢ ባለው ሾላ ገበያ ዶሮ ከ300 እስከ 750 ብር፣ እንቁላል በሸማች ማህበሮች በኩል ሰባት ብር እየተሸጠ ይገኛል። አምስት ሊትር ፈሳሽ ዘይት በ880 ብር ለህብረተሰቡ እየቀረበና ሸማቾችም እየገዙ ሲሄዱ በቦታው ተገኝተን ተመልክተናል።

ሽንኩርት እስከ 50 ብር ደርሶ የነበረ ቢሆንም ገበያውን ለማረጋጋት በኦሮሚያ ልዩ ዞን ከሚገኙ አርሶ አደሮች እና ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋር ትስስር በመፈጠሩ አሁን ከ30 ብር እስከ 37 ብር እየተሸጠ ነው። እስካሁን ባለው ገበያ ሁኔታ የተጋነነ ዋጋ አለመኖሩን የኢትዮጵያ ፕሬስ ጋዜጠኞች በተለያዩ የአዲስ አበባ የገበያ ቦታዎች በመሄድ ማረጋገጥ ችለዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ህብረተሰቡ ለበዓል የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ለመግዛት በተለያዩ ባዛሮች ሲገበያይ ይስተዋላል። በአራዳ ክፍለ ከተማ አዘጋጅነት እየተካሄደ በሚገኘው ባዛር ቅመማ ቅመሞችን ስትሸጥ ያገኘናት ወጣት ገነት ገብረማርያም፤ ለበዓል የሚያስፈልጉ ሁሉንም ቅመማ ቅመሞችን አዘጋጅተን ለገበያ አቅርበናል ስትል ትናገራለች።

ከአንድ ዓመት በፊት የነበረው የቅመማ ቅመሞች ዋጋ ተመጣጣኝ እንደነበር የምታስታውሰው ወጣት ገነት፣ በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ በእያንዳንዱ ቅመማ ቅመም ላይ የሃያ ብርና ከዛ በላይ የዋጋ ጭማሪ መኖሩን ገልጻለች። ይህ ደግሞ የገበያው ሁኔታ እንዲቀዛቀዝ አድርጎታል ባይ ናት።

እንደ ወጣት ገነት ገለጻ፣ ከዚህ በፊት ሸማቹ ሶስት አራት እቃዎችን በአንድ ጊዜ ይገዛ ነበር። በአሁኑ ጊዜ በዋጋ ጭማሪው ምክንያት አንድ ነገር ብቻ ገዝቶ ይሄዳል። ቢሆንም ከአምናው የተሻለ የግብይት አውድ መፍጠር ተችሏል ትላለች።

በሾላና አዋሬ ገበያም የደራ ነው። የዘንድሮው በዓል ዋጋ በተለይ ከአምናው ጋር ሲነጻጸር የተረጋጋ መሆኑን ሸማቾችና ነጋዴዎች ይናገራሉ።

በሾላ ገበያ የበግ እና የፍየል ንግድ ላይ ያገኘናቸው አቶ አረቦ መሀመድ፣ አዲስ ዓመት ገበያ ከሁሉም የአገሪቱ አቅጣጫ ስለሚገባ እና የክረምት ወር በመሆኑ በግ እና ፍየል ዋጋቸው ተመጣጣኝ ነው ብለዋል።

በገበያዎቹ የበግ ዋጋ ከ3000 እስከ 9000 ብር፣ የፍየል ደግሞ ከ4000 እስከ 12000 ሺህ ብር ዋጋ ሲጠራበት



ታዝበናል። ነገር ግን ሸያጩ ከዚህ ሊቀንስ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። አምና እስከ 10 ሺህ ብር የተሸጠው በግ ዘንድሮ እስከ ስምንት ሺህ ብር እየተሸጠ መሆኑን ነግረውናል።

አምና ስድስት ሺህ ብር የነበረው ፍየል ዘንድሮ አምስት ሺህ ብር ፤በግ ደግሞ ስድስት ሺህ ብር የነበረው እስከ 500 ብር ቅናሽ አሳይቷል። በሾላ ገበያ እንቁላል ከስምንት እስከ 12 ብር የሚሸጥ ሲሆን፣ ቅቤ ከ550 እስከ 800 ብር፣ ሽንኩርት ከ45 እስከ 50 በችርቻሮ እየተሸጠ ነው።

በሾላ ገበያ ሲገበያዩ ያገኘናቸው ወይዘሮ ወይንሸት ጸጋዬ በበኩላቸው ዶሮ አምና 900 መቶ ብር የገዙ ሲሆን ዘንድሮ ግን ሁለት የሀበሻ ዶሮ 1600 ብር መግዛታቸውን ነግረውናል። ነጭ ሽንኩርት ኪሎ 200 ብር፣ ሚጥሚጣ አንድ ኪሎ 250 ብር፣ እንቁላል የሀበሻ 13 ብር ገዝቻለሁ ። የእንቁላል ዋጋ በየወቅቱ የሚቀያየር ነው ብለዋል። ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚደረገው ድጋፍ እንዲቀጥል አገራችን ሰላም እንዲሆን፣ አብሮ የመብላት ባህላችን ይቀጥል ሲሉ ተመኝተዋል።

በአራዳ ክፍለ ከተማ አዘጋጅነት እየተካሄደ ባለው ባዛር ለበዓሉ የሚሆኑ ዕቃዎችን ለመግዛት በባዛሩ ያገኘነው አቶ ንጋቱ ደገፉ በበኩሉ፣ የህብረተሰቡ የበዓል ዝግጅት ከአምናው የተሻለ ነው። ነገር ግን ህብረተሰቡ እንደበፊቱ በርካታ ቁሳቁሶችን ይገዛል ብዬ አላስብም። ምክንያቱ ደግሞ ሀገሪቷ ላይ እየተከሰተ ያለው የኑሮ ውድነት ሸማቹ በፈለገው ልክ እንዲገዛ አያስችለውም ብሏል።

በአሁኑ ወቅት ለእለት ፍጆታ የሚያገለግሉ ምርቶች ዋጋቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል የሚለው አቶ ንጋቱ፣ ህብረተሰቡ ለእለት ጉርሱ የሚያስፈልጋቸውን ምርቶች ይገዛል እንጂ ለልብስ አሊያም ለጌጣጌጦች የሚውል ወጪ ማውጣት አይፈልግም የሚል ሀሳብ አለው።

እንደ አቶ ንጋቱ ገለጻ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ አዲስ ዓመትን ሲያከብር የተቸገሩ ወንድሞቻችንን በማሰብና በመርዳት መሆን ይኖርበታል። ይህ ደግሞ ከእናትና አባቶቻችን የወሰድነውና የተማርነው ሥነ ሥርዓት ነው። ህብረተሰቡ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት መጪውን አዲስ ዓመት የኢትዮጵያ ሰላምና ብልጽግናን ተስፋ አድርጎ ማክበር ይኖርበታል ብሏል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ቢሯቸው የአዲስ ዓመት በዓል አከባበር ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ የዋጋ ንረትን ለማርገብና የተረጋጋ የግብይት ስርዓት እንዲኖር ሲባል ቅድመ ዝግጅት አድርጓል።

በዓሉን ተከትለው የሚመጡትን ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር እና ስርዓት ያለው የዋጋ ግብይት እንዲፈጠር ሲባል ግብረ ኃይል ተቋቁሟል።ይህ ግብረ ኃይልም በየገበያ ቦታዎች እየሄደ ሁኔታዎችን ይከታተላል፤ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ የእርምት እርምጃ ይወስዳል ብለዋል።

አሮጌው ዘመን በአዲሱ የመቀየሩን ብሥራት አብሣሪው የአዲስ ዓመት (ዕንቁጣጣሽ) በዓል፤ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልዩ ሥፍራ ከሚሰጣቸው በዓላት ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው። የጨለማ ተምሳሌት የሆነው ጭጋጋማው የክረምት ወቅት አልፎ፣ ምድር በአደይ አበባ ተጥለቅልቃ በልምላሜ የምትታይበት የብርሃን ወቅት ነው።

ዜና

# በመጪው ዓመት በበጋ መስኖ 40 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማምረት ታቅዷል

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- በ2015 ዓ.ም በበጋ መስኖ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ በማልማት 40 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ለማምረት ዕቅድ መያዙን የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ዶክተር ፍጹም ገለጹ። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሰሜኑን ጦርነት ጨምሮ ብዙ የውጭና የአገር ውስጥ ፈተናዎች ቢያጋጥሙትም እነዚህን ተቋቁሞ ዕድገት ማስመዝገብ ችሏል።

ዶክተር ፍጹም 'ፈተና፣ ድል፣ ተስፋ' በሚል ርዕስ የ2014 በጀት ዓመትን ዐበይት የመንግሥት የሥራ ክዋኔዎች የሚዳስስ የአዲስ ወግ የውይይት መርሐ ግብር ሰሞኑን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ባለፈው ዓመት በበጋ መስኖ 600ሺህ ሄክታር መሬት በማልማት 26 ሚሊዮን ኩንታል ማምረት ተችሏል።ይህን ስኬት በማስፋትም በመጪው ዓመት በበጋ መስኖ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 40 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማምረት ዕቅድ ተይዟል።

ከውጭ የሚገባን ስንዴ በአገር ውስጥ ምርት ለመተካትና በምግብ ራስን ለመቻል ከ600 ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ በስንዴ ሰብል በማልማት 26 ሚሊዮን ኩንታል የሚጠጋ የስንዴ ምርት መሰብሰብ መቻሉን አመልክተው፤በአጠቃላይ የበልግን ሳይጨምር በክረምትና በበጋ 90 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማምረት እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

በመጪው ዓመትም የስንዴን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ዝግጅት መደረጉን ገልጸው፤በበጋ ስንዴ የተገኘውን ውጤታማ ሥራ በወተት፣በእንቁላል፣በዶሮና በማር ምርት ለመድገም በመጪው ዓመት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሰሜኑን ጦርነት ጨምሮ ብዙ የውጭና የአገር ውስጥ ፈተናዎች ቢያጋጥሙትም እነዚህን ተቋቁሞ ዕድገት ማስመዝገብ ችሏል ያሉት ዶክተር ፍጹም፤ ዕድገቱም የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ በውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ምርትና ምርታማነት በማሳደግ እና የውጭ ኢንቨስትመንት በመጨመር ረገድ ተጨባጭ ለውጥ የታየበት መሆኑን አብራርተዋል።

የኢኮኖሚ ዕድገቱ አንዱ መለኪያ ዜጎችን የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ማድረግ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ፍጹም፤ በበጀት ዓመቱ ለሁለት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ዜጎች አዳዲስ ቋሚ የሥራ ዕድል መፈጠራቸውንና እነዚህ ዜጎች የሥራ ዕድል ተጠቃሚ መሆናቸውና ገቢ ማግኘታቸው አንዱ ስኬት መሆኑን ተናግረዋል።

ሌላው የኢኮኖሚ ዕድገቱ ማሳያ የውጭ ምንዛሪ ግኝት መሆኑን ጠቅሰው፤ ባለፈው በጀት ዓመት ከሸቀጥ ንግድ ፤ከአገልግሎት፤በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለዘመዶቻቸው ከሚልኩት ገንዘብና ከውጭ ኢንቨስትመንት 22 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ የውጭ ምንዛሪ መገኘቱን አብራርተዋል።

ለአብነትም ከአገልግሎት ሴክተሩ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ስድስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ዶላር መሆኑን አመልክተው፤ይህም ከ2013 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር 29 በመቶ ብልጫ እንዳለው ተናግረዋል።የኢትዮጵያ አየር መንገድ ብቻ አራት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ማግኘቱን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች የዓለም አገራት ብዙ ችግሮች እያጋጠሙ ቢሆንም ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ሶስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ተገኝቷል ያሉት ዶክተር ፍጹም፤ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያኝ ለዘመዶቻቸው ከላኩት ገንዘብ ሰባት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን ገልጸዋል።

ሌላው የኢኮኖሚ ዕድገቱ ተጨባጭ ማሳያ የገቢ መጨመር መሆኑን ገልጸው፤በበጀት ዓመቱ 360 ቢሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ የሰሜኑ ጦርነት ጨምሮ ሌሎች የአገር ውስጥና የውጭ ፈተናዎች ሳይበግሩት 336 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰቡንና ይህም ከ2013 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር 26 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን አብራርተዋል።

እንደ ዶክተር ፍጹም አገላለጽ፤ ፋይናንስ ዘርፉም በባንኮች ያለው ተቀማጭ ገንዘብ አንድ ነጥብ ሰባት ትሪሊዮን ብር ደርሷል። ከዓምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸርም 25 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። 276 ቢሊዮን ብር ብድር ተመላሽ ተደርጓል። ይህም ከ2013 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር 48 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል። ይህም ተጨባጭ ለውጥ የመጣው ኢኮኖሚው ችግሮችን ተቋቁሞ ዕድገት በማስመዝገቡ ነው።

በግብርና ዘርፍ በዋናዋና ሰብሎች ብቻ 336 ሚሊዮን ኩንታል ምርት መገኘቱን ጠቅሰው፤ ይህ ምርት የተገኘው በሰሜኑ ጦርነትና ከፍተኛ ድርቅ ባጋጠመበት ጊዜ በመሆኑ ችግሮቹን ተቋቁሞ ዕድገት ማስመዝገብ እንደሚቻል ግብርናው ዘርፍ አንዱ ማሳያ ነው ብለዋል።

ወተት ዶሮ እንቁላል በመጪው ዓመት እንደ በጋው ስንዴ ሁሉ ስኬት ለማስመዝገብ ዕቅድ መያዙን ጠቅሰው፤ አጥጋቢ ሥራ በመስራትም ለውጥ ለማምጣት የትኩረት አቅጣጫ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በመጪው ዓመት ህዝቡን እያማረረ የሚገኘውን የዋጋ ንረት ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ረገድ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ ገልጸው፤ ከዚህ ጎን ለጎንም የገበያ ሰንሰለቱን ለማሳጥር፣ ቁጥጥርና ክትትልን ለማጠናከር የሚያስችሉ ሥራዎችም በትኩረት እንደሚሰሩም ጠቁመዋል።

# የጥላቻ ትርክቶች አንድነትን በሚያጠነክሩ አዳዲስ ትርክቶች ሊተኩ ይገባል

ዘላለም ግዛው



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን አንድነትን የሚሸረሽሩ፣ የሚያለያዩ፣ የሚከፋፍሉ እና የተዛቡ የጥላቻ ትርክቶችን አስወግደው አንድነትን በሚያጠነክሩ አዳዲስ ትርክቶች ሊተኩ እንደሚገባ የህገ መንግሥትና ፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሃይለየሱስ ታዬ ገለጹ።

ዶክተር ሃይለየሱስ ዛሬ እየተከበረ የሚገኘውን የአንድነት ቀን አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሃገርን ለመገንባት የተለያዩ ማንነቶችን በመያዝ በአንድነት አንድ ጠንካራ የጋራ አገር መፍጠር ላይ ማተኮር ይገባል።

የተሻለ ሃገራዊ ዕድገት ለማምጣት የኢትዮጵያውያንን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ብዝሃነትን በመያዝ አንድነትን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ማመን ይገባል ሲሉም አመልክተዋል።

መተማመን በፌዴራሊዝም ስርዓት ትልቅ እሴት ነው ያሉት ዶክተር ሃይለየሱስ፤ የአንድነት እና የወንድማማችነት ትርክት ያስፈልገዋል እንጂ በጥላቻ ትርክት ላይ በመመስረት እና መለያየትን በመስበክ አንድነትን መገንባት አይቻልም ብለዋል። ችግሮቹ ባለፉት ስርዓቶች የተፈጠሩ በመሆናቸው አሁን ባለው ሁኔታ ተወያይቶ መፍታት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

ባሉ አለመግባባቶች እና የሃሳብ ልዩነቶች ዙሪያ በደንብ በመወያየት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ልዩነቶችን ትቶ በአዲስ ትርክት፣ በወንድማማችነት እና በአብሮነት መቀጠል ይገባል። የፌዴራሊዝም ትርክትም የሚገነባው በእነዚህ በጎነቶች ነው ሲሉም ተናግረዋል።

‹‹የፌዴራሊዝም ስርዓትና የፖለቲካ ስርዓት ካፈጣጠሩ ጀምሮ በትክክል ያልተረዳነውና ያልተገበርነው አስተሳሰብ ነው›› ያሉት ዶክተር ሃይለየሱስ፤ የፌዴራሊዝም ስርዓት መነሻው አንድነት መሆኑን መረዳት እንደሚጠይቅ ነው የተናገሩት።

ስርዓቱ የድርድር፣ የንግግር እና የትብብር መሆኑ ነው የሚታወቀው። በተግባርም ነገሮችን በትብብር በቅንጅት የመስራት ባህልን መገንባት ያስፈልጋል። የህግና የሕገ መንግሥታዊነት ስርዓት እንደመሆኑም የሴራ ፖለቲካ መጥፋት አለበት ብለዋል።

በፌዴራሊዝም ስርዓት የሚለያይና የሚከፋፍል ሃሳብ በተግባርም በጽንሰ ሃሳብ ደረጃም ማሰራጨት ትክክል አይደለም። የሰው ልጆች የራሳቸውንና የጋራ ጉዳያቸውን አስተሳስረው ሚዛን በማስጠበቅም አንድነት ለማምጣት የሚተገበር ስርዓት ይሁን እንጂ ቀደም ሲል የተተገበረበት መንገድ ትክክል እንዳልነበረም ነው ያስታወሱት።

ዶክተር ሃይለየሱስ እንደተናገሩት፤ ብሔራዊ ምክክሩ በርካታ ነገሮችን እንደሚፈታ ይጠበቃል። ልዩነት እና አንድነትን ሚዛን ማስጠበቅ ይገባል። አመለካከት እና አስተሳሰብ ላይ ሰፊ ሥራ መስራት፣ ትክክለኛ የፌዴራሊዝም መልክ ያላቸውን ተቋማት መገንባት ያስፈልጋል።

ውይይቱ ሲካሄድ ህዝቡ በሂደቱ በንቃት ለመሳተፍ ካሁኑ መዘጋጀት ይኖርበታል ያሉት ዶክተር ሃይለየሱስ፤ በአገር ጉዳይ መሰረታዊ እውቀትና መረጃ ለመጨበጥ ጥረት ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ተጽእኖ ፈጣሪዎች፣ ምሁራን፣ ፖለቲከኞች ትልቁን ሥራ ሊሰሩ ይገባል። የአገርን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ፣ ያለውን ተጨባጭ ችግር ሊፈታ የሚችል አስተሳሰብ ይዘው ሊቀርቡ ይገባል። ተጨባጭ ሃሳቦችን ይዘው መንቀሳቀስ ይጠቅማልም ሲሉ አስረድተዋል።

ያለንበት ዘመን መብት የሚጠየቅበት ነው ያሉት ዶክተር ኃይለየሱስ፤ መብቶች ተቻችለውና ተሰናስለው በአንድ አገር ውስጥ ተተግብረው አንድነት የሚመጣበትን መንገድ መከተል ያስፈልጋል። ተጨባጭ የሆነ የመፍትሄ ሃሳቦችን በማመንጨት ችግሮችን መፍታትም ይገባል። ማሕበረሰቡንም በማሳተፍ ከተሰራ አብሮ የመኖር ጥበብ ላይ ብዙ መፍትሄ ሊያመጣ ይችላል ብለዋል።

# አዲስ ዓመት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዘመን ልጆችም ከአያቶቻችን የወረስነውን ጀግንነት አስጠብቀን ለትውልድ ማውረስ ይጠበቅብናል" ብለዋል።

አሁን ላይ የውጊያ መልክና ቅርጽ መቀየሩን አስታውሰው፣ "እኛ የምንጠቅሰው ሀገራዊ ጀግንነት በእነዚህ መለዋወጦች ምክንያት ምን ያህል እንደተፈተነ በሁለተኛው የጣልያን ወረራ ወቅት አይተናልም" ነው ያሉት።

የእኛ የዝግጁነት መጠን ከዓለም ለውጥ ጋር አብሮ ያለመሄዱ፣ ሀገር እስከማሳጣት የሚያደርስ ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍለን ይችላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ዛሬም ጠላቶቻችን እንደ ድሮው በቀጥታ ውጊያ ሳይገጥሙን የሚያሸንፉበትን መንገድ ከመንደፍ ወደኋላ እንደማይሉ ነው የጠቆሙት።

በድንበር አካባቢ ከሚሰነዝሩብን ቀጥተኛ ጥቃቶች ባለፈ፣ የሽብር ስልጠና የወሰዱ ሰዎችን አስርገው በማስገባት የሚያካሂዱት የሽብር ተግባር ምን ያህል ፈተና ውስጥ እንደሚያስገባን ይታወቃል ሲሉም አስረድተዋል።

የሀገር ውስጥ ታጣቂዎችንና ያኮረፉ ኃይሎችን ተጠቅመው ሀገራችንን ገዝግዘው ለመጣል ዘወትር እንደቋመጡ መሆኑን ጠቁመው፣ በአንድ በኩል እኛ በምድርና በአየር የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን በተጠንቀቅ ስንጠብቅ፣ በሌላ በኩል የሳይበርና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻው ፋታ በሚያሳጣ መልኩ ይጎርፋል፤ ይህ እውነታ ዘወትር ነቅተን እንድንጠብቅ ግድ ብሎናል ብለዋል።

ጠላቶቻችንን በስትራቴጂ በልጠን እስካልተገኘን ድረስ ሉዓላዊነታችን በአስተማማኝ መሰረት ላይ አይቆምም ሲሉም ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የገለጹት።

በተለይ አሁን የኢትዮጵያን ተስፋ የሚያለመልሙ አጋጣሚዎች በየአቅጣጫው የተከፈቱበት ወቅት መሆኑንም አንስተዋል።

እኛም ጠላት እንዳይበዛብን ብለን ወደ ከፍታው ከምናደርገው ጉዞ አንገታም ሲሉም አስገንዝበዋል።

በአንድ በኩል የህዳሴ ግድብ ወደ መጠናቀቁ ላይ መሆኑ፣ በሌላ በኩል በምግብ ራሳችንን የመቻል እርምጃችን ውጤት ማምጣት መጀመሩ እንዲሁም ቀጣናዊና አህጉራዊ ተጽዕኖችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ "ይቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም" በሚል ብሂል ተስፋችንን በእንጭጩ ለማስቀረት የሚቋምጡ ኃይሎች በዝተዋል ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በመልዕክታቸው።

ሠራዊት ለጦርነት የሚዘጋጀው አውዳሚ የሆነ ጦርነትን ለማስቀረት የሚያስችል አቅም ለማዳበር መሆኑንም ገልጸዋል።

ሠራዊቱም "አቅሙን ለማደርጀት ዘወትር መትጋት አለበት" ስንል ሌሎች ላይ ጥቃት ለመሰንዘር እያሰብን ሳይሆን ሀገርን ከጠላት ትንኮሳ በብቃት መከላከል እንድንችል በማሰብ ነው ሲሉም ነው ያስረዱት።

"ጠላቶቻችን አርፈው የሚቀመጡት በሁሉም ዘርፍ ብቃት ላይ መገኘታችንን ሲያውቁና በስትራቴጂም ይሁን በቁሳቁስና በቴክኖሎጂ አቅም በልጠው ሊያሸንፉን እንደማይችሉ ሲያውቁ ብቻ ነው" ሲሉም አመላክተዋል።

# "የትግራይ ወጣት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አልባና የቀቢጸ ተስፋ ጦርነት ሲሆን ምናልባት የቡድኑ ህልውና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያከትምበት ጦርነት ይሆናል ብለዋል።

ሕወሓት ለ27 ዓመታት ያህል ያለምንም ተቀናቃኝ አገሪቱን በጉልበት ሲገዛ ቆይቶ በህዝባዊ እምቢተኝነት ከሥልጣን ሲወገድ ያልለመደው እኩልነት የበታችነት መስሎት በአገሪቱ ላይ በተለይ በትግራይ ህዝብ ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው በደል እየፈጸመ ይገኛል ሲሉም ተናግረዋል።

ከለውጡ ወዲህ በሌሎች ክልሎች ልማትና የህዝብ አገልግሎት ተቋማት በፍጥነት እየተስፋፉ ባለበት ሁኔታ በተቃራኒው ሕወሓት ለውጡን ላለመቀበልና ወደ ነበረበት ለመመለስ በተደጋጋሚ ጦርነት በመክፈቱ ምክንያት ክልሉ የደህንነት ተምሳሌት እንዲሆን ማድረጉን የገለጹት ዶ/ር አረጋዊ፣ ከዚህ አንጻር በቡድኑ እኩይ ድርጊት በክልሉ የወደሙ መሰረተ ልማቶችና ህዝባዊ አገልግሎቶች መጠገን ወይም መሥራት ስለማይቻል በአሁኑ ጊዜ የትግራይ ህዝብ በብዙ መልኩ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ መግባቱን ገልጿል።

የትግራይ እናት መቦረቅ ያልጠገበው ልጇ በቡድኑ ተገዶ ወደ ጦርነት እየተማገደ የጥይት ሲሳይ ሲሆን አይታ ከማልቀስ ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌላት የተናገሩት የፓርቲው ሊቀመንበር፣ እስካሁን እንደ ማስፈራሪያ ሲጠቀም የነበረው በእርዳታ የሚመጣን እህል እንደሆነ ተናግረዋል።

ነገር ግን በክልሉ ያለውን የከፋ ረሃብ ማስታገስ የማይችል ከመሆኑም በላይ በዓለም ተጨባጭ ሁኔታ በዘላቂነት በእርዳታ ብቻ የኖረና ችግሩን የፈታ አገር ስለሌለ ህዝቡ ከሚመጣው አስከፊ ችግር ለመላቀቅ መወሰን እንዳለበት ጠይቀዋል።

ባለፉት ሶስት ዓመታት የሽብር ቡድኑ ጨምድዶ በመያዙ ምክንያት በኢኮኖሚ ክፉኛ የተጎዳ፣የታፈነ፣በሥነ ልቦና ቀውስ የተዳረገና በሁሉም ረገድ ወደኋላ የቀረ እንደ ትግራይ ያለ ክልልና ሕዝብ እንደሌለ የተናገሩት ዶክተር አረጋዊ፤ ይህንኑ ደግሞ ሕወሓት ራሱ አምኖ በግልጽ ሲናገር መቆየቱን አንስተዋል።

ነገር ግን ቡድኑ የሚናገረውንና የሚሰራውን የማያውቅ በመሆኑ ሰሞኑን አፈትልኮ በወጣው ሚስጥራዊ ሰነዱ የትግራይ ህዝብ ከሌላው ህዝብ የተሻለ እየኖረ መሆኑን መግለጹ ይታወሳል።

በመሆኑም የትግራይን ሕዝብ ከተጋረጠበት ፈረጀ ብዙ አደጋ ለመታደግ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ዶክተር አረጋዊ አስገንዝበዋል።

ፓርቲያቸውም በተለይ ወጣቱን ከአፈና ለመላቀቅ ቀደም ሲል ከአማራ ወጣቶች ጋር የጀመራውን አንዳንድ እንቅስቃሴዎች አጠናክሮ እንደሚቀጥሉና የተለያዩ እንቅስቃሴዎችንም እንደሚያደርጉ የጠቆሙት ዶ/ር አረጋዊ፣ የትግራይ ህዝብ "ኢትዮጵያ ወደር የለሽ እናቴ ናት" የሚል የአጼ ተዎድሮስ መፈክር በማጤን ችግሩን ለወንድም ህዝቦች እንዲያካፍል መክረዋል።

ከቡድኑ ሾልኮ የወጣው ሰነድ እንደሚያመላክተው የቡድኑ መጨረሻ ግብ ያለና የሌለ ሀይሉን በማሰባሰብ አራት ኪሎ በመግባት በሕዝብ የተመረጠውን መንግሥት በሀይል በማስወገድ ሥልጣን የመያዝ ህልሙ የቀን ቅዠት ነው ያሉት ዶ/ር አረጋዊ፣ በሕዝብ ተመዝኖ የተተፋው ቡድን ይቅር አራት ኪሎ ወልዲያንም ማለፍ እንደማይችልና ይልቁንስ ወደ መቃብር እየተቃረበ መሆኑን ቢገነዘብ መልካም ነው ብለዋል።

በውጭ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆችና ወዳጆች ቀደም ሲል ሕወሓት ከከፈተው ጦርነት የትግራይ ሕዝብ ከችግርና መከራ ውጪ ያተረፈው ነገር ስለሌለ ለአውዳሚ ጦርነት ለሕወሓት ጥይት ከማቀበል ተቆጥበው ሕዝቡ ከቀውስ ተላቅቆ ከሌላው ወንድም ሕዝቦች ጋር በሰላም የሚኖርበትና ትግራይን መልሶ የሚገነባበት ሁኔታ እንዲፈጠር የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡም ጠይቀዋል።

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹የዓባይ ግድብ ቀድሞ የነበረውን የኢትዮጵያውያንን አንድነት የመለሰ ነው››

*- ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ*

*በአ.አ.ዩ. ዩኒቨርሲቲ መምህርና የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪ*



አስቴር ኤልያስ

የተወለዱት በቀድሞ ከምባታ አውራጃ በያያማ አካባቢ፣ ዘገሾ መንደር በ1943 ዓ.ም ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በትውልድ አካባቢያቸው ከምባታ እንዲሁም በወላይታ ተምረዋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በአዲስ አበባ እና በአምቦ ጉደር የተማሩ ሲሆን፣ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋም ብቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ ደግሞ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አቅንተው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ለመማር በቅተዋል - የዛሬው የዘመን እንግዳችን ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ።

በዓባይ ግድ ጉዳይ ላቅ ያለ አስተዋጽዖ በማበርከት የሚታወቁት እንግዳችን ሁለት የማስተርስ ዲግሪ ትምህርታቸውን በአፍሪካ ዓለም አቀፍ ጉዳይና በፖለቲካል ሳይንስ መስክ አሜሪካ ከሚገኘው ኦሐዩ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል። የዶክትሬት ትምህርታቸውን በሲውዘርላድ ከሚገኘው ከታዋቂው ዙሪክ ዩኒቨርሲቲ በናይል ውሃ ጉዳይ በፖለቲካል ሳይንስ መስክ አጠናቀው የፌሎሶል ዶክተርነት ተቀብለዋል። ከትምህርታቸው ባሻገር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት መስክ በማስተማር፣ በምርምርና በማማከር ስራ እየሰሩ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት የፖለቲካል ሳይንስ ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው።

ዶክርተር ያዕቆብ፣ የፖለቲካ ትምህርት ክፍል ሊቀመንበር፣ የሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ዲን እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ዳይሬክተር በመሆን ሰርተዋል። የአፍሪካ፣ የእስያና የአውሮፓ ዩኒቨርሲቲዎች የውሃና ማሕበረሰብ ምርምር አባልና የኢትዮጵያ አስተባባሪ ናቸው። እንዲሁም የሰሜንና የደቡብ አህጉራዊ ምርምር የምስራቅ አፍሪካ ዘርፍ አማካሪ ቦርድ ሊቀመንበር ሆነውም አገልግለዋል። የዋቸሞና የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአመራር ቦርድ አባል እንዲሁም የኢትዮጵያ ካቶሊክ ዩኒቨርሲቲ አማካሪ ቦርድና የኢትዮጵያ የአስተዳደር ወሰንና የማንነት ኮሚሽን አባል ናቸው።

ዶክተር ያዕቆብ ብዙ ናቸው ማለት ይቻላል፤ በኢትዮጵያ የጠፉ ወንዞችና የውሃ ሀብቶችን የመመለስ እንቅስቃሴ አስተባባሪም ናቸው። በብዙ ደርዘን የሚቆጠሩ ሙያ ነክ የምርምርና የስርጸት ጽሑፎችን አበርክተዋል። እንዲሁም በርካታ የሙያ ማጠናከሪያና ማስፋፊያ መጻሕፍትን ከሌሎች የሙያ አጋሮቻቸው ጋር በመሆን ያበረከቱ ሲሆን፣ €€ናይልና ኢትዮጵያ« በሚል ርዕስ ደግሞ መጽሐፍ ማሳተም ችለዋል። በአፍሪካ፣ በኢስያ፣ በአውሮጳና በአሜሪካ ተዘዋውረው ትምህርታዊ ሌክቸር ሰጥተዋል። በድንበር ተሻጋሪ የኢትዮጵያ ወንዞች የድርድር ጉዳይ የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካሪም ናቸው

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ብሔራዊ ፓነል አባልና ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም የሕዳሴ ግድቡ ብሔራዊ የድርድር ቡድን አባል ናቸው። የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ብሔራዊ ምክር ቤት አባል ናቸው። የሰሯቸው ስራዎችና ያለባቸው ኃላፊነቶች ከብዙ በጥቂቱ ይህን የሚመስል ሲሆን፣ ለሰሯቸው ስራዎችና ሳበረከቱት የላቀ አስተዋጽዖ ከተበረከቱላቸው ሽልማቶች ጥቂቶቹ ደግም በጀርመን አገር የሚገኘው ዩኒቨርሲቲ ፒቴር ቤከር የ1999 የሰላም ምርምር ተሸላሚ፣ የ2012 ዓ.ም የዓመቱ በጎ ሰው ልዩ ተሸላሚ፣ የ2013 ዓ.ም የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የዱራሜ ካምፓስ ልዩ ተሸላሚ ናቸው። ሌላው አንድ ሽልማት ጀርመን ሜልበርግ ውስጥ ፊሊፕስ ዩኒቨርሲቲ የሚባል እርሳቸውና የ3ደኛቸው በውሃ ላይ ባቀረቡት ጥናት ገንዘብም ያካተተ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ሰርተፍኬቶች፣ የምስጋና ደብዳቤዎች እና የምስክር ወረቀቶች በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪም ተሰጥቷቸዋል። ከዛሬው ‹‹የዘመን እንግዳችን›› ከዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እነሆ ብለናል።

**አዲስ ዘመን፡- ዶክተር ያዕቆብ የእርስዎና የዓባይ ውሃ ቁርኝታችሁ ጥብቅ እንደሆነ ይታወቃል፤ በዚህ ጉዳይ ለምን ያህል ጊዜ ጥናትና ምርምር አደረጉ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡**-በናይል ወንዝ ላይ ትኩረት ማድረግ የጀመርኩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል በ1972 ዓ.ም የአራተኛ ዓመት ተማሪ ሆኜ ነው። ወቅቱ የኢትዮጵያ እና የሶማሊያ ጦርነት ተጠናቆ ኢትዮጵያ ድል ያደረገችበት ጊዜ ቢሆንም የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ በወቅቱም ቢሆን ትኩሳት ያለበት ነበር።

በወቅቱ በርካታ አገሮች ከሶማሊያ ጎን ሆነው ኢትዮጵያን በመቃወም የሚታወቁ ናቸው። ከዚህም የተነሳ ብዙ ተጽዕኖ ሲፈጥሩ ስለነበር በተለይም ግብጽና ሱዳን በተለየ ሁኔታ ደግሞ ግብጽ ጫናዋ የበረታ ነበር። ግብጽና ሶማሊያ የአረብ ሊግ አባል በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን የሚጎዳ ማንኛውም ነገር በግብጽ በኩል ተደጋፊ በመሆኑም ጭምር ነው። ስለዚህም ይህ ጉዳይ በጂኦፖለቲካው ምክንያት ኢትዮጵያ ላይ ያመጣው ተጽዕኖ ከኢትዮጵያ ውሃ ሀብት ጋር የተገናኘ መሆን አለመሆኑን በመጠየቅ ነበር የተነሳሁት። በተጨማሪም የግብጽና የሶማሊያ መቀራረብ በመሰረቱ ከውሃ ሀብታችን ጋር ባለን ሽኩቻ የተወሳሰበ መሆን አለመሆኑን ጠይቄም ነው የተነሳሁት። የመመረቂያ ጽሑፌንም የጻፍኩት በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው። በናይል ፖለቲካ ላይ ትኩረት አድርጌ ስሰራ የቆየሁት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው። ጉዳዩ በጥቅሉ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ያለው የሃይድሮ ፖለቲካ ጉዳይ፣ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ የሃይድሮ ፖለቲካ ዋናው እምብርት የኢትዮጵያና የግብጽ ሽኩቻና የጥቅም ግጭት ላይ ያጠነጠነ ነው ማለት ይቻላል።

ሌሎች አገሮች ቀስ እያሉ እዛ ላይ መጥተዋል። ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኖርኩት ስለምስራቅ አፍሪካ ሃድሮ ፖለቲካ፣ ስለምስራቅ አፍሪካና ስለመካከለኛው ምስራቅ ሃይድሮ ፖለቲካ ምን አይነት እንደሆነ ስከታተል ነው። በክፍለ ትምህርቴ በኩል ኮርስ አዘጋጅቼ ሥርዓቱን ተከትዬ በዩኒቨርሲቲ አጸድቄ ተማሪዎቻችንን ሳስተምር ቆይቻለሁ። ማስተማር ብቻ ሳይሆን በርካታ የማስተርስ ተማሪዎች ከኢትዮጵያም ከሌሎች አገሮችም እዚህ ማስተርስ የሚገቡ ተማሪዎች ሃይድሮ ፖለቲካ በተለይም ናይልን በተመለከተ ኮርስ ወስደዋል፤ ከኬንያም፣ ከዩጋንዳም እንዲሁም ከሲውዘርላንድ፣ ከፈረንሳይ፣ ከዴንማርክ፣ ከቻይና እንዲሁም ከእስራኤል መጥተው የተማሩ አሉ።

ከዚህ ከማስተምረው ኮርስ ጋር አንድ ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ ዓለም አቀፍ ግንኙነት የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ከደቡብ ሱዳን፣ ከሱዳንና ከግብጽ ድህረ ምረቃ ተማሪዎች ጋር በአንድ ላይ ለአንድ ሳምንት ያህል የፈጀ ሴሚናር አዘጋጅቼ አስተማሪዎቻቸውንም ጭምር እንዲከታተሉ አድርጌያለሁ። ይህ የዓባይ ግድብ ከመጀመሩ በፊት የሆነ ነው።

ሃሳቡ ምንድን ነው ያልሽኝ እንደሆነ ለኢትዮጵያ ቅርብ የሆኑ የውሃ ተቀባዮች ደቡብ ሱዳንን፣ ሱዳንንና ግብጽን በሚመለከት የጋራ ፍላጎትና ጥቅም ያለበት ጉዳይ ስለሆነ ወጣት ተማሪዎች ደግሞ የነገ መሪዎች ስለሆኑ ይህንን ቢያውቁና እርስ በእርሳቸው ቢነጋገሩ መልካም ነው በሚል ነው ሴሚናሩ የተደረገው።

እንዲህ ሲባል ግን እኔ በናይል ጉዳይ ጀማሪ ነኝ ማለቴ እንዳልሆነ ልብ ይባልልኝ። በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉም ሆኑ ሌሎችም ከ1940ዎቹ ጀምሮ ያሰቡበትና የሰሩበት ብዙ ሰዎች አሉ። የእኔን ትንሽ ልዩ የሚያደርገው በዚህ ጉዳይ ባለፉት 42 ዓመታት ያህል ዓመታት በተከታታይ በየደረጃው እያደገ እንዲሄድ ከምርምር፣ ከማስተማርና ከማስፋት በኋላም ፖሊሲ በመደገፍ እንዲሁም ወደ ድርድርና አሁን ያለበት ደረጃ ለመድረስ አንዳች ክፍተት ሳይፈጠር እንዲሰራ መልካም ጥረት ማድረጌ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአራተኛ ዓመት ተማሪ እያሉ ነው ከዓባይ ወንዝ ጋር ተያያዥነት ያለው ጥናት ማድረግ የጀመሩት፤ ከገቡበት በኋላ እንዴት አገኙት?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡**- በጣም ተደስቻለሁ። ሳስተምርም፣ ስመራመርም ሆነ በድርድሩ ውስጥም እንዲሁም በዓለም አቀፍ ኮንፍረንሶች ላይ በአዘጋጅነትም ሆነ በተሳታፊነት ስንቀሳቀስ የምሰራው በጥልቅ የፍቅር ስሜት ነው። የዚህ መነሻ ምክንያት ደግሞ ይህ ትልቅ ብሔራዊ ሀብት ስለሆነ እና ይህን ሀብት ማንቀሳቀስ ለኢትዮጵያ ብልጽግና ትልቁ በር ከፋች ስለሆነ ነው። በተጨማሪም በውሃ ሀብታችን የመስኖም ሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨትና ሌሎቹን የልማት አጀንዳዎች በኤሌክትሪክ ኃይል በማካሄድ ከድህነት እንደምትወጣ ስለማምንም ነው። በኢኮኖሚው ብቻ ሳይሆን በፖለቲካው መድረክም ጎልታ እንድትታይ ስለሚያደርጋትም ነው።

ኢትዮጵያ የዓባይ ብቻ ሳይሆን በርካታ ወንዞች አሏት። እነዚህ ወንዞች ከኢትዮጵያ ሆድ ውስጥ የሚወጡ ንጥር የአካሏ ክፋይ ናቸው። እነዚህ ወንዞች ደግሞ ወደ 93 በመቶ ከአገር ውስጥ ወጥተው ወደጎረቤት አገር የሚሄዱ ናቸው። አባይን ብቻ ሳይሆን ዋቤ ሸበሌን፣ አኮቦን፣ ባሮን፣ ተከዜን፣ አሞን፣ ግቤን፣ ገናሌን እና ሌሎቹንም ማልማት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። በእነዚህ ወንዞች ልማት ጉዳይ ተማሪዎቻችንን ከስር ማሰልጠን የነገ መሪዎቻችንን እንደማሰልጠን ይቆጠራል። ዲፕሎማቶችንና ኤክስፐርቶችን ማሰልጠን ማለት ክርክራቸው በእውቀት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን እንደማድረግ ይቆጠራል።

አጠቃላይ የምሰራቸው ስራዎች፣ በመጣጥፍ መልክ የሚቀርቡ ጽሑፎችም ሆኑ በኮንፍረንሶች ላይ የማቀርባቸው ሁሉ በዚሁ መስመር የሚሄዱ ናቸው። ለዚህም ነው እኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርንም ሆነ የውሃ፣ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴርን ለረጅም ጊዜ በውሃ ድርድርና በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ፖሊሲ የማማከረው። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹን ጨምሮ ሌሎቻችን በአባይ ግድብ ላይ ያደረግናቸው ድርድሮች እውቀትና ብልሃት የተሞላበት አካሄድ ስለተከተሉ ውጤታማ መሆን ተችሏል እንጂ አፈሙዝ አሊያም ሻሙላ በመማዘዝ የተገኘ ስኬት የለም።

**አዲስ ዘመን፡- ቀድሞ የእርስዎ ተማሪዎች የነበሩ ዶክተር ያዕቆብ የአደባባይ ምሁር ናቸው ይላሉ፤ በዚህ ሃሳብ ምን አስተያየት አለዎት?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡**- እኔ በዚህ አይነት አባባል ራሴን አስቀምጬ አላውቅም። ነገር ግን ምንጊዜም የምሰራውን ለተማሪዎቼም ሆነ ለኢትዮጵያውያን አካፍላለሁ። ሌላው ደግሞ ይህ ጉዳይ ሃሳብ የማቅረብ ብቻ ሳይሆን ሃሳቡን እስከ ጫፍ ድረስ የመግፋትና የመመካከር አንዳንዴም ያ ሃሳብ እንዲጸናም ጭምር ስለሆነ ይህን የምሰራው በልበ ሙሉነት ነው። ስለዚህ በእርግጥ ከሱዳንና ከግብጽ አቻዎቼ ጋር አብረን እንጽፋለን፤ አብረን እናሳትማለን። የእነርሱም የእኛም ፍላጎት ሌላ መሆኑን አውቃለሁ፤ ነገር ግን ክርክራችን አንድ ላይ ስለሚሄድ ሶስተኛው አንባቢ በአንድ ላይ ያነበዋል። ፈራጁ ሶስተኛ ወገን ሊሆን ይችላል በሚል ከእነርሱ ጋር በልበሙሉነት ስንሰራ ቆይተናል። ስለዚህ እንዲህ ያሉ ሰዎች በዚህ አይነት መዝነውት ከሆነ መልካም ነው።

**አዲስ ዘመን፡-የእርስዎ ስም ከግድብ ድርድር ጋር በተያያዘ ስብዙዎች ቅርብ ነው፤ ግድቡ ደግሞ ሊጠናቀቅ የቀረው ከሃያ በመቶ በታች ሆኗል፤ ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያን የሚያሰጋ ነገር አለ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው፤ ምክንያቱም እንዲህም አድርገን ማሰብ አለብን፤ ሁልጊዜ የደረስንበትን ጉዳይ መጠየቅ አለብን። ከዚህ አንጻር ጥያቄው ጠቃሚ ነው። ከዚህ በኋላ የሚኖረው ተግዳሮት

**ወደ ገጽ 9 ዞሯል**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## «የዓባይ ግድብ...

ከመጣንበት አንጻር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ቀደም ሲል እኛ ሳንፈቅድላችሁ ግድቡን ልትሰሩት አትችሉም የሚል ነበር። ነገር ግን ግድቡ እናተን የማይጎዳ እኛን የሚጠቅም ግድብ ነው ስንላቸው ቆይተናል። ይሁንና ግድቡ ጥራት አይኖረውም፤ መሬቱም ልል ነው፤ የመሬት መንቀጥቀጥ ጸባይም ይኖረዋል እያሉ ሲያስወሩ ነበር። ነገር ግን የእኛ ምሁራን እነርሱ ያሏቸው ስጋቶች እንደሌሉ ሲያስረዷቸው ነበር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ግድቡን ለመስራት ልምድ የላችሁም ለሚሉት ደግሞ በግብጽ የተሰራው የአስዋን ግድብ የተሰራው በሶቪት ሕብረት ሰዎች ነው። በተመሳሳይ ሱዳን ውስጥም የተሰሩ ግድቦች በሌላ የሰው ኃይል የተሰሩ ናቸው። በኢትዮጵያ የተሰሩ ግን ኢትዮጵያ የሌሎችን ድጋፍ ጠይቃለች እንጂ ኢትዮጵያውያን በሚገባ ተሳትፈው የሰሯቸው ናቸው። ደግሞም ኢትዮጵያ ውስጥ ግድብ ሲሰራ የዓባይ ግድብ የመጀመሪያው ሳይሆን ብዙ ግድብ ተሰርቷል። አንዱም የመፍረስ አደጋ አላጋጠመውም በሚል በየአጋጣሚው እናስረዳቸዋለን።

ቀጥሎ የነበረው የገንዘብ ተግዳሮት ነበር፤ ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በከፍተኛ ሁኔታ ተሳትፈውበት እዚህ አድርሰውታል። ሌላው ደግሞ ግድቡን ለመሙላት ግብጽ አልፈቀደችም፤ ጦሯን ልትመዝ ትችላለች ሲባል ነበር። የመጀመሪያው ነገር ግብጽ ጦር ልትመዝ አትችልም፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ሉዓላዊት አገር ናት። በዲፕሎማሲውም በኩል ግብጾች ያመጡት ጫና አሜሪካዎችን፣ ምዕራባውያኑንና አረቦችን ደጋፊ አድርገው መነሳታቸው ነው፤ ይሁንና የግድቡ አሰራርም ሆነ ዲዛይኑ ግልጽ ስለሆነ እና የሚመለከታቸውም አካላት ስላዩት ግድቡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ ግድቦች ምንም ልዩነት የሌለው ተብሎ ተመስክሮለታል። ስለዚህም በዲፕሎማሲው በኩል ኢትዮጵያ ባቀረበችው ሰነድ በግልጽ ስለታየ በዚሁ ተቋጭቷል። ይህ ማለት በግድቡ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ላይ ተግዳሮት የተሞላበት ነበር ማለት ይቻላል።

ይሁንና ይህ ሁሉ ታልፎ ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሊት ስኬታማ ሆኖ ተጠናቋል፤ ሁለተኛው ተርባይንም ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ስለሆነም ከዚህ በኋላ የቴክኒክ ተግዳሮት የሚያጋጥም አይመስለኝም፤ ከፍተኛ የመንግሥትም ትኩረት ያለበት ነው። ሱዳንም ግብጽም ውሃ አንሷቸው አያውቅም። ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ የሚኖርባት ተግዳሮት ይህን ግድብ ከመጨረስ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ተጨማሪ ሌሎች የውሃ ሀብቶችን እንዴት አድርገን እናልማ እና እንዴት ከድህነት እንውጣ የሚለው ሊሆን ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- የዓባይ ግድብን ለማጠናቀቅ ጫፍ ላይ ተደርሷል፣ በዚህ ውስጥ በጥናቱም፣ በማማከሩም ሆነ በድርድሩ የእርስዎ ሚና ከፍ ያለ ነውና በዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎ የተደሰቱበት አሊያም ያዘኑበት ጊዜ ይኖር ይሆን?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ይህ በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው፤ እኔ የግድቡ የመጀመሪያውን፣ ሁለተኛውንና ሶስተኛውን ዙር የውሃ ሙሊቶች በተከታታይ ስኬታማ ሆኖ መጠናቀቁ በእጅጉ የተደሰትኩበት ጊዜ ነው። በምንም አይነት ሁኔታ ይህን ግድብ በጨለምተኝነት አይቼ አላውቅም። በተለይ ደግሞ የኃይል ማመንጫ በተኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተጭነው ኃይል እንዲያመነጭ ባደረጉበት ሰዓት ውስጤን የፈነቀለ ደስታ ተሰምቶኛል። በቦታው ሆኜም በአይኔ ያየሁት በመሆኑም ኩራት ተሰምቶኛል።

ያዘንኩበት ነገር ቢኖር ግድቡ ከአሁን በፊት ማለቅ ሲገባው ግድቡ ላይ ኃላፊነት፣ ገንዘብና ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ከቦርድ ሊቀመንበርነት እስከታች ድረስ የነበሩ ግድቡን እየሰራን ነው፣ የውሃ ሙሊቱን በዚህ ዓመት እንጀምራለን እያሉ እያታለሉ መቆየታቸው ነው፤ በተለይ የግድቡን ስራ ከስር እየገዘገዙ በመጨረሻም ግድቡ ሊወድቅ አፋፍ ላይ በደረሰበት ጊዜ በጣም ትልቅ ኀዘን ተሰምቶኝ ነበር። እንደዛ ሆኖ ቢቀር ኖሮ በጣም እንዳዘንኩ እቀር ነበር። ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ክፉ ነገር ተሸንፏል፤ ክፉ የሰሩ ሰዎችም በተለያየ መንገድ ታርመዋል። ግድቡ ረጅም ጊዜ ቢወስድም የተቀመጠለትን ኢላማ ስለመታም የአሁን ደረጃው ላይ ደርሷል። በመሆኑ ኀዘኔም ተስተካክሏል።

**አዲስ ዘመን፡- በአሜሪካ፣ በምዕራባውያኑም ሆነ በአረብ አገራት በኢትዮጵያ ላይ ሲደረግ ከነበረው ጫና መካከል ልብዎን ያሳዘነ ይኖር ይሆን?**



**ዶክተር ያዕቆብ፡-** በእርግጥ ከፈረንጆቹ ጥሩ ነገር ጠብቄ አላውቅም፤ እነሱ የሚያስቡት ኢትዮጵያን በሌላ በምን አይነት ጥቅም እንለውጣት በሚል ነው እንጂ ታላቅነቷንና የሥልጣኔ ምንጭ የሆነች አገር መሆኗን አይደለም። ግብጽን መደገፋቸው ደግሞ ምንም አያስደንቀኝም። ምክንያቱም የግድቡን ዲፕሎማሲ የሚያሸንፈው በኢትዮጵያ በኩል ቁርጠኝነት ተይዞ ግድቡን ትክክለኛ እውቀት ላይ በመመስረት ሰርቶ መጨረስና ስራ ላይ ማዋል ነው።

ቀደም ሲልም ማን ወዳጅ ማን ጠላት የሚለው ጉዳይ በዓድዋም ሆነ በማይጨው ጊዜ የነበረ ነው። ስለዚህም ከፉ ቀን ሲያጋጥመን የሚያጋጥሙን ወዳጆች አሉ። ይህ ግን በእኛ ጥንካሬና በምናሳየው ትጋት እና ቁመና የተለካ እንጂ በመልካችንና በቁመታችን ስለወደዱን አይደለም።

አሜሪካም ሆነች ምዕራባውያኑ ምኞታቸው ኢትዮጵያን አንካሳ ማድረግ ነበር። በተለይ የግብጽ ፍላጎት እንዲናኝና ራሳችንን የሚጎዳን ጉዳይ በገዛ ፈቃዳችን እንድንፈርም አድርገው አዘጋጅተው ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ተደራዳሪዎችና የኢትዮጵያ መንግሥት ልዩ ድጋፍ ታክሎበት ጫና ያለበት ዲፕሎማሲ ከሽፎ ዛሬ ላይ ተደርሷል። በዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት መኩራት ያለብን ይመስለኛል። ምክንያቱም ይህ የተሰራው በአርበኝነትና በትጋት እንጂ በቅጥረኛ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡-ኢትዮጵያ ግድቡን ከጀመረች ጀምሮ የተለያዩ ጫናዎች ከመኖራቸው በተጨማሪ ተደጋጋሚ ጦርነት ደግሞ ከሕወሓት በኩል ሲነሳ ተስተውሏል፤ ስለዚህም እርስ በእርስ መባላት ምክንያቱ ምንድን ነው ይላሉ?መፍትሔውስ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-**ይህ ጥያቄ በራሱ ብዙ የሚያነጋግርና ሰፊ የሆነ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የፖለቲካ ድርጅቶችን ጨምሮ ብዙዎች በተለያየ መንገድ ሃሳብ ይሰጡበታል። ስለዚህ በመጀመሪያ ማየት ያለብን ኢትዮጵያን ነው። ኢትዮጵያ በቅርብ የተፈጠረች አገር አይደለችም። ለረጅም ዘመን ስትገነባ የመጣች አገር ናት። ሕዝቧም በፍጹም የተዛመደና የተጋመደ ነው። በውስጥ የአንድነትና የሕብርነት መንፈስ የተላበሰ ሕዝብ ነው። አደጋ በአገርህ ላይ ደረሰ ሲባል ደግሞ መሪውን እንኳን ማን እንደሆነ በቅጡ የማያውቅ ሁሉ በነቂስ ወጥቶ የሚሰለፍ ነው።

ገዢ አገሮች ሌሎች አገሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው በማስመሪያ እያሰመሩ ሲቀራጩ ኢትዮጵያ ግን አልተነካችም። ይህ በመሆኑም ኢትዮጵያ ከማን በልጣ ነው በሚል ብዙ ጦርነት ተካሂዶባታል። ነገር ግን አሸናፊ ነበረች። ያሸነፈችው ደግሞ ንጉሡና አዛዦቹ ብቻ ስለተዋጉ አይደለም። መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለተጋደለም ጭምር ነው። ገሚሱ ጦረኛ፣ ግማሹ ደጀን፣ ሌላውም ደጎም በጾም ጸሎቱም ጭምር ስለተባበረ ነው ኢትዮጵያን ከገዢዎች ማስመለጥ የተቻለው። ጣሊያን በአምስት ዓመት ውስጥ አገሪቱን በቅጡ እንኳ ሳያዳርስ ተባርሮ መውጣት የተገደደው በነበረው ትብብር ነው። የኢትዮጵያውያን ልብ ጠላት የማሸነፍና አገርን የማዳን መንፈስ የተሞላ ነው። ስለዚህም ነው የዓድዋ ድል በዓለም ላይ አንጸባራቂ ድል መሆን የቻለው። አሁንም ቢሆን በዚህ ጉዳይ ገድላችን ተጽፎ አላለቀም ። በዚህ ጦርነት የተጋደሉ ጀግኖች ሁሉም ታውቀዋል ብዬ አላስብም። ይህ አይነት ልበ ሙሉነት በሶማሊያም ሆነ በባድመ ጦርነት የአንድነት መንፈስ በእጅጉ የታየበት ነው።

እንዲህ አይነት አገር በየቦታው በብሔረሰብ ስም ቢጠራ፣ የተለያየ አይነት ቋንቋ ቢናገር በዚህ ነው መተዳደር ያለበት በሚል ሲኬድበት ቆይቷል። ኢትዮጵያ በቢላዋ ተቆርጣ የጎሳ አገር ተድርጋና የጎሳ ሕግ ወጥቶ፣ የጎሳ አደረጃጀት ተፈጥሮ፣ የጎሳ አለቃ ተበጅቶ፣ የጎሳ ሚሊሻ ተዋቅሮ በአጠቃላይ በጎሳ ሰው ተከልሎና በሕገ መንግሥት ተቀርጾ ይህን ነገር ለማስተዳደር የተደረገበት ሙከራ አንደኛ አገር የሚያጠፋ፣ የሚያዳክም ነው። በአንድነቱ ከሚኮራበት እሴቱ የሚነጥልና ከሕብረቱ የሚያስተጓጉል ብሎም ሃሳቡ በግድ የተጫነበት በመሆኑ ይህ አደረጃጀት ውሎ አድሮ ዛሬ ላለንበት ግጭት ዳርጎናልና ይህ በጣም አሳዛኝ ነው።

ኢሕአዴግ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እኛ እስከምናውቀው ድረስ የጎሳ ግጭት አንድም ጊዜ በርዶ አያውቅም። ወይ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል፣ ደቡብ፣ ሶማሌ ወይ ደግሞ ሌላው ቦታ ሲከሰት የቆየ ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ ሰነዶች አሉ። አሁን ያለንበት ጦርነት ቁስሉ አመርቅዞ ካንሰር ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያሳይ ነው። አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ወረራ የሚባለው እና አልፎ ተርፎ የአገርን ሉዓላዊነት ሌት ተቀን የሚጠብቅ የአገር መከላከያ ሁሉ የተወጋበት ምክንያት በጎሳ አደረጃጀት ነው። የጎሳ አደረጃጀቱም ቢሆን ለአንተ ለጎሳ መሪው ትቼልሃለሁ የሚባል ሳይሆን በጎሳ ተደራጅና እኔ ከላይ ሆኜ እመራሃለሁ በሚል የተደረገ ነው። በጎሳ መሰረት የሕግ ረቂቅ ተበጅቶና ጸድቆ አገር ሰላሟ ይጠበቃል ማለት አያስደፍርም።

መፍቻው እዚህም እዚያም የሚሰማውን ግጭት አሊያም የሚነሳውን ጦርነት ማስተካከል ሳይሆን መሰረታዊ የሆነ የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ መንፈስን ማምጣት ነው። ኢትዮጵያዊ የትም ቦታ ቢሆን ኢትዮጵያዊ መሆኑን ኢትዮጵያ ደግሞ ትልቅ አገር መሆኗን የሁሉም ሰው ትልቅነት መገለጫ ስለሆነ ኢትዮጵያን ወደቀድሞ አንድነቷ ማምጣትና መልሶ በዚህ መንፈስ መገንባት ተገቢ ይመስለኛል። የኢትዮጵያን ሕብርነት ማምጣት መፍትሔው ነው እላለሁ። ይህ የሕግ የበላይነትም ጥያቄ ነው። ኢትዮጵያ የኤ፣ቢ፣ሲ ወይ የዲ አገር ብቻ ሳትሆን የሕብረተሰብ አገር ናት። ይህ እንዳይሆን ሸብበው የያዙ በጎሳ የተመሰረተ ሕግጋቶችና አሰራሮች መሻር አለባቸው። ሕገ መንግሥቱን ጨምሮ መለወጥ መቻል አለባቸው። ሕገ መንግሥቱ ኢትዮጵያን የማፍረስ ባህሪ ያለው ነው። ስለዚህም ለዘመናት የተጋመዱ ኢትዮጵያውያን መፍረስ የለባቸውም። ሰው ከሰላሙ፣ ከከፍታው፣ ከክብሩ መውረድ ለምን ያስፈልገዋል። በተለይ በሕገ መንግሥት ኮሚሽን በነበረው ትልቅ ውይይት እኔም የተሳተፍኩበት ሲሆን፣ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በ1986 ዓ.ም ታህሳስ 21 እና 22 ባወጣው እትሙ የእኔ ሃሳብ ከአንዴም ሁለቴ ተካቷል። ያኔም ቢሆን ሕገ መንግሥት ተቀባይነት ያልነበረው ሲሆን፣ እስከዛሬ ድረስ ዘልቋል። ስለዚህም ይህ ሕገ መንግሥት የግጭት እርሾ ሆኖ ቆየ እንጂ የሰላምና የሕብረት ምክንያት መሆን አልቻለም። በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ ፍላጎት የሚያንጸባርቅ አልነበረም። ለወደፊቱም ቢሆን ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥቴ ነው ብላ የምትይዘው ሕገ መንግሥት ኢትዮጵያን የሚወክል ሕገ መንግሥት እንጂ እነ እገሌንና እገሊትን የሚወክል ብቻ መሆን የለበትም።

**አዲስ ዘመን፡-እርስዎ እንዳሉት ሕገ መንግሥቱ በመከፋፈሉ ረገድ ሚናው የጎላ ቢሆንም ታላቁ የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያውያን አንድ ከማድረግ አኳያ ምን ያህል ርቀት ሄዷል ብለው ያስባሉ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ከረጅሙ በአጭሩ ይህንን ግድብ አጋዴን ያለው ሰው ወይም በደቡብ ኢትዮጵያ ጫፍ ላይ ያለው ዳሰነች አሊያም ኛጋቶም ያለው ሰው ወይም ደግሞ ጋምቤላ ኢታንግና አቦቦ ያለው ሰው እንዲሁም ወደምስራቅ ኢትዮጵያ ያለውና መሃል አገር የሚኖረው ሰው ሁሉ ደግፎታል። የደገፈበት ምክንያት ደግሞ ግድቡ የሚያመጣለትን የኤሌክትሪክ ኃይል ወይም ደግሞ ሌላ ነገር አስቦ አይደለም። የኢትዮጵያ መንግሥት በዚህ ውሃ ላይ ግድብ ገድቦ ለኢትዮጵያ ጥቅም ለማዋል ሲፈልግ ይህን አታደርግም የሚል ጠላት ስላለ ይህንን መመከት አለብን ከሚል የተነሳ ነው።

ቀደም ሲል የነበረው ቅኝ ግዛት እንዲሁም የውጭ ወረራና ተጽዕኖ እንደተመከተ ሁሉ ይህንንም መመከት አለብን በሚል ስሜት ይመስለኛል በአንድነት የመደገፋቸው ምስጢር። እንደ እኔ በውስጡ የኢትዮጵያዊ አርበኝነት ያለበት ይመስለኛል። ይህ ደግሞ ለእኔ ትልቅ ትርጉም አለው። በእርግጥ ልማቱ ሲመጣ አልጠቀምም ብሎ አያስብም ማለት ሳይሆን ትልቁ ነገር ግን አርበኝነቱ ነው። የአባይ ግድቡ ቀድሞ የነበረውን የኢትዮጵያውያንን አንድነት የመለሰ ነው ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣይ እቅድዎ ምንድን ነው? አያይዘውም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካልዎት እድሉን ልስጥዎት?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ኢትዮጵያ በህዳሴ ግድቡ ትልቅ ተሞክሮ ስላካበተች በቴክኒኩም፣ በዲፕሎማሲውም ሆነ በጂኦፖለቲካው ተጽዕኖ በመቋቋም ትልቅ ተሞክሮ አሳይታለች፤ ይህም ኢትዮጵያውያኑን ያኮራና ውጤቱም ያማረ ሆኗል። ጎረቤቶቻችንም እየተቀየሙን አስቸገሩን እንጂ ለእነርሱም በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። ይህ ተሞክሮ ውጤት ያገኘ በመሆኑ በቀጣይም እሱ ላይ አስፍቼ እሰራለሁ የሚል እቅድ አለኝ። ግድብ የልማት ስራ ነው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ወንዞች አሉና የመላ ኢትዮጵያውያ ስለሆኑ ወንዞቻችንን መንከባከብ አለብን፤ አረንጓዴ አሻራም ቀጣይነት ያለው እንዲሆን እሻለሁ። ልምዱም በአጼ ኃይለስላሴ ጀምሮ ያለ ቢሆንም ጉድለት በማሳየቱ በዚህ ደረጃ አልታየም ነበር። የአሁኑ ግን በእጽዋት ምርጫም ሆነ በእንክብካቤ ደረጃ ከፍ ብሎ የታየ ነው ማለት ይቻላል። ይህ ከተፈጥሮ ጋር ያለን ቁርኝት ከፍ ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ሌላው ኢትዮጵያ ውስጥ እንደካንሰር አንድነታችንን እየቦረቦረ ያለው ጎሰኝነት ስለሆነ ይህም ቀድሞ ሲገዙ በነበሩ ሰዎች የተተከለ ብዙዎቹን የሚጎዳ ጥቂቶችን ደግሞ ለጊዜው የሚጠቅም የሚመስል ነው። ነገር ግን ለዘለቄታው የማይጠቅም በመሆኑ በአጠቃላይ ይህ እንደ ስህተት ተቆጥሮ ከታረመ ኢትዮጵያውያን እርስ በእርሳቸው ያላቸው ቁርኝትና የአገር አርበኝነት እንዲሁም የልማትና የህብር ጥምረት እንደገና እንዲገነባ ይረዳል። ኢትዮጵያውያኑም እንዲህ ማሰብ ይጠበቅባቸዋል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ተናጋሪው ዶሴ

# “የፍቅር ጥያቄዬን አልተቀበልሽኝም” በሚል አሲድ የተደፋባት ወጣት

**አስመረት ብስራት**



**ያች የውበት መለኪያ የሆነች ውብ የገጠር ወጣት ከስራ ስትመለስ የፍቅር ጥያቄዬን መቀበል አለብሽ ያላት ሰው መንገድ ላይ ጠብቆ አሲድ በፊቷና በራሷ ላይ ደፋባት። ቃጠሎውን መቋቋም የከበዳት ያች ወጣት እየጮሄች ብትጠርገውም ሰውነትዋ ከመበጣጠስ ያለፈ ቃጠሎው ሊታገስላት አልቻለም**

በለምለሙ የገጠር ቀበሌ ነው ተወልዳ ያደገችው። ይህ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ የሆነችው ወጣት ለቤቱ ሶስተኛና ብቸኛ ሴት ልጅ ናት። ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ልጅ ያገኙት እናቷ የረሀቤ መድሃኒት ሲሉ የራብ ብለው ስም አውጡላት። የራብ ብርሃኔ እንደ አካባቢው ልጆች ከብት ስታግድ ወላጆቿን ስትደግፍ አደገች። ይች ልጅ ስምን መልአክ ያወጣዋል ይሉት ነገር ሆኖ እውነትም እንደ ስሟ ለእናት ለአባቷ ደጋፊ ሁነኛ ልጃቸው ሆነች። ሴት ልጅ ተርበውና ተጠምተው አምላካቸውን ሲማጸኑ ያገኟት  የአይናቸው ብቻ ሳትሆን የድካማቸው ማረፊያ አገልጋያቸው ሆና ነው የተፈጠረችው።

በአጋጣሚ እድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ በተወለደችበት አካባቢ በቅርበት አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ይከፈታል። ትምህርት ቤቱ የወላጆቿ ቤት አቅራቢያ በመሆኑና በፈረቃ ትምህርት ግማሽ ቀን ብቻ ስለምትማር “ቶሎ መለስ ብላ ትረዳናለች” በማለት ወላጆቿ ያለምንም ማንገራገር ትምህርት ቤት እንድትገባ ይፈቅዱላታል።

የራብ በልጅነቷ ንቅት ያለች ቀልጣፋ ልጅ ስለነበረች ትምህርቱን ለመያዝ ብዙም አልተቸገረችም ነበር። አስተማሪዎቿ የሚናገሩትን አዳምጣ ወዲያው የምትረዳ የቀለም ቀንድ የሆነች ጎበዝ ልጅ ወጣት። ከትምህርት ቤት መልስም ወላጆቿን አስከፍታ ከትምህርት እንዳያስቀሯት በማሰብ ቀደም ትሰራው ከነበረው በላይ ጨምራ በመስራት ታስደስታቸው ጀመር።

አመት አመትን እየወለደ የራብም ከልጅነት ወደ ኮረዳነት እድሜ ተሸጋገረች። ከዛም ባለፈ አካባቢያቸው የሚገኘው ትምህርት ቤት እስከ ስምንተኛ ክፍል ብቻ የሚያስተምር ስለነበረ ትምህርቷ እዚህ ላይ ሊቋጭ ይሆን በሚል ስጋት ተወጠረች። የስምንተኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተናን ከወሰደች በኋላ በጣም ከምትወደው ትምህርቷ የመቅረቷ ነገር ያሳሰባት ይች ልጅ ለማንም ሳትተነፍስ በውስጧ መብሰልሰል ጀመረች።

የልጃቸውን መጨነቅ ያስተዋሉት አባቷ ምን እንደሆነች ሲጠይቋት ትምህርቷን የመቀጠል ፍላጎት እንዳላትና ትምህርት ቤቱ እስከ ስምንተኛ ክፍል ብቻ መሆኑ እንዳሳሰባት ታስረዳቸዋለች። አባቷም “እስኪ ቅድሚያ ውጤቱ ይምጣና እንማከራለን” በማለት ያልፉታል። ለአፋቸው ይሄንን ይበሉ እንጂ ጎበዟ ልጃቸው ዝቅተኛ ውጤት እንደማታመጣ ልባቸው ያውቀዋል።

ለእሷ ይሄንን ካሉ በኋላ በአቅራቢያቸው ያለ የገጠር ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስለመኖሩና በምን መልኩ መማር እንደምትችል ሲያስቡና ሲያስተካክሉ ቆዩ። የራብም በለስ ቀንቷት በከፍተኛ ውጤት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገባች። ቤት ተከራይተውላት ስንቅ ቋጥረው የላኳት ብቸኛ ሴት ልጃቸው ተምራ እንደምታኮራቸው ያመኑት አባቷ ምንም የማጀቱ አድማቂ ብትሆን እንኳን ከምትወደው ትምህርቷ ሊነጥሏት አልፈለጉም ነበር።

የአባቷና የእናቷ ተስፋ የሆነችው ወጣት ውጤታማ በመሆን በፋርማሲስትነት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ያዘች። ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት በራቀቻቸው ወቅት የነበረውን ናፍቆት የተረዳችው ወጣት ቤተሰቦቿ ከሚኖሩባት የገጠር ቀበሌ አጎራባች በሆነችው በሁለት እጁ ነሴ ወረዳ ቀራንዮ በተባለች አነስተኛ የገጠር ከተማ በአንድ ግለሰብ መድኃኒት ቤት ተቀጥራ ትሰራ ጀመር።

ስራ በማይኖራት ቀን በአገኘቻት ብር የሚያስፈልጋቸውን በሙሉ ቁጥርጥር አድርጋ በመሄድ እናት አባቷን ጠያቂ ወንድሞቿን ደጋፊ አስተማሪ የሆነች ጠንካራ ወጣት ሆነች። በቤተሰቧ ተወዳጅ የሆነችው ይች ወጣት የቤተሰቧ ፍቅር በልጦባት ትዳር ፍቅረኛ ስለሚባል ነገር ጨርሶም አስባ አታውቅም ነበር።

በልስላሴ ድፍት ከሚለው ሃር ከመሰለው ዘንፋላ ፀጉሯ አንስቶ ጥርት ያለው ውብ ጠይም የቆዳ ቀለሟ፤ የተኳሉ የሚመስሉት አይኖቿ፤ እንደ ፀበል ኩስኩስት ቀጥ ብሎ የወረደው ውብ አፍንጫዋ፤ ሞላ ያሉት ከንፈሮቿ በአጠቃላይ አብ ሳላት የተባለላት አይነት ውብ ሴት ናት።

ይች ውብ የጤና ባለሙያ ብቻዋን ገባ ወጣ ማለቷን በአይነቁረኛ የሚከታተሉ ጎረምሶች በረከቱ። አይናቸውን ከመጣል በሻገር ደፈር ብለው የፍቅር ጥያቄ ያቀረቡላትም አልታጡም። የራብ ግን ልቧ የገባ ሰው ትጣ ወይም የወላጆቿ ፍቅር ሁለመናዋን ተቆጣጥሮት ባይታወቅም ስሜቷ ማንንም በፍቅር አይን ለመመልከት አላስቻላትም ነበር።

የእንቢታ መልሷን የሰጠቻቸው ሰዎች በሙሉ መልሱን በፀጋ ተቀብለው ቢመለሱም ከአፍቃሪዎቿ መካከል አንዱ የፍቅር ጥያቄውን ያለመቀበሏን በንቀት ቆጥሮት በልቡ ቂምን አዝሎ መውጫ መግቢያዋን ይቆጣጠራት ገባ። ሁልጊዜ መከታተሉ ምቾት ያልሰጣት ወጣት ይረሳኝ ይሆናል በማለት የአመት ፈቃዷን ወስዳ ቤተሰቦቿ ጋር ሰነባብታ ተመለሰች።

ይሁንና ጭራሽ ከአይኑ መጥፋቷ ያሳበደው አፈቀርኩ ባይ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ወደ ስራ ገበታዋ የምትመለስበትን ቀን ይጠባበቅ ጀመር። መድረሱ አይቀርም የእረፍቷ ቀኗ አብቅቶ ወደ ስራ ገበታዋ ተመለሰች። ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ሆዷን ባር ባር እያለው የተለየቻቸው ቤተሰቦቿን ተመልሳ የማታያቸው ያህል እንባ እየተናነቃት ነበር ከተወለደችበት ቤት የወጣችው።

ወደ ስራ ገበታዋ በተመለሰች በሶስተኛው ቀን ከየት መጣ ሳትለው አፈቀርኩሽ የሚላት ሰው እጇን ለቀም አድርጎ ያዘ። አይኑን አጉረጥርጦ ለምን ሳትነግረው እንደሄደች በጩኸት ጠየቃት። ‹‹የሚሄድበትን ሁሉ ላንተ የማሳወቅ ግዴታ የለብኝም›› አለች ፈርጠም ብላ። “አንቺ የእኔ ካልሆንሽ የማንም መሆን አትችይም እሰራልሻለሁ” በማለት ጥርሱን ነክሶ የቅናት ክብሪቱን በራሱ ላይ ለኩሶ  በውስጡ እያንቦገቦገ  ተለያት።

ታኅሣሥ 18 ቀን 2014 ዓ.ም እንደተለመደው በጠዋት ከቤቷ ወጥታ ቤተክርስቲያን ተሳልማ ወደ ስራዋ ሄደች። ያለወትሮዋ ቅፍፍ በሚል እንቅልፍ እንቅልፍ በሚል  ስሜት ውስጥ  ነበር የዋለችው። ድብርቷን ያስለቅቅላት ይመስል ደጋግማ ቡና ስትጠጣ የነበረችው ወጣት ምንም ቀለል ያለ ስሜት አልሰማት ሲል ቤት ሄጄ ልረፍ በማለት ከቀኑ 11 ሰዓት አካባቢ ከሥራ ወጣች።

ያች የውበት መለኪያ የሆነች ውብ የገጠር ወጣት ከስራ ስትመለስ የፍቅር ጥያቄዬን መቀበል አለብሽ ያላት ሰው መንገድ ላይ ጠብቆ አሲድ በፊቷና በራሷ ላይ ደፈባት። ቃጠሎውን መቋቋም የከበዳት ያች ወጣት እየጮሄች ብትጠርገውም ሰውነትዋ  ከመበጣጠስ ያለፈ ቃጠሎው ሊታገስላት አልቻለም።

ሰውነቷ ላይ በተደፋው አሲድ በፊቷ፣ በግማሽ እራሷና በአንድ ጡቷ ላይ ከፍተኛ አካላዊ ጉዳት ያደረሰባት ሲሆን ተሰምቷት የማያውቅ አይነት ሰቃይ ውስጥ እንደከተታት ትናገራለች። ወጣቷ ስትጮህ በአካባቢው በርካታ ሰዎች ቢሰበሰቡም እላይዋ ላይ ውሃ ከመድፋት የዘለለ እርዳታ ስላላደረጉላት ጉዳቱ ከፍተኛ ሊሆን ችሏል።

ጉዳቱን ያደረሰው ግለሰብ ወዲያውኑ ከአካባቢው ለመሰወር ሙከራ ቢያደርግም በህብረተሰቡ ርብርብ ሊያዝ መቻሉን ያስታወቀው ፖሊስ ግለሰቡ የፍቅር ጥያቄዬን አልተቀበልሽኝም በሚል የተናቅኩ ስሜት ተነሳስቶ እንዲህ አይነት የከፋ ጉዳት እንዳደረሰባት በማስረጃ መረጋገጡን ጠቅሰዋል።

በምስራቅ ጎጃም ዞን የሁለት እጁ ነሴ ወረዳ ፖሊስ የተፈፀመው የአካል ማጉደል ወንጀል ላይ የዓይን ምስክሮችን፤ የህክምና ማስረጃን በማካተት የሰነድ ማስረጃ ለወረዳው አቃቤ ህግ በማቅረብ ክስ መስርቶ ጉዳዩን ሲከታተል ቆይቷል።

## ፍቅር ናፋቂው ወንጀለኛ

ደብረታቦር አካባቢ በምትገኝ የገጠር ቀበሌ ነበር የተወለደው። ወላጅ እናቱ በልጅነቷ በመዷራና ሰውነቷ  ሳይጠና በማርገዟ የተነሳ እሱን እንደወለደች ነበር ሕይወቷ ያለፈው። ወላጅ አባቱ ብዙም ሳይቆይ በማግባቱ እንጀራ እናቱ ታሳድገው ጀመር። አባቱ የመጀመሪያ ሚስቱን በጣም ያፈቅራት ስለነበር ልጁ የገደላት ያህል አምርሮ ይጠላው ነበር። ሲወጣ ሲገባ “አንተ ገፊ” በማለት ነበር የሚጠራው።

በእናት ፍቅር  እንክብካቤ ሳያገኝ በጥላቻ በተሞሉ ሰዎች መካከል ያደገው ይህ ልጅ ከፍ ብሎ እግር እንዳወጣ ነበር ወደ ምስራቅ ጎጃም ዞን የሁለት እጁ ነሴ ወረዳ የመጣው። በዛም ያገኘውን እየሰራ በትርፍ ጊዜው እየተማረ እራሱን ሲያሳድግ ኖረ።

ቤታቸው ተከራይቶ ይኖርባቸው የነበሩ ልጅ ያልነበራቸው ሴትም ልክ እንደ ልጃቸው እያዩት እሱም ያጣውን የቤተሰብ ፍቅር ያለስስት የሰጡትን ሴት እየደገፈ በቤተሰብነት ይኖሩ ጀመር።

አንድ ቀን ያየውን ማመን እስከሚያቀተው ድረስ ምትሃት የሆነ ውበት ከፊት ለፊቱ ሲመጣ ይመለከታል። በጣም የምታምር ቆንጆ ወጣት በተረጋጋ እርምጃ ከፊቱ መጥታ አጠገቡ ደርሳ እስከታልፍ ደረስ አፉን ከፍቶ እየተመለከታት ነበር።

እንዲህ ፍቅር ዳሶት የማያወቀውን ከራሱ ሌላ ምንም የኔ የሚለው የሌለውን ሰው ልብ ወከክ ያደረገችውን ልጅ ሲፈራ ሲቸር ቆይቶ የፍቅር ጥያቄውን አቀረበላት። እሷም እንደማይሆን ግልፅ  በሆነ አማርኛ ነግራው ወደ ቤቷ ሄደች።

ያን ቀን ነው እንግዲህ ልቡ ውስጥ ተሸሽጎ  የኖረው ፍቅር የማጣት የመጠላት ስሜት ቀንድ አውጥቶ የእጅና የእግር ጥፍሩን አሹሎ ከወደ ልቡ ስር የወጣው። ያለመፈለግ ስሜቱ አድጎና ጎልብቶ የማይፈልጉትን የማይወዱትን ሊያጠፋ ተነሳ። ይህ ክፉ ስሜት ውቧ የራብ ላይ እጁን እንዲያነሳ አደረገው። ያችን ታይታ የማትጠገብ ወጣት ግማሽ  ፊቷንና ግማሽ አካሏን በአሰቃቂ ሁኔታ  አሳጣት። በዚህ ስራውም ፍትህ ሊጠይቀው ከህግ ፊት መቆም ግድ ሆነ።

## ውሳኔ

ዓቃቤ ህግ ያቀረበውን ክስ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት ማስረጃና መረጃዎችን ሲመረምር ቆይቶ በተከሳሹ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ለማሳለፍ በቀነ ቀጠሮ ተገኝቷል። “ግለሰቡ ወንጀሉን ሆን ብሎና አቅዶ ጭካኔ በተሞላበት መንገድ የፈፀመው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት በወንጀል ማክበጃነት ይዟል” ብለዋል።

ተከሳሹ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነኝ፣ ከዚህ በፊት የወንጀል ሪከርድ የለብኝም በሚል ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ ከፈፀመው ወንጀል አንጻር ያቀረበውን የፍርድ ማቅለያ ሳይቀበለው ቀርቷል።

የወረዳው ፍርድ ቤት በዋለው ችሎት ሌላውንም ህብረተሰብ ያስተምራል፤ ጥፋተኛውንም እንዲጸጸት ያደርጋል በሚል  በፈጸመው ወንጀል ግለሰቡን በ14 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ  ወስኗል። ወንጀለኛ በጥፋቱ የተወሰነበትን ቅጣት መቀጣቱ ግድ ነውና አከራረሙን ማረሚያ ቤት አደረገ።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ከሳይንስም ከአመክንዮም የተጣላው አንድነትን ጠል የትሕነግ ትርክት

ይበል ካሳ

ታሪክ ሰዎች በተግባር አድርገውትና ሆነውት ያለፉት እውነተኛ የሥራ መዝገብ እንጂ በመለኮት ፈቃድ የሚፈጠር ተዓምር አይደለም፡፡ ታሪክ የፈለጉትን ማድረግና መሆን እንደሚቻል ሰዎች በተግባር ሞክረው ያረጋገጡበት፣ ዛሬን ከትናንት እና ከወደፊቱ ጋር የሚያገናኝ ድልድይ ነው። ትውልድ ሥራ የሚማርበትና የሚለማመድበት ህያው የድርጊት ቤተ ሙከራ ነው እንጂ በሃሳብ ብቻ የቀረ ወይም በቢሆን ምኞት የሚፈጠር በእውነተኛው ዓለም በገሃድ ያልተፈጸመ ልብ-ወለዳዊ ፈጠራ አይደለም፡፡ እናም ታሪክ ዛሬን ከትናንትናና ከወደፊቱ ጋር የሚያገናኝ፣ የአሁኑና መጪው ትውልድ መሆንና ማድረግ እንደሚቻል በወሬ ሳይሆን በድርጊት የሚማርበት ህያው የድርጊት ቤተ ሙከራ ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት ራሳችንን ስንመረምር የረጅም ዘመን የነጻነት፣ የአሸናፊነትና የጀግንነት የሚያኮራና ደስ የሚያሰኝ ታሪክ ያለን ሕዝብና ሀገር መሆናችንን እንገነዘባለን፡፡ ከጥንት ከቅድመ ዓለም ጀምሮ እስከ የቅርብ ዘመኖቹ ዓድዋና የፋሽስት ወረራ ለሦስት ሺ ዓመታት በኢትዮጵያ ነጻነት ላይ ደጋግማ በዘመተችው ጣሊያን፣ አስራ ስድስት ጊዜ ሞክራ አስራ ስድስት ጊዜ በተሸነፈችው ታሪካዊ ጠላታችን ግብጽ፣ በዚያድባሬዋ ሶማሊያም ሆነ ክብራችንንና ነጻነታችን ለመድፈር በሞከሩ ማናቸውም እብሪተኛ ኃይሎች በታሪካችን ተሸንፈን የማናውቅ መሆናችንም ለዚህ ሕያው ምስክር ነው፡፡

የአሸናፊነታችንና የድላችን ሁሉ ሚስጥር ደግሞ አንድነታችን ነው፡፡ እጅግ የቅርቡንና በዓለም ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የሰው ልጅ ፍጡር ዘንድ እንድንከበርና እንድንኮራ ያደረገንን አንዱንና ዋነኛውን የነጻነትና የክብር ታሪካችን በማሳያነት በማንሳት ልጀምር፡፡ እብሪተኞች እንደ ሰው የማይቆጥሩት የጥቁር ሕዝብ "ምንጊዜም የበላይ ነን" ብሎ የሚያምነውን የነጭ ወራሪ በጦር ሜዳ ገጥሞን ለመጀመሪያ ጊዜ ያሸነፍን እናም ለጥቁር ሕዝብ ሁሉ ኩራት የሆነውን ከዚያም አልፎ ለመላው ሰው ልጆች ሁሉ የሰውነት ክብርን ያጎናጸፈውን አኩሪ ታሪክ የሠራነው በአንድነታችን ነው፡፡ ይህም አንድነታችን ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችንና ለመላው የሰው ዘር በሙሉ፣ ከራሳቸው ከነጭ ዘር የተገኙ ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ ለነጻነታቸው እንዲታገሉ ምክንያት፣ ድል አመላካች፣ የአሸናፊነት ምልክት እንድንሆን አድርጎናል፡፡

ይሁን እንጂ የትንሽነትና ታህተ ሰብዓዊነት፣ የአጥንት ቆጠራና የኢምክንያታዊና ግዑዛዊ መንገኘነት ፖለቲካ መስራችና አቀንቃኝ የሆኑት እንደ ትሕነግና እነሱን የመሳሰሉ አላዋቂዎች ሁለቱንም፤ ታሪክንም አንድነትንም የሚጠሉና ከመጥላትም አልፈው የሚያጥላሉ መሆናቸውን ባለፉት ዓመታት በስፋት ስንሰማው የኖርነውና ዛሬም ድረስ የምንታዘበው ሃቅ ነው፡፡ ትሕነጋውያን ሰዎች የፈለጉትን ማድረግና መሆን እንደሚችሉ የሚማሩበትንና በተግባርም መሆናቸውንና መቻላቸውን የሚያረጋግጡበትን ታላቁን የዕውቀትና የሥነ ልቦና ትምህርት ቤት የሆነውን ታሪክን "ተራ ተረት ተረት ነው" በማለትና ዋጋውን በማሳነስና በማጥላላት ትውልዱ ከአኩሪ ታሪኩ ተምሮ የአባቶቹንና የቀደምቶቹን ጀግንነት እንዳይደግም በታሪክ ላይ ሰፊ የጥፋት ዘመቻ ሲያካሂዱ መኖራቸው ይታወቃል፡፡ አንድነትን ደግሞ አሀዳዊነት፣ ብሔር ብሔረሰቦችን የሚውጥ... እያሉ በማጥላላት፣ ያለስሙ ስም በመስጠትና ጥላሸት በመቀባት የኢትዮጵያውያን የነጻነታቸውና የአሸናፊነታቸው ምንጭ የሆነውን አንድነት በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንዲጠላና ተቀባይነት እንዳይኖረው ለማድረግ ዘመናቸውን ሙሉ ሲታትሩ ኖረዋል፡፡

ታሪክ ላይ ያለውን ለሌላ ጊዜ እናቆየውና ዛሬ አንድነት ቀን በመሆኑ አንድነትን በሚመለከት ትሕነጋውያንና መሰሎቻቸው በአንድነት ላይ ለዘመናት ሲሰብኩት የኖሩት ትርክት ትክክል መሆን አለመሆኑንና የአንድነትን እውነተኛ ምንነት አመክንዮ (ሎጂክንና) ሳይንስን ዋቢ አድርገን እውነታውን ለመመልከት እንሞክራለን፡፡ ለመሆኑ ግን የመልካም ነገሮች ሁሉ ጠላት የሆነውና የክፋትና የጥፋት አበጋዙ ትሕነግ እንደሚለው እውነት አንድነት ጎጂ ነገር ነውን? እነርሱ እንደሚሉትስ አንድነት ራስን በራስ የማስተዳደር መብት የሚያስቀር፤ ብሔር ብሔረሰቦችን ለመዋጥ በማጭበርበሪያነት የሚያገለግል ነውን? "የውሸት አንድነት" የሚባል አንድነትስ ሊኖር ይችላልን?

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሱ በአጭሩ አይደለም፣ ሊሆንም አይችልም! የሚል ነው፡፡ "ለምን?" ለሚለው አመክንዮአችንን እናቅርብ፡፡ ትሕነጋውያን ለአንድነት ሌላ ስም በመስጠትና ከእውነታው በተቃራኒ ለቃሉ አሉታዊ ትርጉም በመፈብረክ አንድነት ላይ በዚህ መንገድ አዲስ ትርክት ፈብርከው አንድነትን የማስጠላትና የማጥላላት ዘመቻ ውስጥ የገቡበት ምክንያት እነርሱ እንደሚሉት አንድነት ሕዝብን የሚጎዳ ነገር ሆኖ አይደለም፡፡ የራስን በራስ የማስተዳደር መብትን የሚነፍግ፣ ፌዴራላዊ ሥርዓትን የሚያጠፋ፣ ወደ አሃዳዊ ሥርዓት የሚመልስ፣ ብሔር ብሔረሰቦችንም የሚውጥ ስለሆነም አይደለም፡፡ እነርሱም ለሕዝብ አስበው አይደለም እንዲህ ዓይነቱ የሃሰት ትርክት ውስጥ የገቡት፡፡ እውነተኛው ምክንያታቸው ከዚህ ትርክት ጀርባ እነርሱ ማግኘት የሚፈልጉት የራስ ብቻ ተጠቃሚነት ርካሽ የጥፋት ትርፍ ነው፡፡

ይኸውም ትሕነጋውያን "የአሃዳዊነት መሳሪያ ነው" በሚል በሃሰት አንድነትን የሚወነጅሉትና እንዲጠላ የሚያደርጉት ለብሔር ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር "መብት" እና ለሕዝቦች "እኩልነት" አስበውና ተቆርቁረው ሳይሆን ይህንን ሽፋን አድርገው የራሳቸውን ጥቅም ለማስቀደም ነው፡፡ ትሕነጋውን በአንድነት ላይ የዘመቱት ሁሌም እነርሱ ብቻ የበላይ ሆነው ለመኖር የሚፈልጉ ጊዜ ያለፈበት የ"እኔ አውቅልሃለሁ" የክፋት ፖለቲካ መስራችና አራማጅ በመሆናቸው በለመዱት የ"ጨቋኝ-ተጨቋኝ" የሃሰት ፍረጃ ትርክታቸው ራስን በራስ በማስተዳደር ሽፋን ሕዝብን ለመከፋፈልና ሕዝብን አለያይተው፣ በጠላትነት አቧድነው ተከፋፍሎ የተዳከመ ሕዝብን ያለ ተቃውሞ በበላይነት ለመግዛት ነው፡፡

እነርሱ እንደሚሉት አንድነት በምንም ተዓምር የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ሊጨፈልቅ አይችልም፤ "የውሸት አንድነት" የሚባል ነገርም የለም፡፡ "ውሸት" የሚሆነው እነርሱ እንደሚያደርጉት ለብሔር ብሔረሰቦች መብት በመቆርቆር ሽፋን የራሱን የበላይነት ለማምጣት አብረው የሚኖሩ ሕዝቦችን የሚከፋፍለው የሀሰት "ተቆርቋሪነት" ነው፡፡ ይህም ለብሔር ብሔረሰቦች ያዘኑ በመምሰል የራስን የበላይነት ለማስፈን የሚደረግ ድብቅ ሴራ ነው፡፡ እናም የሕዝቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት የሚነፍገውና ማንነታቸውን የሚጨፈልቀው መደጋገፍንና መተባበርን መሰረት ያደረገውና ለእኩልነት በጋራ የሚሰራው አንድነት ሳይሆን የራሱን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅና በሌሎች ላይ የበላይ ሆኖ ለመኖር "አንድነትን እያጥላላ" ሕዝብን ከፋፍሎ አዳክሞ ለመግዛት የሚሞክረው የትሕነጋውያን የጥቅምና የክፋት እኩይ ፖለቲካ ነው፡፡

አንድነትማ የተራራቀውን ያቀራርባል፣ የተቃቃረውን ያስማማል፣ በልዩነቱ ምክንያት አብሮ መኖር አቅቶት የተለያየውን አንድ ያደርጋል፣ በብዙነቶችና በልዩነቶች ስምምነት በጋራ ጉዳዮች ደግሞ ሕብረት እንዲፈጠር ሕዝቦች በፍቅርና በሰላም አብረው እንዲኖሩ ያደርጋል እንጂ እንዴት አድርጎ መብትን ያፍናል? እንዲያውም "የአንዲት ሀገር ዕድገትና ታላቅነት የሚለካው በሕዝቦቿ አንድነት ነው" እንዲሉ ታላቁ ንጉሠነገሥት አፄ ቴዎድሮስ ስምምነትና ሕብረት የጋራ ዕድገትና ብልጽግና ይፈጥራል እንጂ እንዴት አንድነት ጭቆናን ይወልዳል?

እናም እላችኋለሁ ትሕነግና የትሕነግ ጀሌዎች የቱንም ያህል ትርጉሙን ለማጣመም ቢሞክሩ፣ እንዲጠላ ቢጥሩ እውነታውን መቀየር አይችሉም፡፡ በሃሰት ፕሮፓጋንዳና በዘመቻ ብዛት አይለወጥም፡፡ አንድነትን የሚጠላም አያገኙም፡፡ ምክንያቱም ዛሬም ነገም ወደፊትም አንድነት አጥፊ ሆኖ አያውቅምና፡፡ አንድነት ያው አንድነት ነው ሌላ ትርጉም የለውም፡፡ አንድነት እውነተኛ ትርጉሙ ሕብረት ነው፣ ሕብረትም ኃይል ነው፡፡ ኃይል ደግሞ በፊዚክስ ሕግ የማይጠፋ፣ የማይፈጠር- ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ ፀንቶ የሚኖር ማለት ነውና! ኢትዮጵያም በአንድነቷ ለዘላለም ትኖራለች!

# ዓለም አቀፍ

## አማካይ የዕድሜ ጣሪያ መቀነሱን የተባበሩት መንግሥታት ጥናት አመለከተ

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከተከሰተ ጀምሮ አማካይ የዕድሜ ጣሪያ፣ የትምህርት እና የምጣኔ ሀብት እድገት መቀነሱን የተባበሩት መንግሥታት ጥናት አመለከተ። የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት በየዓመቱ ይፋ በሚያደርገው 'ሂዩማን ዴቨሎፕመንት ኢንዴክስ' ሪፖርት እንዳመለከተው ባለፉት ሁለት ዓመታት ከአስር አገራት ዘጠኙ ከነበሩበት ወደ ኋላ ተመልሰዋል።

ለዚህ የዓለም እድገት ወደ ኋላ መቀልበስ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ የዩክሬን ጦርነት እና የአየር ንብረት ለውጥ ያሳደረውን ተጽዕኖን በምክንያትነት ጠቅሷል። ሂዩማን ዴቨሎፕመንት ኢንዴክስ የተዋወቀው እንደ አውሮፓውያኑ በ1990 ሲሆን ዓላማውም ደህንነትን ለመለካት የአገር ውስጥ ምርት ዕድገትን (ጂዲፒን) ከመጠቀም ባሻገር ለመመልከት ነው።

በዚህ ዓመት ባወጣው ሪፖርቱ ላይ የስዊዘርላንድ አማካይ የዕድሜ ጣሪያ 84 ዓመት ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በጥናቱ ከተካተቱ አገራት በመጀመሪያ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። ከዚህ ውስጥም ዜጎቿ በአማካይ 16.5 በመቶ የሚሆነውን ዕድሜ ያሳለፉት በትምህርት ሲሆን አማካይ የደመወዝ መጠናቸውም በዓመት 66 ሺህ ዶላር ነው።

በሌላው በኩል ደግሞ በደቡብ ሱዳን አማካይ የዕድሜ ጣሪያ 55 መሆኑን ጥናቱ አመልክቷል። ዜጎቿም ከዚህ ውስጥ በትምህርት ያሳለፉት 5.5 በመቶ የሆነውን ዕድሜያቸውን ብቻ ሲሆን የሚያገኙት አማካይ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢያቸውም 768 ዶላር ሆኖ ተመዝግቧል። በዚህ ጥናት ከተካተቱ 191 አገራት አብዛኞቹ በተለይም በአማካይ የዕድሜ ጣሪያ ጥናት ላይ በ2016 ወደነበሩበት ተመልሰዋል።

በአሜሪካ በውልደት ወቅት ያለው የዕድሜ ጣሪያ ከአውሮፓውያኑ 2019 ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ያህል አሽቆልቁሏል። ጥናቱ ከተጀመረ ጀምሮ በነበሩት ባለፉት ዓመታትም አብዛኞቹ አገራት ቀውስ ያጋጠማቸው መሆኑን ያመላከተው ሪፖርቱ፤ አገራቱ ወደኋላ መመለሳቸውን ገልጿል።

የዕድሜ ጣሪያ ባለፈው ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ መቀነሱን ያመላከተው ጥናቱ፣ የዚህ ዓመቱ ውጤት እያሽቆለቆለ መሆኑ በተጨባጭ የታየበት ነው ብሏል። በዚህ ዓመት ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ሃብታም አገራት ባለፈው ዓመት ወደነበሩበት የተመለሱ ሲሆን የሌሎቹ ግን አሁንም ማሽቆልቆሉን ቀጥሏል።

የዚህ ዓመት ጥናት የተሰራው ከባለፈው ዓመት በተወሰደ



መረጃ መሆኑን የጠቀሱት ከአጥኚዎቹ አንዱ የሆኑት አቺም ስቴነር፣ ከ80 በላይ አገራት ብሔራዊ ብድራቸውን በመክፈል ችግር ላይ ናቸው ብለዋል። አቺም ስቴነር ከእንደዚህ ዓይነት ቀውስ አንድ እርምጃ የራቁት ስምንት አገራት ብቻ መሆናቸውም ችግሩ ከባድ መሆኑን ያሳያል ማለታቸውን ቢቢሲ ጠቅሶ ዘግቧል፡፡

## ሰሜን ኮሪያ የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ባለቤት መሆኗን በይፋ አወጀች

ሰሜን ኮሪያ ራሷን የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ባለቤት መሆኗን ይፋ የሚያደርግ ሕግ ማወጇን የአገሪቱ መንግሥት ዜና ወኪል ኬሲኤንኤ ዘገበ። የአገሪቱ መሪ ኪም ጆንግ ኡን ውሳኔውን "የማይቀለበስ" ሲሉ ገልጸውታል። ኒውክሌር ካለመታጠቅ ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት ድርድር ሊኖር እንደማይችልም ገልጸዋል።

በአዲሱ ሕግ መሠረት ሰሜን ኮሪያ ራሷን ለመከላከል በሚል ቀድሞ የኒውክሌር ጥቃት የመፈጸም መብት እንዳላት ይደነግጋል። ፒዮንግያንግ በተደጋጋሚ ማዕቀብ ቢጣልባትም ከ2006 እስከ 2017 ባለው ጊዜ ስድስት የኒውክሌር ሙከራዎችን አድርጋለች።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔዎችን በመጣስ ወታደራዊ አቅሟን ማሳደጓን



ኪም ጆንግ ኡን ፤

ቀጥላለች። የጦር አቅሟን በማሳደግ ከጎረቤቶቿ በተጨማሪ አሜሪካን ማጥቃት ሚያስችሉ መሣሪያዎችን ታጥቃለች። ኪም እ.ኤ.አ. በ2019 ከወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ጋር ሁለት ዙር ንግግር ካደረጉ በኋላም የረዥም ርቀት የሚሳኤል እና የኒውክሌር ሙከራዎችን አድርገዋል።

አሜሪካ እና በሰሜን ኮሪያ መካከል ሲካሄድ የነበረው ውይይት በኋላ ላይ ተቋርቷል። የባይደን አስተዳደር ከፒዮንግያንግ ጋር ለመነጋገር ፍቃደኛ መሆኑን ተጠቁሟል። ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ከኪም ጋር በቀጥታ መገናኘት ስለመፈለጋቸውን ግን አልተነገረም። ፒዮንግያንግን ለማግኘት እና በኮቪድ ወረርሽኙ ዙሪያ ድጋፍ ለማድረግ ያደረገው ሙከራ አለመሳካቱን ዋይት ሐውስ አስታውቋል።

አሜሪካ በሰሜን ኮሪያ ላይ ያላትን ፖሊሲዋን ባለፈው ዓመት ገምግማለች። የኮሪያ ልሣነ ምድር "ሙሉ በሙሉ ከኒውክሌር ነጻ መሆኑ" ዓላማው እንደሆነ በድጋሚ ተናግራለች። ባይደን ከአገሪቱ ጋር የሚኖራቸው ግንኙት ዲፕሎማሲ እና "ጠንካራ መከላከልን" እንደሚያጣምር ተናግሯል። ኪም በበኩላቸው አገራቸው "ለውይይት እና ለግጭት" መዘጋጀት አለባት ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

በዚህ ዓመት ፒዮንግያንግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የባለስቲክ ሚሳኤሎችን በማስወንጨፍ በኮሪያ ልሳነ ምድር ያለውን ውጥረት አባብሳለች። ይህን ተከትሎ ደቡብ ኮሪያ እና አሜሪካ ሚሳኤል በማስወንጨፍ እና በባሕረ ገብ መሬቱ አካባቢ ትልቅ የተባለውን የጋራ ወታደራዊ ልምምድ በማድረግ ምላሽ መስጠታቸውን ቢቢሲ በዘገባው አመልክቷል፡፡

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# መመስረት፤ መገንባት

በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ

ወጣቶቹ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ናቸው። ሰላማዊ ሰልፉን ያስተባበሩት፤ መፈክር የጻፉት፤ በሰልፉ ላይ የመሪነትን ሚና የወሰዱት ሁሉም በተሰጣቸው ሃላፊነት ላይ ሆነው ስራቸውን ይሰራሉ። ስራቸውንም ሰርተው ሞቅ ደመቅ ያለውን ሰልፍ አድርገው ተመልሰዋል። የሰላማዊ ሰልፉን አፈጻጸም ለመገምገም ቀጠሮ ይዘው በቀጠሮው ቦታ ሁሉም አስተባባሪዎች ተገኝተዋል።

አንደኛው ወጣት "ዛሬ መቼስ ሚዲያዎች ይህን ሰልፍ እንዴት እያደረጉ እንደሚዘግቡት ለማየት ጓጉቼያለሁ አለ።" ወጣቱ በሞቅታ ነገሮችን በማስረዳት የሚታወቅ ነው። አንድ ስራ ጥሩ ተሰራ ብሎ የሚያስበው ነገሮች በሞቅታ ውስጥ ሲከናወኑ ነው። ስብሰባ ራሱ ሞቅ ካላለ ውሳኔ የተላለፈ አይመስለውም። ደጋፊዎች በሌሉበት ሜዳ ውስጥ ኳስ መጫወት በጠባብ ክፍል ውስጥ ፈረስ እንደመጋለብ እንደሆነም ሲያስረዳ ተደምጧል። ይህ ወጣት የሰልፉ ውጤት ምንም ይሁን ምን ሞቅ ያለ መሆኑና ሚዲያዎችም በደንብ የሚዘግቡት ሆኖ ማለፉ ትኩረቱን ይዞታል።

ሌላኛው ወጣት ሰልፉ በመንግሥት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደፈጠረ በማመን "መንግስት መቼስ ከእዚህ በኋላ ለጥያቄያችን የሚኖረው ምላሽ ዝምታ አይሆንም። በሰልፉ ላይ የተላለፈው መልእክት መንግሥት አካሄዱን እንዲፈትሽ የሚያስገድደው ነው።" አለ። ይህኛው ወጣት ሰልፉ የፈጠረው ተጽእኖ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል በማመኑ ከሚፈለገው ውጤት አንጻር የተቃኘ ነው።

ተከታዩ ወጣት ደግሞ ሲቀጥል "እኔ እኮ የሆነ ሰዓት ላይ ፖሊሶቹ ሊተኮሱብን ብዬ ፈርቼ ነበር፤ ግን በቃ ይህ ትግል ነው ብዬ ሞትንም ቢሆን ለመቀበል ዝግጁ ነበርኩ። አሁንም መክፈል የሚገባንን ዋጋ እየከፈልን ትግሉን ወደ ምን ማድረስ እንዳለብን ማሰብ አለብን። ትኩረታችን በትልቁ ምስል ላይ እንጂ በእያንዳንዱ ነጠላ ሁነት ላይ መሆን የለበትም። እያንዳንዱ ነጠላ ሁነት ተመጋግቦ ሊፈጥረው የሚገባውን ትልቁን ምስል ማግኘት ያስፈልጋል።" አለ። ሁሉም የየራሱን ሃሳብ እያወጣ እያወረደ ቆየና ሰልፉን ገምግሞ ለቀጣይ ሥራ ምክክር አድርገው፤ በቀጣይ ከሰልፉ ተከትሎ በተጨባጭ የሚሆነው ነገር ላይ ለመነጋገር ቀጠሮ ይዘው ወደየቤታቸው ተበታተኑ።

ከሰልፉ በኋላ በተጨባጭ የመጀመሪያው ወጣት እንዳሰቡት ሚዲያዎችም ትኩረት አልሰጡትም፤ መንግሥትም ሰልፉን ተከትሎ አዲስ የወሰደው እርምጃም አልነበረም። ሁለቱ ወጣቶች ተስፋ ቆረጡ፤ ቀጣይ የሚደረገው ትግልም ወደ ውጤት ሊያደርስ ስለማይችል መተው ነው ብለውም አመኑ። ተስፋ በቆረጠ ድባብ ውስጥ ሆነው ተገኙ። ሦስተኛው ወጣት ግን በዚህ ጊዜ ወጣቶቹ ካሉበት ስሜት አውጥቶ ወደ ተሻለ ውጤት ሊያደርስ የሚችልን ሃሳብ ይዞ መጣ። ወጣቱ ይዞ የመጣው ሃሳብ ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ወደ እያንዳንዱ ሰው የበለጠ ቅርብ መሆን የሚል ነበር። በአደባባይ የሚቀርበው የራሱ የሆነ ውጤት ቢኖረውም፤ በሚዲያ የሚተላለፈውም እንዲሁ የራሱ ጥቅም ቢኖረውም በግለሰብ ደረጃ ሰዎች ጋር በሚኖር ግንኙነት የሚመጣው ውጤት ግን ከፍተኛ እንደሆነ አስረዳ። የበለጠ ወደ ሰው በቀረብን ቁጥር የበለጠ ተጽእኖ እንፈጥራለን ብሎ እንደሚያምን አስረዳ። የጋራ ስምምነት ላይም ደርሰው አዳዲስ ድምጻቸውን የሚያሰሙበትን መንገድ ቀየሱና ተሰማሩ።

የሰልፍና የሚዲያ አድናቂው እንዲህ አለ "በሜዳ ላይ ወጥተን ስለጮህን ብዙ ውጤት አላመጣንም፤ ነገር ግን የተወሰነ አካባቢን ለብቻ ነጥለን ሰውን በብዛት ሰብስበን ስናወያይ ውጤት አገኘን፤ ቀጥሎ ደግሞ በቡድን በቡድን እየሆንን የመንግሥት ሰዎች ለውጥ እንዲያመጡ ደብዳቤ ስንልክላቸው ለውጥ ማየት ጀመርን፤ እናም ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ እንዲያመጡ ወደምንፈልጋቸው ሰዎች በተጠጋን ቁጥር ነው ለውጥ እያመጣን ያለነው።" በማለት ምስክርነቱን ሰጠ።

በምድር ላይ ለውጥ እንዲመጣ በብዙ የደከሙ አሉ። የደከሙት ለውጥ በምን ያህል ደረጃ ተጽእኖ አመጣ የሚለውን መርምረን በቅደም ተከተል አስቀምጠን የስኬታቸው ምክንያትን ለመመርመር ስንሞክር የምናገኘው መልስ አለ፤ እርሱም መመስረት፤ መገንባትን ያሳየናል።

ህዝብ እንደ ህዝብ ተንቀሳቅሶ አንድን አላማ ማሳካት እንዲችል ከጀርባው ህዝብን የሚያደራጁ፤ በህዝብ ውስጥ ሃሳብን የሚጨምሩ አሉ። በማህበራዊ ለውጥም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ላይ ሰዎችን አንቀሳቅሶ ስለ ብዙሃን የሚሆን ለውጥን ለማምጣት ይህ አሰራር አዋጭ ሆኖ በታሪክ ውስጥ ተቀምጧል።

ወጣቶቹ ወደ አደባባይ ወጥተው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የጮሁት ጩኸት እንዳሰቡት ለምን ለውጥ እንዳላመጣ በገመገሙ ጊዜ የገባቸው እውነት እነርሱ ይዘውት የሚጮሁትን ጉዳይ ይዞ የሚያስተጋባ ከጀርባቸው የተፈጠረ ግንዛቤ አልነበረም። የተሻለ ግንዛቤን የያዙ፤ በእውቀት የተሞሉ ሰዎች ለማናቸውም ዓላማ አመቺ ናቸው። ውጤታማ የሆነን ስራ ለመስራትም የሚችሉ ሆነው ይገኛሉ። በዛሬው ጽሁፍ ስለ መሠረት እና ስለመገንባት እናያለን። ከሰፊው መድረክ ወደ እያንዳንዱ ሰው በመቅረብ ውስጥ ለውጥን ማምጣት ስለመቻል። ኢየሱስ ክርስቶስ የተከተለው ሌሎችም ለውጥ ያመጡ ሰዎች ከአደባባይ በበለጠ በቅርርብ ውስጥ ተከታዮችን ያፈሩበት መንገድ።

መሠረት ለመመስረትም ሆነ ለመገንባት አስፈላጊ የሆነው መንገድ። መምህር ወደ ተማሪው ሲቀርብ፤ አሰሪው ወደ ሰራተኛው ሲቀርብ፤ አስተዳዳሪው ወደሚያስተዳድረው ህዝብ ሲቀርብ፤ ቄሱ፤ ሼኩ ሆነ መጋቢው ወደ መንጋው ሲቀርብ፤ የሚፈጠር ለውጥ። ግለሰብን በመቀየር፤ ቤተሰብን ሆነ ማህበረሰብን የመቀየር መንገድ። መሠረት በመመስረት መገንባት የሚያስችል መንገድ።

## መሠረት

ወደ ላይ ምን ያህል ፎቅ እንደምትገነባ ስታስብ አስቀድመህ የምትሰራው መሰረቱን ነው። መሰረቱ አጥልቆ በተቆፈረ ልክ ወደ ላይ የሚወጣው ከፍታው ብዛት ይወሰናል። በመሰረት ላይ ጊዜውን ያጠፋ፤ የተሻለውን ግንባታ ማድረግ ይችላል። መሠረትን የመመስረት መርህ ለውጤታማ አመራር ቁልፍ እንደሆነ የተለያዩ ጸሃፍት ከትበውት ይገኛል። ሰዎችን አስተባብሮ ውጤት ማምጣት የሚያስብ አንድ መሪ ስለ መሠረት አብዝቶ ማሰብ አለበት። ከስራው በፊት የሚሰራው ቀዳሚ ስራ የመሰረት ስራ ነው። ተከታዩ ስራ እንዲሸከመው የሚታሰበው ስራ የመሰረት ስራ ነው። በወጀብም ሆነ በአውሎ ነፋስ ውስጥ አልፎ ወደ ውጤት መድረስ ታስቦ የሚሰራው ስራ የመሰረት ስራ ነው። በሰው ላይ የሚሰራ፤ በሰው በኩል የሚሰራ።

መሰረትን ለመመስረት ስናስብ የምናስባቸው የመሰረት ግብዓቶች ዋና እሴቶች/Core Values ይባላሉ። የተለያዩ ጸሐፊዎች ግለሰባዊ አቅምን ለመገንባት የሚያስፈልጉን ዐበይት እሴቶችን ይዘረዝራሉ። ዐበይት እሴቶቹ እኒህ ናቸው ብለውም ይዘረዝራሉ። ተቋማት ተልእኳቸውን ለማሳካት ግምት ውስጥ የሚከቷቸውን ዐበይት እሴቶች ዘርዝረው ይገልጻሉ። የተቋሙ በር ላይም ይለጥፋሉ። አንባቢው የሕይወቱ ዋና ወይንም ዐበይት እሴቶች የሚላቸው ምንድን ናቸው?። በተለያየ ጸሐፊያን ደጋግመው ከሚጠቀሱ ግለሰባዊ እሴቶች መካከል ታማኝነት፤ ፍመት (ነገሮችን በንቃት ማድረግ)፣ ጽናት፣ በራስ መተማመን እና ጠንካራ ሰራተኝነት ዋናዎቹ ናቸው። ራእይን፣ የዓላማ ሰው መሆንን፣ ጽናትን፣ ፍቅርን፣ ትእግስትን፣ ወዘተ የራሳችን እንዲሆኑ የምንሰራባቸው እሴቶች ናቸው። እሴቶቹን ለመላበስ በምናደርገው ጥረት ውስጥ ሆነን ማለፍ የፈለግነውን ሆነን ማለፍ እንድንችል የሚረዳ። ፍቅርን እሴቱ ያላደረገ ሰው ውጤታማ ግንኙነትን ከሰዎች ጋር አድርጎ ወደ ውጤት መድረስ አይችልም።

ጠንካራ መሰረት ላይ የሚዘራው የእሴት ዘር አይነት፤ ዘሩ የሚኮተኮትበት መንገድ እና ዘሩ የሚጠበቅበት ጥበብ ወሳኝነት አላቸው። ከትውልድ ትውልድ ጠንካራ የሆነን መሰረት መመስረት እንደ አገር የሚኖርን ጥንካሬ ይወስናል። የእሴት መሰረትን ስናስብ ሦስቱን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። አይነቱን በማስቀደም እንጀምር።

በየአቅጣጫው የሚዘራው ዘር አይነተ ብዙ ነው። የሚዲያ ዘመን እና ሁሉም ነገር በተንቀሳቃሽ ስልክ ጋር የተገናኘ በሆነበት በዚህ ጊዜ ስንኖር የዘር ጉዳይ በደንብ ማሰብን ይጠይቃል። የሚዘራው የእሴት ዘር የሚኖረው ትርጉምን መረዳት የሚኖረንን መሰረት የሚኖረውን አቅም ያሳየናል። ልጆች፣ ታዳጊዎች እንዲሁም ወጣቶቻችን ዛሬ ያሉበት ሁኔታ ትላንት የተዘራባቸው ዘር ውጤት ናቸው። ትላንት የተዘራው የእሴት ዘር ዛሬ ላይ ይዘውት የሚገኙት እሴት ማሳያ ነው። ለነገ እንዲሆኑ የምናስበውን ነገር ደግሞ ዛሬ እንዘራለን። የዘሩ አይነት ግን ሁልጊዜ የሚታሰብበት ነው። በምናየው የቴሌቪዥን መርሃግብር፣ በምናነበው መጽሐፍ፣ አብረናቸው በሚውሉት ሰዎች እንዲሁ የእሴት ስንቃችን ይሰነቃል። የመረጥነውን እንመገባለን፤ በተመገብነው ልክም አቅምም ሆነ ጤንነት ይኖረናል። ከዘሩ ልየታ ቀጥሎ የሚመጣው ኩትኳቶው ነው።

የተዘራው ዘርን ውሃ ማጠጣትና መኮትኮት ለምንዘራው ዘር የሰጠነውን ትኩረት ያሳያል። መኮትኮት ዘሩን የበለጠ ወደ ፍሬ እንዲጠጋ ፍሬውም በጥንካሬ የሚገለጥ እንዲሆን የሚያደርገው ነው። መኮትኮት በሕይወታችን ላይ የተዘራውን ዘር እንደ አዋጅ አንዴ ታውጆ የምንተወው ሳይሆን መላለስን የምንሰራውን ስራ የሚገልጥ ነው። መኮትኮት ዘር የተዘራበትን ሰው ነባራዊ ሁኔታ ተረድቶ ነገሮችን በየጊዜው በመልኩ በመመልከት የሚገለጽ ነው። የተዘራው ዘር ወደ ፍሬ እንዲቀየር ከተፈለገ ሁልጊዜ ጥንቃቄን ይፈልጋል፤ ጥንቃቄውም በመኮትኮት ጊዜ በሚኖር ትኩረት ይገለጻል። መልካም ዘር ስለመዝራት የተጨነቅነውን ያህል ስለ መኮትኮት ትኩረት ካልሰጠን መገንባት ላይ መድረስ አንችልም። ትልቁ መገንባት ያለው መሰረት ላይ ነው፤ መሰረት ደግሞ የተዘራው በአግባቡ ሲኮተኮት የሚጸና ነው።

ዘሩን የመጠበቅ ጥበብ ደግሞ ሦስተኛው ለመሰረት የሚሆነውን ዘር ወደ ፍሬ የምናደርስበት መንገድ ነው። የተዘራውን ዘር ሊነጥቅ የሚመጣ ከተዘራው ዘር በተቃራኒው ያለ የመልካም ዘር ጠላት አለ። በተቃራኒው በኩል ያለውን የክፋት መንገድን በዘመናዊነት እንዲሁም በስልጣኔ ወዘተ አሳቦ የሚመጣን ዘርን መከላከል ያስፈልጋል። ትጋትን ስንዘራ የትጋት ተቃራኒ የሆነ በአቋራጭ መክበር የሚባል ጠላት አለ። ለእያንዳኑ ዐብይ እሴት ተቃራኒ የሆነ ልብን ሰርቆ የሚወስድ ስላለ ራስን መጠበቅ ያስፈልጋል።

ልጆቻችን በቤተሰብ፣ በመደበኛ ትምህርት እና በሃይማኖት መድረኮች ላይ ዛሬ ላይ የሚዘራባቸው ዘር አይነቱ፣ መኮትኮቱ እና ከተቃራኒ ዘር መጠበቁ መሰረታቸው ለረጅም ጉዞ የሚሆን ያደርገዋል። አገራችን በአመታት ውስጥ የምታልፍበት አስቸጋሪ መንገድ ውስጥ ማለፍ መቻሏ በልጆቿ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው። የኢትዮጵያ መዳከም የተዳከመ መሰረት ባላቸው ልጆቿ ውጤት መሆኑ ጥርጥር የለውም። በዘመናት መካከል አገራዊ ጥቅምን ወደ ጎን አድርገው ግለሰባዊ ጥቅምን ባሳቀደሙ ልጆቿ የዓለም ውራ ለመሆን በቅታለች። ዛሬም እንደ ትውልድ የተጋረጠብንን ሙሉ ሰው ሆኖ የመገኘት ፈተናን መወጣት የምንችለው አጥልቀን መቆፈር በቻልንበት የመሰረት ግንባታ ነው። መሰረቱ የጠራና ለፍሬ የሚሆን ትውልድ እንዲመጣ ስለምንዘራው ዘር እናስብ። ዘሩ ወደ ሚታጨድ ምርትነት እንዲቀየር መኮትኮቱና የቅርብ ክትትል ማድረጉ የግድ ነው። ጡሩን ሰብቆ የሚመጣ አፍራሽ የሆነ አስተሳሰብ እየተዋጉ መጠበቅ ደግሞ ሌላው ቁልፍ ነጥብ።

## መገንባት

ግንባታው ተጠናቆ የሚታየው ነው። ግንባታን ሊያደርግ ዝግጅት የሚያደርግ ግለሰብ ከዝግጅቱ ጀምሮ እስከ ግንባታው ማጠናቀቅ



ድረስ የሚያልፍባቸው ምዕራፎች ለሕይወት አስተማሪ በርካታ ቁምነገሮችን ይዟል። በውበቱ ሆነ በጥንካሬው የምንደመምበት ግንባታ እንዲሁ በዋዛ የተገኘ አይደለም። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የተግባር ስራ ውጤት እንጂ። በተጨባጭ የተሰራ ስራ። ግንባታው ከመሰረቱ ጀምሮ በአግባቡ ሲገነባ ቆይቶ የፊንሽኒግ ስራ ቢቀረው ህንጻው የሚሰጠው አገልግሎት በከፍተኛ ሁኔታ ከሚጠበቀው በታች መሆኑ አይቀሬ ነው። ግንባታው ተጠናቆ ወደ ስራ ከገባ በኋላ በየወቅቱ የሚደረገው አስተዳደራዊ የሆነ ስራዎች ካልተሰሩም እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ። የተወሰኑትን የግንባታ ምዕራፎች መነሻ በማድረግ መሰረት፤ መገንባትን እንቀጥል።

መገንቢያውን ቦታ ከማግኘት እንጀምር። መገንባት ሲታሰብ የመገንባት አቅም ስላለ ብቻ እንዲሁ ብድግ ተብሎ ወደ ግንባታ ሊገባ አይችልም። ምክንያቱም ግንባታውን ማከናወኛ ቦታን ማግኘት ስለሚገባ። የግንባታ ቦታውን ለማግኘት በመንግስት መመራት ወይንም በሊዝ መወዳደር ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ህገወጥ ግንባታ ሆኖ አንድ ቀን ሊፈርስ ይችላል። ግንባታው ተገቢውን ውጤት ስለማፍራቱ እርግጠኛ የምንሆንበት እክል ቢገጥመን ጉዳያችንን ይዘን ለፍርድ ቤት አቤት የምንልበት ላይሆንም ይችላል። በሰው ላይ የምናደርገው ግንባታም እንዲሁ ፈቃድ ይጠይቃል፤ የግለሰቡን ፈቃድ።

ግለሰቡ ፈቀዶ ለግንባታው ዝግጁ መሆን አለበት። ህጻናት በተፈጥሮ ህግ ሆኖ ፈቃዳቸውን ሳይገልጹ ግንባታ ይከናወንባቸዋል። ጨቅላ ህጻናት በተፈጥሮ ህግ ገፊነት የእናታቸውን ጡት ፈልገው ይጠባሉ። ህጻናቱ እንዲያድጉ ይጠቅማቸዋል ተብሎ የታሰበውን ምግብ ቤተሰብ አቅም እንደፈቀደ ይመገባል። ውጤቱ አካልን መገንባት ነው። በትምህርት እንዲሁም በማህበራዊ እሴቶች እንዲሁ እንደ ግለሰብ ግንባታው ይሆናል። ነገር ግን ይህ በተፈጥሮ ህግ ተከትሎ የሚደረገው ግንባታ እስከመጨረሻው አይሄድም። ጨቅላው አድርጎ ግራ ቀኙን ማገናዘብ ሲፈልግ ምርጫውን ማሳለፍ ይችላል። በህጻንነት ጊዜ አለመፈለግን በማልቀስና በሌላም መንገድ የሚገለጽ ቢሆንም በእድገት ጊዜ ግን በምክንያት ፍላጎትን ይገልጻል። ከህጻንነት ወቅት በተሻለ ሁኔታ ምክንያታዊነት ቦታውን ይይዛል፤ ምርጫ የሚባለው ሃሳብ በተግባር ይተገበራል።

አንባቢው እድገት ጨርሼያለሁ ከእዚህ በኋላ ማደግ አያስፈልገኝም እስካላለ ድረስ ዛሬም ፈቃዱን ከሰጠ ለማደግ እድል አለው። አካላዊ እድገታችን እንደ ልጅነት ወቅታችን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚቀያየር ባይሆን እንኳን አስተሳሰብ እንዲሁም እሴትን መገንባት ግን ይቻላል። ትላንት የተዘራው በቀላሉ መልቀቅ አዳጋች ቢመስልም ለውጥ ግን ማድረግ ይቻላል። ዛሬ ታዳጊዎች ራሳቸው ላይ መርጠው እንዲዘሩ ማስገንዘብ አስፈላጊ የሚሆነው በብዙ ምክንያት ነው።

መሰረቱ በዋና እሴቶች እንዲሁም ግንባታው በመልካም ፈቃድ ላይ አድርጎ ለቀናቱ ትርጉም የሚሰጥ ሰው መጠሪያው ለመገንባት የተሰራ፤ ለመመስረት የተመሰረተ ማለት ነው።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የመንገድ መሰረተ ልማቶችና ሕዝብ የማስተሳሰርና የአንድነት ስሜት የመፍጠር ፋይዳቸው

መላኩ ኤርሴ



የዘንድሮ አምስቱ የጳጉሜን ቀናት በልዩ ሁኔታ ታይተዋል። ጳጉሜን በመደመር በሚል መሪ ቃል ቀናቱ የየራሳቸው ስያሜ ተሰጥቷቸው በተለያዩ መርሃ ግብሮች እየተከበሩ ይገኛሉ። ጳጉሜን 1 የበጎ ፈቃድ ቀን፣ ጳጉሜን 2 የአምራችነት ቀን፣ ጳጉሜን 3 የሰላም ቀን፣ ጳጉሜን 4 የአገልጋይነት ቀን፣ ጳጉሜን 5 የአንድነት ቀን ተብለው ተሰይመው ነው የተከበሩት።

ዛሬ የ2014 የመጨረሻው ቀን የሆነው ጳጉሜን 5 የአንድነት ቀን ተብሎ እየተከበረ ነው። በእያንዳንዱ የጳጉሜን ቀን ከእለቱ ስያሜ ጋር የተገናኙ መርሃ ግብሮች እና የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን፣ በዛሬው እለትም ከአንድነት ጋር ቁርኝት ባላቸው እና አንድነትን በሚያጠናክሩ መርሃ ግብሮች እየተከበረ ይገኛል።

የአዲስ ዘመን መሰረተ ልማት አምድም መሰረተ ልማቶች በተለይ እንደ መንገድና ትራንስፖርት ያሉ መሰረተ ልማቶች ሕዝብን፣ አካባቢዎችን፣ ሀገርን በማስተሳሰር የአንድነት ስሜትን ከመፍጠር አኳያ ባላቸው ፋይዳ ላይ የሚያተኩር ይሆናል።

እንደሚታወቀው፤ ኢትዮጵያ በየዓመቱ በተለያዩ ፕሮግራሞች በርካታ ኪሎሜትሮችን የሚሸፍን የመንገድ ግንባታ ታካሂዳለች። እነዚህ የመንገድ ፕሮጀክቶች የሚገነቡት ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው በተጓዳኝ ሕዝቦችን፣ አካባቢዎችን እንዲሁም ኢትዮጵያን ከሌሎች ሀገራት ጋር በማስተሳሰር አንድነት እንዲጠናከር ከፍተኛ ሚና ይጨወታሉ በሚል ነው።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ ውስጥ የመንገድ ሽፋን ለማሳደግ በተሰሩ ስራዎች አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል። የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴርን የ2014 በጀት ዓመት የ10 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ባዳመጠበት ወቅት የሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸውን እና የተጠሪ ተቋማትን የአፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡት የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ለ2014 በጀት ዓመት የተያዙ የፊስካል ስራዎች 1 ሺህ 265 ኪሎ ሜትር ነባር መንገዶችን ለማጠናከር፣ የነባር መንገዶች ደረጃን ለማሻሻል፣ የአዲስ መንገዶች ግንባታን ለማከናወን፣ የፍጥነት መንገድ ግንባታን ለማካሄድ ታቅዶ 935 ኪሎ ሜትር መፈጸም ተችሏል።

በሌላ በኩል በ326 ኪሎ ሜትር መንገዶች ላይ ከባድ ጥገና ለማከናወን ታቅዶ 155 ኪሎ ሜትር ማከናወን መቻሉን ሚኒስትሯ ጠቅሰዋል። የ659 ኪሎ ሜትር ወቅታዊ መንገዶች ጥገና ለማከናወን ታቅዶ 523 ኪሎ ሜትር 79 በመቶ መከናወኑን የጠቀሱት ሚኒስትሯ፤ በዚህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ27 በመቶ ብልጫ መታየቱን ነው የተናገሩት። በተጨማሪም የ 8255 ኪሎ ሜትር መደበኛ ጥገና ለመስራት ታቅዶ 7204 ኪሎ ሜትር ጥገና መካሄዱን፣ በአጠቃላይ በመንገድ ግንባታና ጥገና የተመዘገበው አማካይ አፈጻጸም 84 በመቶ መሆኑን አብራርተዋል።

በመንገድ ዘርፍ የተመዘገበው ውጤት የሕዝቦችን ትስስር በማጠናከር ሀገራዊ አንድነትን እውን ለማድረግ ፋይዳው የላቀ መሆኑን በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የዲዛይን አስተዳደር ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ፍሬው በቀለ ይናገራሉ። መንገድ ጽንሰ ሃሳቡ ራሱ ሲነሳ ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ባሻገር ዋና ዓላማው ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ማገናኘት ነው። ከኢኮኖሚያዊ ምክንያት ባሻገር ዋናው ዓላማ ተደራሽነትን ለመጨመር ነው ሲሉ ያመለክታሉ።

ተደራሽነት ሲባል ሰዎች ከመንገድ ያላቸው ርቀት በቅርብ ርቀት እንዲሆን እና በቀላሉ ወደፈለጉበት ቦታ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ማድረግ ነው። ይህም አንድ ቦታ የሚኖር ማሕበረሰብ ሌላ ቦታ በፈለገበት ሰዓት እንዲደርስ ያስችላል። ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚሄዱት ለኢኮኖሚያዊ ተግባራት ሊሆን ይችላል፤ ዘመድ ለመጠየቅም ሊሆን ይችላል። መንገድ በተለያዩ ምክንያቶች ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ያለ እንግልት እንዲንቀሳቀሱ ያስችላል። በተሳለጠ መልኩ ወደፈለጉበት ቦታ ያለ እንግልት መድረስ መቻል ትስስሩ የተሳለጠ እንዲሆን ይጠቅማል።

ሰዎች ሳይገናኙ ሲቀሩ መግባባት ሊከብዳቸው ይችላል። ሰዎች ሳይገናኙ ሲቀር እየተራራቀ ሊሄድ ይችላል። ሰዎች እየተቀራረቡ ሲሄዱ ትስስሩ እየተጠናረ፣ እየተግባቡ እየተስማሙ ይሄዳል። ይህ ደግሞ የሕዝቦች አንድነት እየተጠናከረ እንዲሄድ እደሚያስችል አቶ ፍሬው ጠቁመዋል

በተለይም የገጠር መንገድ/ ዩራፕ መንገድ/ ፕሮግራም ዋነኛው ዓላማ ቀበሌን ከቀበሌ፣ ወረዳን ከወረዳ ማገናኘት ነው። ከዚያ በላይ ዞን፣ ከተማ እና ክልል ያሉትን ደግሞ የፌዴራል መንገዶች አስተዳደር እና የክልሎች የገጠር መንገድ የማገናኘት ስራ እንደሚሰሩ የሚጠቁሙት አቶ ፍሬው፤ ወረዳን ከወረዳ፣ ቀበሌን ከቀበሌ፣ ዞን ከዞን፣ ከተማ ከከተማ፣ ክልልን ከክልል ማገናኘት ማለት ቦታዎችን የማገናኘት ዓላማ ብቻ ሳይሆን ሰዎችን የማገናኘት ዓላማ ነው። ሰዎች የፈለጉበት ቦታ በፈለጉበት ሰዓት እንዲደርሱ የማድረግ ዓላማ ስለሆነ አንድነትን ከማጠናከር ረገድ ያለው ፋይዳ አጠያያቂ አይደለም ሲሉ ያብራራሉ።

እንደ አቶ ፍሬው ማብራሪያ፤ ፕሮግራሞች ሲቀረጹም ይህንኑ ወደ መሬት ለማውረድ ታስቦ ነው። በአንድ ቀበሌ፣ ወይም ወረዳ ያለው ሕዝብ ወደ ሌላ ቀበሌ ወይም ወረዳ፣ በአንድ ዞን ያለው ሕዝብ ወደ ሌላ ዞን ወይም ከተማ ወስዶ ምርቱን እንዲሸጥ ነው፤ ማግኘት የሚፈልገውን ሰው በቀላሉ እንዲያገኝ ለማድረግ ስለሆነ የመንገዶች የመጀመሪያው ጠቃሜታው ተደራሽነትን መጨመር ስለሆነ፤ ተደራሽነት ደግሞ አንድነትን ያጠናክራል። የተራራቀ ሰው መቼም አንድ ሊሆን አይችልም።

መንገድ በኢትዮጵያ ውስጥ አንድን ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ፣ አንድን ዞን ከሌላው ዞን፣ አንድን ከተማ ከሌላ ከተማ ከማገናኘት ባሻገር ቀጠናዊ ትስስርንም እውን በማድረግ ቀጣናዊ ውህደትንም እውን የማድረግ ዓላማም አለው።

ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ናት። አብዛኞቹ ትልልቅ ግብዓቶች የሚገቡት በመንገድ ነው። በዚህ ረገድ በርካታ መንገዶች ተገንብተው ለአገልግሎት በቅተዋል። አሁንም በመገንባት ላይ ናቸው። ቀደም ሲልም ከኢትዮጵያ ወደ ጅቡቲ፣ ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ ኬንያ እና ደቡብ ሱዳን የሚወስዱ መንገዶች ተገንብተዋል።

ድሬዳዋን ከጂቡቲ ወደብ ጋር የሚያስተሳስረው የድሬዳዋ ደወሌ የ220 ኪሎ ሜትር መንገድ ከዓመታት በፊት ተጠናቆ ወደ አገልግሎት የገባ ሲሆን፣ ይህን መንገድ ከአዲስ አበባ ጋር ለማስተሰሰር ከአዳማ፣ አዋሽ፣ መኢሶ፣ ድሬዳዋ፣ ደወሌ የሚደርስ የፈጣን መንገድ ግንባታ አካል የሆነው የአዳማ አዋሽ የፍጥነት መንገድ ፕሮጀክትም ከወራት በፊት ግንባታው ተጀምሯል።

ኢትዮጵያን ከሱዳን የሚያገናኘውና የፖርት ሱዳንን ወደብ ተጠቃሚ የሚያደርገው 604 ኪሎ ሜትር ጠጠር መንገድ ወደ አስፓልት ኮንክሪት ደረጃ አድጎ ለአገልግሎት የበቃ ሲሆን፤ ኢትዮጵያን ከበርበራ ወደብ ጋር የሚያገናኘው መንገድ ደግሞ 483 ኪሎ ሜትር መንገድ ካለው ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታ አንጻር ወደ አስፓልት ኮንክሪት ደረጃ ተገንብቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

የሞምባሳ ወደብን መጠቀም የሚያስችለው የአዲስ አበባ ሞያሌ መንገድ ደግሞ ከሞጆ እስከ ሀዋሳ የትራፊክ ፍሰቱን መጨመር ተከትሎ የፈጣን መንገድ ግንባታ እየተከናወነለት ይገኛል። ፕሮጀክቱ በአራት ምዕራፎች ተከፍሎ ነው ግንባታው እየተከናወነ የሚገኘው። ከሞጆ መቂ፣ ከመቂ ባቱ፣ ከባቱ አርሲ ነገሌ እና ከአርሲ ነገሌ ሀዋሳ ተብሎ በ4 ኮንትራቶች ተከፍሎ ሲገነባ ቆይቷል። ከሞጆ መቂ እንዲሁም ከመቂ እስከ ባቱ ያሉ የመንገድ ፕሮጀክቶች ተጠናቀዋል፤ ከባቱ እስከ አርሲ ነጌሌ እንዲሁም ከነጌሌ እስከ ሀዋሳ ያለው መንገድ ግንባታ ደግሞ እየተፋጠነ መሆኑን የመንገዶች አስተዳደር መረጃ ያመለክታል።

ኢትዮጵያን ከደቡብ ሱዳን ጋር የሚያገናኘው የጋምቤላ ኢታሚን ጂካዎ መንገድም በአስፓልት ኮንክሪት ደረጃ ተገንብቶ አገልግሎት እየሰጠ ነው። የዚሁ አካል የሆነው የሚዛን ዲማራድ 157 ኪሎ ሜትር አስፓልት ኮንክሪት መንገድ በግንባታ ላይ ይገኛል። ተመሳሳይ መልኩ የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ኢትዮጵያን ከኤርትራ ጋር የሚያገናኙ መንገዶች እድሳት እና ግንባታ በሰሜን ኢትዮጵያ ማካሄድ ጀምሮ ነበር።

አቶ ፍሬው እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያን ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚያገናኙ እነዚህ የመንገድ ፕሮጀክቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የማይመረቱ ምርቶችን ከውጭ ሀገራት ለማስገባት እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን ወደ ጎረቤት ሀገራት ለመላክ እንዲሁም ከጎረቤት ሀገራት ጋር ትስስርን ለማጠናከር በጣም ጠቃሚ ነው።

ለእነዚህ የመንገድ ፕሮጀክቶች ከኢትዮጵያ መንግሥት ባሻገር የመንገድ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ በሚያደርጉ እንደ አፍሪካ ልማት ባንክ ያሉ ሌሎች አካላት ጭምር ትልቅ ትኩረት ሰጥተው እውን እንዲሆኑ እንደሚሰሩ የጠቆሙት አቶ ፍሬው፣ እነዚህ አካላት ትኩረት የሚሰጡበት ምክንያት እነዚህ ፕሮጀክቶች ቀጣናውን የሚያስተሳስሩ በመሆናቸው ነው። ምክንያቱም ንግድ መሳለጥ አለበት። ወደብ አልባ ሀገራት ከውጭ የሚገቡ ነገሮችን ማግኘት ይኖርባቸዋል። እነሱም ያላቸውን ምርት ወደ ውጭ ሀገራት መላክ መቻል አለባቸው።

በዚህ የንግድ ትስስር ውስጥም ሰው ከሰው ጋር ይገናኛል፤ ይግባባል፤ ይተዋወቃል፣ እነዚህ ቀጠናዊ ትስስርን የሚያሳልጡ መንገዶች የአንድ ሀገር ሕዝቦች ትስስር እና አብሮነትን ከማሳለጥ ባሻገር ሀገራት ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላቸውን ትስስር ያጠናክራሉ። ትውውቅን ይጨምራሉ፤ የንግድ ግንኙነትን ያሰፋሉ። ስለዚህ ጠቃሜታቸው ላቅ ያለ ነው።

እንደ አቶ ፍሬው ገለጻ፤ ቀጠናውን ማስተሳሰርን እንደ አንድ መርህ ወስዶ የፌዴራል መንገዶች አስተዳደር ቀጠናዊ ትስስርን እውን በሚያደርጉ መንገዶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው። በዚህ ረገድም በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። እንዲህ አይነት ስራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ናቸው።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኢትዮጵያ በዴቻ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ የተገነቡ መሰረተ ልማቶች የኢትዮጵያውያንን አንድነት የሚገልጹ ናቸው። በጥንት አያቶች የተገነቡት አክሱም ላሊበላ የመሳሰሉ ቅርሶች ኢትዮጵያውያን አያቶቻችን በአንድነት ገንብተው ያቆዩት ታሪክ ማሳያ ናቸው።

በተመሳሳይ በአሁኑ ጊዜ እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶችም የኢትዮጵያውያንን ትስስር እና አንድነት የሚያጠናክሩ ናቸው። ለምሳሌ፤ የሁሉንም ኢትዮጵያውያን አንድነት ማሳያ የሆኑ ፕሮጀክቶች የአንድነት መገለጫ ተደርገው ይወሰዳሉ። በፓርኮች ውስጥ የተገነቡ ቅርሶች የአንድነት ማሳያ የሚሆኑ ናቸው። የእኢትዮጵያ ሕዝቦች እሴቶች የሚታዩባቸው ናቸው።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሕዝቦችን አንድነት በሚያጠናክሩ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ከመስራቱ ባሻገር፣ የሀገሪቱ ከተሞች በእኩል ደረጃ እንዲያድጉ እየተሰራ ነው። አዲስ አበባ ሲያድግ በአካባቢው ያሉ ከተሞች ጭምር እንዲያድጉ፣፤ ሀዋሳ ሲያድግም እንዲሁ በትኩረት እየተሰራ ነው።

በሀገሪቱ ውስጥ እየተገነቡ ያሉ የመንገድ ፕሮጀክቶችም ዞኖችን ከዞኖች፣ ክልሎችን ከክልሎች እንዲሁም ሀገራት ጋር ማገናኘትን ያለሙ እንደመሆናቸው ለአንድነት እርሾ የሚሆኑ ናቸው። እያንዳንዱ መንገድ ሕዝቦችን ያስተሳስራል። አንድን ሕዝብ ከሌላ፤ ሕዝብ፣ አንድን ብሄር ከሌላ ብሄር የሚያገናኙ ናቸው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአሸባሪው ሕወሓት ጸረ ሕዝብ ባህሪ ዛሬም በአደባባይ እርቃኑን ታይቷል!

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የሕዝባዊ መንግስት ጥያቄ ወደ ስድስት አስርት ዓመታትን ያስቆጠረ ነው። በተለይም በ1960ዎቹ ይህ ጥያቄ ከፍ ያለ ደረጃ የደረሰበት፤ ብዙዎችን አነቃቅቶ አደባባዮችን ያጥለቀለቀበት እንደነበር የታሪክ ድርሳናት በስፋት የዘገቡት እውነታ ነው።

በወቅቱም ጥያቄውን በአደባባይ ይዘው የወጡ ዜጎች ከፍ ላለ እንግልት፣ መከራና ስቃይ ፤ ተዳርገዋል። ለሞት እና ለስደት የበቁም ጥቂቶች አይደሉም። እውነታው በአገሪቱ ፖለቲካ ላይ ጥሎ ያለፈውም ጠባሳ እስከ ዛሬ ድረስ የሻረ አይደለም።

በአገሪቱ ጥያቄውን ተከትሎ በተፈጠረው የፖለቲካ ግርግር እና ክፍተት ስልጣኑን የያዘው የደርግ አገዛዛ ጥያቄውን ሙሉ በሙሉ በመጨፍለቅ አምባገነናዊ ወታደራዊ አገዛዝ መስርቶ አገሪቱን ለ17 ዓመታት አስተዳድሯል።

የጥያቄውን በኃይል መጨፍለቅ ተከትሎ የተለያዩ ኃይሎች የደርግን አገዛዝ በኃይል ለመታገል ወደ በረሀዎች የፈለሱበት ሁንታ ተፈጥሯል። እንደ ሕወሓት የመሰሉ ቡድኖችም በአንድ በክል የብሔር፤ በሌላ በኩል የሕዝባዊ መንግስትን ጥያቄ አንግበው ወደ ትግሉ ተቀላቅለዋል።

ትግራይን እስከ መገንጠል የዘለቀውን እኩይ ዓላማ በሕዝባዊ መንግስት ምስረታ ቀለም አድምቆ የነበረው አሸባሪው ሕወሓት፤ ሌሎች የአገሪቱን ብሔር፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ከጎኑ በማሰለፍ የትጥቅ ትግሉን በድል አጠናቆ አራት ኪሎ ቤተመንግስት ገብቶ ነበር።

ይህ በሆነ በማግስትም ቡድኑ ብዙ ያወራለትን፤ ሌሎችን በዙሪያው ለማሰባሰብ አቅም የፈጠረለትን የህዝባዊ መንግስት ምስረታ ጥያቄ ወደኋላ በመተው ወዳጅ ነው ብለው ያመኑትንና በትጥቅ ትግሉ ወቅት ብዙ ዋጋ የከፈሉ የፖለቲካ ድርጅቶችንና፤ ሕዝቦችን በመካድ ሌላ አምባገነናዊ ስርአት በመፍጠር ለሕዝባዊ መንግስት ምስረታ የተከፈለውን መስዋዕትነት ከንቱ አድርጎታል።

በስልጣን ላይ በነበረባቸው 27 ዓመታትም የአንድ ቡድን ፈላጭ ቆራጭነት የነገሰበትና ዘረፋ ያገነገነበት ስርአት በመገንባት ኢትዮጵያውያን በገዛ አገራቸው ባእድ የሆኑበትን የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርአት ፈጥሯል። የአገርና የህዝብን ሀብት በመዝረፍም ለስርአቱ አቅም ለመፍጠር ረጅም ርቀት ተጉዟል።

እንደ አገር ሕዝባዊ መንግስት ለመመስረት ከፍ ያለ ተስፋ የተጣለባቸውን መልካም አጋጣሚዎች /የ1997 ምርጫ/ በኃይል በመቀልበስም ቡድኑ ፍፁም ለሕዝባዊ መንግስት ምስረታ ምንም አይነት ፈቃደኝነትና ለዚህ የሚሆን አእምሮ እንደሌለው በተጨባጭ አስመስክሯል። ለዚህ አስተሳሰብ ያልተገዙ አእምሮዎችን በማካላሸትና በማሰደድ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን መርጦ በስፋት ተንቀሳቅሷል።

ቡድኑ በዚህ ፍጹም ፀረ- ሕዝብ ባህሪው የተነሳም በሕዝባዊ እንቢተኝነት ከስልጣን ተወግዷል። ይህንንም ማመን አቅቶት እራሱን ያልተገባ መወዛገብ ውስጥ ከመክተት አልፎ አገርና ህዝብን ከፍ ያለ ዋጋ እያስከፈለ ባለ የሽብር ስራዎች ላይ ተጠምዶ ይገኛል።

ለውጡን በተደራጀ መንገድ ከመቃወም አንስቶ ለውጡ ረጅም እርቀት እንዳይሄድ ብዙ ተግዳሮቶችን ሲፈጥርና ሲያስፈጥር ቆይቷል። ግልጽ የሆነውን ጦርነት በመከላከያ ሰራዊቱ ላይ እስካወጀበት ጊዜና ከዚያም በኋላ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሽብር ስራዎችን አቅዶ በራሱና በሌሎች የጥፋት ኃይሎች ፈጽሟል፤ አስፈጽሟልም።

የአገር መከላከያን በማጥቃት የጀመረው ጦርነት ሲቀለበስ፤ ራሱን ለሌላ ሁለተኛ ዙር ጦርነት አዘጋጅቶ እስከ ሰሜን ሸዋ የዘለቀበት የአራት ኪሎ የስልጣን ጥማት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ህጻናት፣ ታዳጊዎች፣ ወጣቶችና አረጋውያንን ከማስፈጀት ባለፈ ምንም ሳይፈጥርለት በመከላከያ ኃይሉ አንጸባራቂ ድል ተቋጭቷል።

ሽንፈትን ለመቀበል መቼም ቢሆን እራሱን ለማዘጋጀት ያልታደለው ቡድኑ፣ የትግራይን ተስፋዎች /ህጻናት፣ ታዳጊዎችና ወጣቶች/ በዘፈን፣ በተለመደ አሳሳች ፕሮጋንዳና አስገዳጅ ሁኔታዎች በማሰባሰብ እና በማስታጠቅ ለሶስተኛ ጊዜ ወደ ጦርነት ገብቷል።

ጦርነቱን አስመልክቶ የተዘጋጀውና ከቡድኑ ያፈተለከው ሰነድ፤ በሽብር አገርን እንደ አገር በማተራመስ የሚፈጠረውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሕዝባዊ መንግስት መመስረት ዋነኛው የቡድኑ ወደ ስልጣን የመምጣት ስትራቴጂ አድርጎ አስቀምጦታል።

በመላው አገሪቱ ሽብርን በመፍጠር ሂደት ውስጥ እራሱን እንደ አንድ ትልቅ አቅም አድርጎ የገመገመው ቡድኑ፣ አሸባሪውን ሸኔን ጨምሮ ሌሎች ጽንፈኛ ኃይሎችን አጋር አድርጎ እንደሚንቀሳቀስ አመልክቷል። ከዓለም አቀፍ አሸባሪው አልሸባቡ ጋርም “ሕዝባዊ መንግስት” ለመፍጠር በሚደረገው ሽብር ተቀናጅቶ እንደሚሰራ አስታውቋል።

ሕዝባዊ መንግስት በሽብር መፍጠር ላይ ያተኮረው የቡድኑ አሁነኛ ስትራቴጂ፤ ቡድኑን በአግባቡ ለሚያውቁት ብዙ ግር የሚያሰኝ ባይሆንም፤ “የህዝባዊ መንግስቱን” በመመስረት ሂደት ውስጥ አጋር ሆነው የተሰለፉ ኃይሎች ማንነት ግን የቡድኑ አመራሮች የቱን ያህል እብደት ውስጥ እንዳሉ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

በ27 ዓመታት የስልጣን ዘመናቸው የራሱትን፣ ሊያስታውሱት ቀርቶ ሲያስቡት የሚጨንቃቸውን ይህንን እውነታ፤ ዛሬ ላይ ያተርፈናል ብለው ከቀበሩበት የመቃብር ስፍራ ለማውጣትና በዚሁ ለማትረፍ ማሰባቸው ካለፈው ነገር ማር የማይችሉ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው!

---


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


---

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ያለጦርነት መኖር የማይችለው የሽብር ቡድን

**ምሕረት ሞገስ**

አሸባሪው ሕወሓት በጫካ ሆኖ ትግል ሲጀመር አላማዬ ብሎ የተነሳው የጠቅላላው ሕዝብን ጉዳይ ሳይሆን የብሔር ጥያቄን መሠረት አድርጎ የአንድ ብሔርን ጭቆናን እገረስሳለሁ ብሎ ነበር፡፡ በጊዜው በእርግጥ የብሔር ጭቆና ነበር፤ አልነበረም የሚለው አጨቃጫቂ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ ለይደር እናቆየውና በመሰረታዊነት ግን የሕወሓት የጫካ የትጥቅ ትግል መነሻው የብሔር ነፃነት መሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡

በወቅቱ ‹‹ያነሳኸው ጥያቄ ለምን የብሔር ጭቆና ጉዳይ ሆነ›› ብሎ ለመኮነን ቢከብድም ሳያስበው የመንግስትነት ስልጣንን ከተቆናጠጠ በኋላ ግን ሃሳቡ ከጠቅላላው ሕዝብ ጉዳይ ሆነ ከአንድ ብሔር ጉዳይ ወጥቶ የጥቂት ቡድን አባላት ጉዳይ ላይ ብቻ ማተኮሩ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ ከብሔር ጥቅም በላይ የጠቅላላውን ሕዝብ ደህንነት ማስጠበቅ የመላውን ሕዝብ እድገት ማረጋገጥ የመንግስትነት መለያ ግዴታ ቢሆንም፤ ቡድኑ ብሔር ውስጥ ተወትፎ፤ የብሔር ካባ ለብሶ አገርን ሲዘርፍ፤ ህዝብን ሲያሰቃይና ሲያንገላታ ቆይቷል። ፍጹም አምባገነናዊ ስርአት ገንብቶ አገርና ህዝብን ከፍ ያለ ዋጋ አስከፍሏል።

ይህ የቡድኑ ባህሪ ህዝባዊ እንቢተኝነት ፈጥሮ ከፌዴራል ስልጣን እንዲባረር ምክንያት ሆኗል፡፡ በሥልጣን ዘመኑ ‹‹ተሰውቼለታለሁ፣ ቆሜለታለሁ እና ወጥቼበታለሁ› ያለው የትግራይ ህዝብ ሳይቀር የዚሁ የቡድኑ ፈላጭ ቆራጭ አስተሳሰብ ሰለባ ሆኗል።

የትግራይ ህዝብ ቡድኑ በስልጣን በነበረባቸው 17 አመታት ልጆቹን ለጦርነት ገብሮ ካተረፈው ሀዘንና የልብ ስብራት ውጭ በቂ የመጠጥ ውሃ፣ ምግብና መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎችን እንኳን በአግባቡ ማግኘት አልቻለም። የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች ግን በከተሞች ውስኪ የሚራጩ፣ በዘመናዊ መኪኖች የሚፈሱ፣ የታላላቅ ፎቆችና ዘመናዊ መኖሪያ ቤቶች ባለቤት ሆነዋል። ከአገር ውጭ በሚገኙ አገሮች ባለሀብቶች፤ ባንኮችም ዋነኝ ደንበኞች ሆነዋል፡፡

የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች ይህንን የተንደላቀቀ ኑሯቸውን ለማስቀጠል ዛሬም የትግራይን ህዝብ የመስዋእት በግ አድርገው እንዳስቀጠሉ ናቸው። የተለያዩ ማደናገሪያ ወሬዎችንና አስገዳጅ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ በእብሪት የለኮሱዋቸው ጦርነቶች የምስኪኑ የትግራይ ህዝብ ልጆች ደም በተራሮችና ሸንተረሮች እንዲፈስ አድርጓል።

ይህ ሁሉ እየሆነ ባለበት፤ በተጨባጭ ሕወሓት የትግራይ ህዝብ እውነተኛ ጠላቱ እና አጥፊው እንደሆነ መረጃና ማስረጃ መጥቀስ በማያስፈልግበት ሁኔታ ህዝቡ ቡድኑን አንቅሮ ሊተፋው፤ ካራ ቆርጦ ሊጥለው ሲገባ ዛሬም ከእነሱ አልፎ ቡድኑ መላውን ህዝባችንን ዋጋ እያስከፈለው ይገኛል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ዛሬ ላይ ከሕወሓት ጋር ያለውን ልማዳዊ ግንኙነት መቁረጥ፤ ከአእምሮ እና ከህሊና ጋር በቅጡ ተማክሮ ሕወሓትን ይብቃህ ማለት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ለማድረግ የቡድኑ የትናንት ታሪክና አሁናዊ እውነታ ከበቂ በላይ እንደሆነ ለማሰብ አይከብድም።

በስሙ የተነገደበት በኢኮኖሚ በቅጡ ተጠቃሚ ያልሆነው የትግራይ ሕዝብ የልጆቹን ሕይወት እንደሸቀጥ እየተጠቀመበት የሥልጣን መጠበቂያ መገልገያው እያደረገው መሆኑን መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል፤ ይህን የማድረግ የሞራል ሆነ የታሪክ ተጠያቂነት አለባቸው።

አንድ ፓርቲ በልምድ አምልኮ በመኖር የሚገኝ ትርፍ የለም፡፡ ትርፍ ለሌለው ነገር ሕወሓትን የሚያክል ዋጋ መክፈል ሆነ ለመክፈል መዘጋጀት፤ የጤነኛ ማህበረሰብ መገለጫ አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም። ይህንን የተዛባ እውነታ ለመለወጥ እድሉ ያለው በትግራይ ህዝብ እጅ ነው።

መላው የትግራይ ህዝብ ሕወሓትን በመስማት ብቻ ሳይሆን ባህሪውንና ያለበትን ሁኔታ በቅርበት በመከታተልና በማወቅ መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት እራሱን ከጥፋት ሀይሉ ሊያርቅ ይገባል። ከዚህ ይልቅ ከቡድኑ አምባገነናዊ አገዛዝ ሊታደጉት ከሚጥሩና የትኛውንም አይነት ዋጋ ለመክፈል ከተሰለፉ ኃይሎች ጋር መተባበር ይጠበቅበታል።

ሕዝቡ ቀደም ባለው ጊዜ ቢሆን የመንግስትነት ግዴታውን መወጣት አቅቶት ከፌዴራል መንግስት ስልጣን ተወግዶ ወደ ትግራይ ክልል ሲገባና በድጋሚ የመንግስትነት ዙፋንን ለመቆናጠጥ ሴራዎችን ሲያውጠነጥንና የትግራይን ህዝብ ሴራው አካል ለማድረግ ሲባዝን በቃህ ሊለው ይገባ ነበር።

በ2013 ጥቅምት 24 ቀን ለአስርት አመት በቀበሮ ጉድጓድ እየኖረ ሲጠብቀው በነበረው የመከላከያ ሰራዊት ላይ ጥቃት ሲፈፅምና አገረ መንግስቱን አደጋ ውስጥ ሲከት፤ ሕዝቡ ለመከላከያው ያለውን ድጋፍ በመግለጥ ቡድኑንና የቡድኑን የጭካኔ ተግባር መኮነን ይጠበቅበት ነበር።

ቡድኑ በልጆቹ ደም በህዝብ እምቢተኝነት የተነጠቀውን ስልጣንና ከዚህ ያተረፈውን የተንደ ላቀቀ ሕይወትና ፈላጭ ቆራጭነት ለማስቀጠል ተደጋጋሚ ጦርነቶችን በመንግስትና በህዝባችን ላይ ሲከፍት ጦርነት ሊያስከትል ከሚችለው ዘርፈ ብዙ ችግሮች አንጻር ቡድኑን ተው ማለትም ይገባ ነበር። ይህንን ባለማድረጉ የልብ ልብ ያገኘው አሸባሪው ሕወሓት በህዝቡ መቆመሩን አዋጭ አድርጎ እንዲወስድ አድርጎታል።

ከዚህ በመነሳትም ለሶስተኛ ጊዜ ጦር ሰብቆና የጦር ነጋሪት ጎሽሞ ወደ ጦርነት ገብቷል። በዚህም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሕጻናትን ጨምሮ የትግራይ ታዳጊዎችን፣ ወጣቶች እና አረጋውያንን በጦርነቱ እሳት ውስጥ እየማገደ ይገኛል።

ከጦርነቱ ባሻግር በመላው አገሪቱ የኑሮ ውድነትን የሚያባብሱ ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮችን በተቀናጀ መንገድ ከመፈጸም ባሻገር፤ መላ አገሪቱን በሽብር ሁከት በማተራመስ ወደ ስልጣን የመመለስ ቀቢፀ ተስፋውን ለመሞከር እየታተረ ስለመሆኑ ሰሞኑን ከቡድኑ ያፈተለከው መረጃ በግልጽ አመላክቷል።

የትግራይ ሕዝብ ቡድኑ የተነጠቀውን ስልጣንና ከዚህ ያተረፈውን የተንደላቀቀ ሕይወትና ፈላጭ ቆራጭነት ለማስቀጠል እየሄደበት ያለውን የጥፋት መንገድ፤ ትክክል እንዳልሆነ በአግባቡ በመረዳት ቡድኑ ከዚህ አጥፊ መንገድ ከመኳዝ እንዲቆጠብ ጫና ሊያደርግ ይገባል።

# ማህደረ ጤና

# ዓመታዊ ምርመራና ጠቀሜታው

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ዓመታዊ የጤና ምርመራ ወይም (Annual health checkup calendar) እንዳለ ምን ያህሎቻችን እናውቃለን? ጥቅሙስ ምን እንደሆነ እንረዳለን? ለመሆኑ ይህ ቀን እንደ አገር መቼ ይከበራል? ዛሬ ስለዚህ ጉዳይ ልናወጋችሁ ወደናልና ተከተሉን:: ዓመታዊ የጤና ምርመራ አዲሱ ዓመት መጣሁ በሚልበት ወቅት ጳግሜን ተንተርሶ የመጨረሻው ቀን ላይ ይከናወናል:: ጤናማ ሆነን እንድንሻገር ማለት ነው::

ይህ የዛሬው እለት ማለትም ጳግሜን 5 ዓመታዊ የጤና ምርመራ ቀን ብለን እናከብረዋለን:: ስንቶቻችን አድርገነዋል ቢባል መልሱ ጥቂቶች የሚል ይመስለኛል:: ምክንያቱም ሙሉ ምርመራ ወይም ዓመታዊ የጤና ምርመራ እንደ አገራችን የተለመደ ባለመሆኑ ::

በእርግጥ እንደባህል አድርገን የምንናገራቸው በርካታ ንግግሮች ነበሩን አልተጠቀምንባቸውም እንጂ:: ለአብነት ቀድሞ መመርመር ያለውን ጠቀሜታ ከማጉላት አንጻር «ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ» እንላለን ተግባሩ ወዲያ ንግግሩ ወዲህ ሆኖ ሳይገናኙ ቢቀሩም:: ለማንኛውም ይህ ቀድሞ መመርመር ወይም ዓመታዊ የጤና ምርመራ ማድረግ ምን ይጠቅማል? ዓመታዊ ምርመራ ማለትስ ምንድነው? እንዴት ምርመራው ይከናወናልና መሰል ነጥቦችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገኘነውን አብነት በማድረግ እናውጋችሁ::

## አጠቃላይ የጤና ምርመራ ሲባል ምን ማለት ነው ?

ሰዎች ገና ከመታመማቸውና አልጋ ይዘው ከመተኛታቸው እንዲሁም በበሽታው ምክንያት ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት፤ በሽታዎችን በመመርመር የተወሳሰበ የጤና ችግር ከመድረሱ አስቀድሞ ለማወቅ የሚደረግ ምርመራ ነው:: በተጨማሪም የግለሰቡን ለተለያዩ በሽታዎች የተጋላጭነት ደረጃውን ለመለየት የሚያገለግል ምርመራ ማለት ነው::

## የዓመታዊ ምርመራ ጥቅም

ሰዎች ከመታመማቸው አስቀድሞ የሚያደርጉት አጠቃላይ የጤና ምርመራ የሚሰጠው ጠቀሜታ በግለሰብና በሀገር ደረጃ የሚታይ ነው:: ግለሰቦች ከመታመማቸው አስቀድሞ የጤና ሁኔታቸው በምን ደረጃ እንዳለ ማወቅ ይችላሉ:: የጤና ችግር ካለ ህመሙ ስር ሳይሰድና የከፋ ጉዳት ሳያስከትል ተገቢውን ህክምና በማድረግ ፈጣን መፍትሄ ማግኘት የሚችሉበትን ዕድል ይሰጣል:: በተጨማሪም የአመጋገብና የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ በማድረግ ረጅም ዕድሜ እንዲኖሩ ያስችላቸዋል::

እነዚህ ጥቅሞች የሚገኙት በአነስተኛ ወጪ መሆኑ ሲታይ ደግሞ አስቀድሞ በሚደረግ ምርመራ፣ የጤና ሁኔታን በየጊዜው መከተል ጠቀሜታው በምንም ሊተካ የማይችል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:: በተጨማሪም የተሟላ ጤና፣ ጠንካራና በራሱ የሚተማመን ማሕበረሰብ ለመፍጠር ያስችላል::

በሌላ በኩል ጠቀሜታው ከሀገር አንፃር ሲታይ፣ ማሕበረሰቡ አስቀድሞ የመመርመር ባህሉን ቢያዳብር፣ በቀላል ምርመራ ህመምተኛውን በመለየት በወቅቱ የማከም ዕድልን ስለሚፈጥር በጤና ተቋማት ላይ የሚታየውን የህክምና ፈላጊ ጫና ይቀንሳል:: ህሙማን በሽታው ከተባባሰባቸው በኋላ በመምጣት ለከፍተኛ ወጪና እንግልት የመዳረጋቸው ጉዳይ ያጠፋዋል:: ይህ ደግሞ ሀገሪቱ በጤናው ዘርፍ አክሞ ለማዳን የምታወጣውን ወጪ ለመቀነስ ያግዛል::

## የግድ ቅድመ ምርመራ ሲደረግባቸው የሚገቡ የጤና ችግሮች

ሰዎች ከመታመማቸው አስቀድሞ በየጊዜው ቅድመ ምርመራ ሊያደርጉባቸው የሚገቡ የጤና ችግሮች በርካታ ናቸው:: ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የበለጠ ትኩረት የሚሹ በሽታዎችን ማንሳት ተገቢ ነው:: እነዚህ በሽታዎች የማህፀን፣ የጡት ካንሰር፣ የፊኛ፣ የዘር ፍሬ፣ የአንጀትና የጨጓራ ካንሰር፣ ስኳር፣ ደም ግፊት፣ ኮሌስትሮልና ኤች.አይ.ቪ፣ የልብና ከልብ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ህመሞች ትኩረት ሰጥቶ ቅድመ ምርመራ ማድረግ ይገባል:: ከእነዚህ የጤና ችግሮች በተጨማሪ ለዓይን፣ ለጥርስ፣ ለጆሮ፣ ለውፍረትና በደም ውስጥ የስብ መጠን መብዛትን ተከትሎ ለሚከሰቱ የጤና ችግሮች ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል::



## ለቅድመ ምርመራ የተለየ ትኩረት መስጠት ለምን ያስፈልጋል ?

የሞት መጠንን ለመቀነስ፣ የአካል ጉዳትን ለመከላከል፣ ደስታ ማጣትን ለማስቀረት፣ በምንም ነገር ላይ ያለመርካት ስሜትን ለመለወጥ፣ ምቾት አለመሰማት ካለ ችግሩን ለይቶ መፍትሄ ለመስጠት፣ ድህነትንና በማሕበረሰብ ደረጃ የሚከሰቱ ጫናዎችን ለመቀነስ እንዲሁም በሽታው ሳይባባስ ከተገኘ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ይረዳል::

## የቅድመ ምርመራ ባህል

በዓለምአቀፍ ደረጃ በተለይም በምዕራቡ ዓለም ሁሉም ሰው የጤናውን ሁኔታ አስቀድሞ የመከታተል ባህሉ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው:: ለምሳሌ፡- አሜሪካን ብንወስድ ለማህፀን፣ ለጡትና ለአንጀት ካንሰር የሚረገው ቅድመ ምርመራ ከ50 እስከ 70 በመቶ ደርሷል:: በሀገራችን ያለው ሁኔታ ግን እዚህ ግባ አይባልም:: ነገሮች ከከበዱ በኋላ የሚመጡት ናቸው የሚበዙት:: በዚህም የሞት ምጣኔ እንጂ የመዳን ምጣኔው በስፋት አይታይም:: ስለሆነም በጣም ብዙ መስራት ይጠበቃል::

## በዓመታዊ ምርመራ ወቅት የሚካሄዱ ዋና ዋና ምርመራዎች

በመጀመሪያ ደረጃ የሚደረገው ምርመራ የተመርማሪውን ታሪክ ጠይቆ መረዳትና እሱን ተከትሎ ደግሞ አካላዊ ምርመራ ማድረግ ነው:: ከዚህ ቀጥሎ እንደ አስፈላጊነቱ የሽንት፣ የደምና የሰገራ ምርመራን ጨምሮ የላቦራቶሪና በተለያዩ የመሳሪያ ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የተለያዩ ምርመራዎች ይደረጋሉ:: ዕድሜ እየገፋ ሲሄድ ጤና ላይ ለውጦች ይኖራሉ:: ስለዚህም በተለያዩ የሕይወት ደረጃዎች ውስጥ ለተለያዩ በሽታዎች የበለጠ ተጋላጭ ይሆናሉ። እነዚህም በርካታ የካንሰር ዓይነቶችን ፣ የደም ግፊት ፣ የስኳር በሽታ እና የደም ቧንቧ መጥበብ ችግሮችን ያጠቃልላል። በመሆኑም ዓመታዊ የጤና ምርመራ ማድረግ የራስንም ሆነ የቤተሰብዎን መልካም ጤንነት ለመጠበቅ አይነተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ሊታመንበት ያስፈልጋል:: እንደውም ይሄን ተግባር በሕይወት ዘመንዎ በቁርጠኝነት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ ማካተት አለብዎት።

አብዛኛዎቹ የውጭ ሆስፒታሎችን ከዓመታዊ የጤና ምርመራ አንጻር ብናያቸው ዕድሜን መሰረት ያደረጉ ተግባራትን የሚከውኑ ናቸው:: ማለትም ዓመታዊ የጤና ምርመራዎችን ሲያደርጉ ዕድሜ-ተኮር ተግባርን በመከወን ነው:: ምክንያቱም በእነእርሱ እሳቤ ዓመታዊ የጤና ምርመራዎች በዚህ ሁኔታ መከናወናቸው የዕድሜ ጤንነትን ከመጠበቅ አኳያ የማይተካ ሚና ይኖረዋል ብለው ያምናሉ:: እናም ምርመራቸውን ሲያደርጉ በእድሜ ደረጃ ከፋፍለው ነው:: ለአብነት ከታዳጊዎች ጀምረን እንመልከተው:: ለታዳጊዎች የሚደረጉ የጤና ምርመራዎች ዋነኛ ትኩረታቸው ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎቻቸው በመደበኛነት እንደሚሰሩ ማረጋገጥ፣ ቅድመ መከላከል ህክምናዎች እና ህመምተኞች ምንም አይነት የሚያስጨንቅ ምልክት እንዳያሳዩ ማረጋገጥ ላይ ነው:: በዚህም ዶክተሮች በእያንዳንዱ ምርመራ ወቅት የተሟላ በሰውነት ውስጥ ያለ የስብ መጠን (lipid profile) ምርመራ ያካሂዳሉ። ይህም ጥሩ ኮሌስትሮል (HDL) እና መጥፎ (LDL) ኮሌስትሮልዎን እንዲሁም የትራይግሊሰሪድ ደረጃ የሚመረምር ሲሆን፤ ዕድሜያቸው እየገፋ ለሚሄዱ ሰዎች የስትሮክ ፣ የልብ ህመም እና የደም ቧንቧ መጥበብ ተጋላጭነትን ቀድመው ለማወቅ ይረዳቸዋል::

በመካከለኛው የእድሜ ክልል ሲሆኑ ደግሞ ከመከላከል እና አጠቃላይ የጤና ምርመራ ከማድረግ ትኩረቱ የተለያዩ በሽታዎች እና የጤና ችግሮች መኖራቸውን ወደ መለየት ይቀየራል:: ከ35 ዓመት እድሜ በኋላ ያሉ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ከደም ውስጥ ያለ ካንሰርን ለመለየት ያነጣጠረ የጠቅላላ የካንሰር ላብራቶሪ ምርመራ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: እነዚህ ጠቅላላ ምርመራዎች እንደ ዕድሜዎ መጠን እየሰፉ ይሄዳሉ። አብዛኛዎቹ በሽታዎች እና ሥር የሰደዱ ችግሮች በሴቶችም ሆነ በወንዶች ላይ የሚከሰቱት ከ35 እስከ 60 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ነው::

ደም መመርመርም የግድ ነው:: በርካታ የጉበት ምርመራዎች እና የካንሰር አመላካች ምርመራዎችም እንዲሁ ያደርጋሉ:: ምክንያቱም እድሜ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ዶክተሩ የሆርሞንዎን መጠንና የቫይታሚን፣ የማዕድን፣ እና የካልሲየም መጠንን በትኩረት ይከታተላል:: በተፈጥሮ እርጅና ሂደት ምክንያት የሚከሰቱትን መጠናቸው ዝቅተኛ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ለመተካት ተጨማሪ ምግቦች ወይም የሆርሞን ቴራፒን ሊያዝልዎት ይችላል::

በሰውነት ውስጥ ያለ የካልሲየም መጠን መቀነስ ወደ አጥንት መሳሳት ችግር ሊያመራ ይችላል። ሐኪሙ የአጥንትዎን ጥንካሬዎን ወደ ሰውነት ምንም አይነት መሳሪያ ማስገባት ሳያስፈልግ ኤክስሬይ በሚመስል የ DEXA ስካን አማካኝነት የአጥንትን ጥንካሬዎትን እና የአጥንት መሳሳት ችግሮችን በትክክል ይለካል:: ይህ የዕድሜ ክልል ዶክተሩ ለልብ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥበት ነው:: የደም ቅዳ በሽታን ለመመርመር ሐኪሙ የተለያዩ የልብ ምርመራዎችን ማለትም የልብ ተግባርን የሚያፋጥኑ ተግባራትን እያከናወንን የሚደረግ ምርመራ ፣ EKG እና CCTA ጨምሮ የተለያዩ የልብ ምርመራዎችን ሊያደርግ ይችላል::

በሌላ በኩል ዓመታዊ የጤና ምርመራ ሲያደርጉ በጾታም የሚያዩበት ሁኔታ አለ:: ለምሳሌ፡- ለሴቶች የቤተሰቡን ያለፈ የህክምና ታሪክ መናገር ለዶክተርዎ ዓመታዊ የማሞግራም ምርመራ መጀመር ያለብዎትን ዕድሜ ለመወሰን ይረዳዋል፣ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ዶክተሮች ሴቶች ከ50 ዓመት ጀምሮ እንዲጀምሩ ይመክራሉ::

## የጤና ምርመራ ሳይደረግ የቤተሰብ ታሪክ ለምን ያስፈልጋል?

ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ከእድሜ ጋር በሚዛመዱ በሽታዎች እና ሁኔታዎች ችግር የሌለብዎት ቢሆንም ሐኪሙ ስለ አኗኗር ሁኔታዎ እና ስለቤተሰብዎ የህክምና ታሪክ ይጠይቃል:: ለወደፊት ለእነዚህ ችግሮች ከፍተኛ የመጋለጥ እድል እንዳለዎት ወይም እንደሌለዎት እርስዎ የሚሰጧቸው መልሶች ይነግራቸዋል። ከዚያም በመልሶችዎ እና በዓመታዊ የጤና ምርመራ ውጤቶችዎ መሰረት ላይ በመመርኮዝ ሐኪሙ በኑሮ ዘዴዎት ላይ አንዳንድ ለውጦችን እንዲያደርጉ ይመክሮታል:: እነዚህን ምክሮች ደግሞ ለጤናዎ መጠበቅ የማይተካ ሚና ይኖራቸዋል:: ምክንያቱም ዶክተሩ ምክሮችን የሚሰጠው ገለልተኛ እና ክሊኒካዊ ከሆነው ምልከታ አንፃር ነው:: የሳይንስ እና የሕክምና ዕውቀት ላይ ተመስርተው ነገሮችንም ያደርጋሉ:: እናም በተገቢው መልኩ ይህንን ማድረግ ከቻሉ ጥቅሙን በቀላሉ የሚገልጹት አይሆንም::

## ዓመታዊ ምርመራ ባለማድረግ የሚመጣ ጉዳት

የህመም ምልክቶች አለመታየት ማለት አለመታመም ማለት አይደለም:: በሽታዎች ምንም አይነት ምልክት ሳያሳዩ ለረጅም ጊዜ በውስጣችን ሊኖሩ ይችላሉ:: በቅድመ ምርመራ የጤና ደረጃችንን ባለማወቃችን፣ በሽታዎች ስር እንዲሰዱና እንዲሰራጩ በማድረግ የተለያዩ የአካል ክፍሎችን በማይድኑበት ሁኔታ እንዲጎዱ ጊዜና ዕድል እንሰጣቸዋለን:: ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ያጋጠመው የጤና ችግር ከሦስት ዓመት በኋላ ቢታወቅለት በቀላሉ መዳን የሚችልበት ሁኔታ የለም:: ወይም ደግሞ አንዱን አካሉን መልሶ ሊያገኘው በማይችለው መንገድ ሊያጣው ይችላል:: ስለዚህ ቀድሞ የጤናን ሁኔታ ማወቅ ከተወሳሰቡ ችግሮች ያድናል::

## የጤና ምርመራ ባህልን እንዴት ማሳደግ ይቻላል?

በመጀመሪያ ደረጃ ሕብረተሰቡን ስለጤናው ሁኔታ ያለውን ግንዛቤ እንዲያድግ የማስተማር ሥራው ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል:: ለዚህ ደግሞ በማሕበረሰቡ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ ተደማጭነት ያላቸው ግለሰቦችን፣ በየጊዜው ዓመታዊ ምርመራ የሚያደርጉ ሰዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው:: በተለያዩ መንገዶች አርአያ ሆነው ሕብረተሰቡን እየደገፉ እንዲያስተምሩ ማድረግም ያስፈልጋል::

በሌላ በኩል የምርመራ አገልግሎቱን ተደራሽ በማድረግ ደረጃ በደረጃ በሕብረተሰቡ ውስጥ የጤና ሁኔታን የመከታተል ባህል እየዳበረ የሚመጣበት ዕድል መፍጠርም ተገቢ ነው:: ለአብነት የተጀመረው የጤና መድህን ብዙውን የማሕበረሰብ ክፍል የሚያነቃቃና ወደ ህክምናው እንዲሔድ የሚያግዝ በመሆኑ ተግባሩን ማስፋትና ግንዛቤ መፍጠር ላይ መንቀሳቀስ ይገባል::

የጤና ጉዳይ በጤናው ዘርፍ ላይ የሚሰራ አካል ጉዳይ ተደርጎ መታየት የለበትም:: ከዚያ ይልቅ ዓመታዊ ምርመራ አድርጎ የተጠቀመ ሰው መድረኮች ባይሰጡት እንኳን ለጎረቤቶቹ በማስተማር ባህሉን ማዳበር ይቻላል:: ስለዚህም ከግለሰብ የጀመረ ተግባር መከናወን ላይ ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል::

# አንድነትና አንድ አይነትነት

**ተገኝ ብሩ**

በልዩነት ውስጥ አንድ ሆነው የሚዘልቁባት አገር ናት ኢትዮጵያ። በመተሳሰብ እና መቻቻል የሚያድሩባት አገራችን ከሁሉ ጉዳዮች ከፍ ያለች ናት። ጉዳዮቻችንን ተቀምጠን እንድናወራ አለመግባባታችንን ተነጋግረን መቅርፍ እንድንችል ቀድመን አገር ያስፈልገናል። ይህቺ አገር ደግሞ አንድነትዋ የፀና መሆን ይኖርበታል፤ ያንን የምናፀናው ደግሞ እኛ ነን። ስለ አገር ብለን ሁሌም አንድ ሆኖ መቆም ግድ ይለናል። የፀናች እና በሌላው የማትደፈር አገር የሚገነባው ደግሞ አንድ ሆኖ በመቆም ነው።

አንድነትና አንድ አይነትነት የተራራቁ ናቸው። ሁለቱ እጅግ የተለያዩ ትርጓሜ ያላቸው ሃሳቦች ቢሆኑም ልዩነታቸውን በቅጡ የሚረዱት ግን ቁጥራቸው ያንሳል። አንድ መሆን እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ይገባንና፤ አንድ ለመሆን ግን አንድ አይነት መሆን ያለብን ይመስለናል። በዚህም ምክንያት አንድ ለመሆን ሁሉንም አንድ አይነት ማድረግ አለብን እንላለን። ነገር ግን አንድ ለመሆን አንድ አይነት መሆን ፈፅሞ አያስፈልግም።

እኛ በአንድነት ፀንተን የምንኖር፤ ስለእርስዋ ለውጥና ህዳሴ አንድ ሆነን የምንቆም ሁላችንም የምንጋራት አንዲት አገር አለችን። ይህቺን አንድ አገር ጠንካራ ለማድረግ አንድ መሆን ግድ ይለናል። ለውጧን ለማቅረብ መተሳሰርና ህብረታችን ወሳኝ ነው። ነገር ግን እኛ ብዙ ነን። የተለያየ ቋንቋ፣ ባህል፣ ብሄር፣ እምነት እና ማንነት ያለን እጅግ ቁጥራችን የበዛ ሕዝቦች ነን።

ታዲያ እዚህ ላይ ነው ዋንኛው ጉዳይ እነዚህ ልዩነቶች ወደ አንድ አይነት ማቀራረብ ፈፅሞ አይቻልም፤ግን አንድ ሆነ አንዲት አገራችንን ማፅናት ይችላሉ። የአገራችንን አንድነት ለማፅናት አንድ ሆነው ለመቆም አንድ አይነት መሆን አይጠበቅባቸውም።

ስለምን አንድ አይነት ስላልሆንን አንድ መሆን ያቃተን ይመስለናል? እስኪ የእጃችንን ጣቶች እንመልከት አንድ እጃችን ላይ ያሉ ነገር ግን አንድ አይነት ያልሆኑ። አጭር ረጅም መካከለኛ ናቸው። በውፍረትም አንዱ ካንዱ ይለያያሉ። ነገር ግን የተለያዩ ተግባራት ስንከውን አንዱ ለሌላው ረዳት ሆኖ በአንድነት አንድን ተግባር እንድንፈፅም ያግዙናል። በልዩነታቸው ውስጥ ህብረት ፈጥረው ተግባራችንን በወጉ እንድንወጣ ይረዱናል።

አንድ መሆን ከአንድ አይነትነት ጋር ፍፁም ይራራቃል። እንኳን ሌላው እንደኛ ካላሰብክ አላቀርብህም ማለት ቀርቶ፤ እኛ ሌላ ውጫዊ አካል በሌለበት ሁኔታ የተለያየ ሃሳብ ወደ አዕምሮአችን ይፈልቅና ሙግት ውስጥ እንገባ የለ?

ኢትዮጵያ በአንድነትዋ ፀንታ ትኖር ዘንድ አንድ የሆነ የጋራ አቋም ሊኖረን ግድ ይላል። እርስዋ ውስጥ የምነገኝ እኔ አንተ እና አንቺ ወይም እኛ ሁላችንም አንድ ሆነን መቆም እንችላለን አንድ አይነት መሆን ግን አንችልም። የየራሳችን መልክ፣ አመለካከትና ባህሪ ተላብሰን እንድ የሆነችዋን አገራችን በአንድነት ቆመን ማፅናት እንችላለን። እኛ አንድ ሆነን ሺህ መሰናክሎችን ማለፍ የምንችል ነን።

የአንድነት ታላቅነት ከአያቶቻችን በላይ ያስተማረን እውነት የለም። አንድ ሆነው ትልቅዋን አገራችንን ያስረከቡን ጀግኖች ዛሬ ተፈጥሮአዊ የሆነው ልዩነት ምክንያት ልናለያየው ከቶም አይገባም። ብዝሀነት ያከበረ ጠንካራ አንድነት ከእርነሱ መማር ይገባናል።

አንድነት ጥንካሬ ያላብሳልና ለአሸናፊነት ያቀርባል። አሸናፊ የሚያደርገን አንድነት ለመላበስ ግን የግድ አንድ አይነት ሆነን መገኘት የለብንም። በፖለቲካ አመለካከት በባህል በሃይማኖትና በተለያዩ ማሕበራዊ ክፍፍሎች ውስጥ መገኘታችን እውነት ነው። ይህን መቀበል ግድም ይለናል። መልመድ ያለብን እነዚህን እንዴት እናስታርቅ፤ እንዴትስ ለአንድነታችን ጥንካሬ እንጠቀምባቸው የሚለው ነው።

> **ብዝሀነት የእኛ መገለጫ ነውና ያንን አክብሮ በሰለጠነ መንገድ መራመድ ይገባል። በዚያ ልዩነት ውስጥ ወደ አንድነት የሚያቃርቡ ጉዳዮችን ማጉላት የሚያስተሳስሩት ላይ መስራት የእኛ ድርሻ ነው**

በፖለቲካ አቋማችን ብንለያይ፣ በእምነትና በአስተሳሰባችን ብንራራቅ ምንም አዲስነት የለውም። አንድ ሆኖ ለመቆማችን ምንም አይነት እንቅፋት አይፈጥርም። በተገኘንበት ማንነት አንድ አይነት ባንሆንም አንድ ሆነን በመቆም አንዲት የፀናች አገር መመስረት እንችላለን። አባቶች ችለውም አሳይተውናል።

አንድ ትልቅ የጋራ ጉዳይ አለን። እስዋም አገራች ናት። ጉዳዮቻችን ሁሉ ታላቅ ከሆነችው ኢትዮጵያ በታች ናቸው። በየጊዜው እዚህና እዚያ እያነሳን የምንጫቃጨቅባቸ፣ የማያግባቡን የሚመስሉ ሃሳቦችና አመለካከቶች ሁሉ ከዚህች አገር እጅግ በጣም ያነሱ ናቸው። ምክንያቱም ሁሉም ሃሳቦች ያሉት እስዋው ውስጥ ነው። ከሚለያዩ ነገሮች ከፍ የሚሉት የሚያቀራርቡን ናቸው። ለኢትዮጵያ ግዝፈት ልዩነቶቻችን አሳንሰን ብናያቸው ያግባቡናል። ለአገር ጥንካሬና ህልውና ስንል ተቀራርበን ብናወራባቸው እጅጉን ይቀሉናል።

ብዝሀንት የበረከተባት ኢትዮጵያ ሰፊ አገር ናት። ከመቶ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ የሚኖርባት። መቶ ሚሊዮኑ አንድ አይነት አቋም ሊያንፀባርቅ ፈፅሞ አይችልም፣ መቶ ሚሊዮኑም አንድ አይነት የፖለቲካ አስተሳሰብ ሊኖረው ከቶም አይቻለውም። ነገር ግን መቶ ሚሊዮኑም በአንድነት የሚኖርበት አንድ አገር አለው። የቁጥሩ ያህል እንኳን የተለያየ አመለካከትና እምነት ቢኖረውም አገር በሚለው እሳቤ ግን መፅናት፤ አንድ ሆኖ መቆም ግድ ይለዋል።

ኢትዮጵያ በደስታችን ወቅት የቦረቅንባት፣ በኀዘናችንም ጊዜ አንባችንን የምናብስባት በቸገረን ጊዜ የምንጠለልባት ለሁላችን የምትበቃ ሰፊ ጎጆ ናት። ስለዚህም ፀንታ እድትኖር ማድረግ ግድ ይላል። ስናኮርፍም ስንደሰትም እስዋ አገራችን ናት። በቅሬታችን ወቅት ትተናት በደስታችን ጊዜ አለሁ የምንላት እርስታችን አይደለችም።

ኢትዮጵያ ጽኑ የሆነች አንዲት አገር በመሆንዋ ላይ ፈፅሞ የአቋም ለውጥ ሊኖረን አይገባም። በድሎታችን አገራችን እዳልነው ሁሉ፤ በመከፋታችን ጊዜ አገሬ ማለት ግድ ይለናል።

የፖለቲካ አመለካከታችን ስለተለያየ እና የፖለቲከኞች ተግባር ስላልጣመን አገር የምንጠላ፤ በአንፃሩ ደግሞ ስለተመቸን ኢትዮጵያዬ የምንል ዜጎች መሆን ፈፅሞ አይገባም። በመከፋትም በመደሰትም ወቅት አገር አገር ናት። መልካም አይደለም ብለን የምናስበውን ውሳኔና ተግባር በሰከነ መልኩ እኛ ጋር ያለውና የተሻለ ነው የምንለው መፍትሄ አቅርበን መፍታት እንጂ የራስን ፅንፍ ይዞ የሌላን መገፍተር ተገቢነት የለውም።

ዛሬ ላይ መጥፎ ልማድ ተፀናውቶናል የመስጠት እንጂ፤ የመቀበል ልምዱ የለንም። የእኔን እንካ ያንተን እንዳታመጣ የሚለው ስሌት ጋር ተጋብተናል። የእኔ ሃሳብ መልካም ነው፤ የአንተ ግን የሚያሻግር አይደለም ብሎ ማሰብ ልክ አይደለም። ሁሌም መዘንጋት የሌለብን አንድ ለመሆን የግድ አንድ አይነት መሆን እንደሌለብን ነው።

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህልና ማንነት መድረክ ናት። ለዘመናት ሕዝቦችዋ አንድ ሆነው ቆመው ሉዓላዊነትዋ አስከብረው ዘልቀዋል። ዛሬ ላይ አዲስ የተፈጠረ የአመለካከት ልዩነት አልያም ደግሞ የእምነት መለያየት የለም። ባይሆን እምነትና አመለካከታችን የምንተረጉምበትና በተሳሳተ መንገድ የምንተገብርበት ሁኔታ ነው የንትርካችን ሰበቡና ያለመግባባታችን መነሻው። ሰፊ አገር ላይ የሰፋ ሃሳብ ይዞ ቀርቦ መሞገት የተሳሳተው ማርም እንጂ የሚገባው ጉዳዮችን አጣቦ ይዞ መፍቻ መንገዶቹን መዝጋት አይገባም።

ያለችን አንዲት አገር ናትና በእስዋ ጥቅምና ህልውና ፈፅሞ ልንደራደር አንችልም። ጉዳዮቻችን ከእስዋ ማነሳቸው ተረድተን ጉዳዮቻችን ሁሉ ከእስዋ ጥንካሬና መፅናት ጋር ማያያዝ ይገባል። ሁላችንም በጋራ አቅፋ የያዘች የጋራ ቤት ናት። እንደኔ ለምን አላሰብክም አያሻግርም፤ ለምን እኔ እንደፈለኩ አትሆንም የትም አያደርስም። አዎ ብዙ ነን ግን አንድ መሆንና አንድ ሆነን መቆም ግድ ይለናል።

ተፈጥሮአዊ በሆነው ልዩነት ማመን አንድ አይነት ካልሆንን ለምንለው እኛ መፍትሄ ነው። ተለያይተን በብቸኝነት መጓዙ አቅም ቢያሳጣ እንጂ አያፀናም። ፍፁም አንድ የሆነ ማንነትና አንድ አይነትነት የለም። ምን አልባትም እንደምናስበው አንድ አይነትነት መርጠን የምንመሰርተው ቡድን በራሱ የተለያየ አመለካከትና ማንነት የተላበሰ መሆኑ ይገባናል።

በአንድ አይነት ፍላጎት ለመመስረት ከምናስበው ቡድን ይልቅ፤ የአንድነት ጥንካሬ ገብቶን በሚያስተሳስሩ ጉዳዮች ላይ አተኩረን በአንድነት የምንቆምበት ፅናትና ለውጡን እንመለከታለን። ብዙ ነንና አንድ አይነት አመለካከት ልንላበስና ተመሳሳይ አቋም ልናፀባርቅ አንችልም። እንደ ብዝሀነታችን አመለካከታችን ሊለያይ፤ አቋማችን ለየቅል፤ ሃሳባችን የማይጣጣም ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በአንዲት አገር ውስጥ የምንገኝ አንድነት የምንጋራ ዜጎች ነን።

በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የአቋም ልዩነት ሊኖረን ይችላል፣ ብዙዎች የተስማሙበት በግለሰብ ደረጃ ላንቀበልም እንችላለን። ነገር ግን የራስን አቋም ማንፀባረቅና የሌሎችን ሃሳብ ማክበር ልማዳችን ሊሆን ይገባል። ከእኛ ፍላጎት ውጪ በሆነ ልንቆጣ፣ ከቁጥጥራችን ውጪ በሆነው ልናዝን አልያም ደግሞ እጅጉን አምርረን ልንቃወም እንችላለን። ነገር ግን አገር ልንጠላ ወይም ለኢትዮጵያ አገራች ያለንን ስሜት ሊለወጥ ፈፅሞ አይገባንም።

ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከእኛ ስሜት የገዘፈች ናት። ስናኮርፍ የምንተዋት፤ ስንታረቅና በሃሳብ ስንግባባ አለሁልሽ ብለን የምንቆምላት ብቻ አደለችም። ስንስቅ ኢትዮጵያ እንዳልነው ሁሉ በመከፋታችን ውስጥ ከስሜታችን ከፍ ያለችው ታላቅዋን አገር አገሬ ማለት ይገባል።

አንድ እንዳንሆን መለያያ አጀንዳ ፈብርከው ሌሎች ያቀብሉናል። ደካማ እድንሆን ስለሚፈልጉ የሚያለያየንን ጉዳይ ይሰብኩናል። ያኔ ከአንድነት ይልቅ መለያየታችን ይጎላብናል። ይህ ግን የተሳሳተ እሳቤ ነው። ኢትዮጵያ የተፈጠረችው አንድ አይነት ስለሆነች አይደለምን ግን አንድ የሆነ አቋም ባላቸው ሕብረትና ትስስር በገባቸው ታላላቅ አሳቢዎች ነው።

እኛ እየፈጠርን ለአገራችን ሰላም የማይበጅ ለሕዝባችን አንድነት እንቅፋት የሚፈጥር አመለካከትና ተግባር ውስጥ በተደጋጋሚ እንወድቃለን። ነገር ግን በመስከንና አገሬ በማለት እስዋን በማሰብ ከስሜታችን በመስከን ነገሮችን በስክነት መፈተሽ ደጋግሞም ማሰብ ይበጃል።

ብዝሀነት የእኛ መገለጫ ነውና ያንን አክብሮ በሰለጠነ መንገድ መራመድ ይገባል። በዚያ ልዩነት ውስጥ ወደ አንድነት የሚያቃርቡ ጉዳዮችን ማጉላት የሚያስተሳስሩት ላይ መስራት የእኛ ድርሻ ነው። የተለመደ ነውና፤ በፖለቲካ ልዩነት አልያም ደግሞ በእምነት መለያየት ምክንያት ልንኳረፍ እንችላለን። ነገር ግን በመኮራረፋችን የማንተዋት ታላቅ የሆነች የጋራ አገር አለችን።

ልዩነታችንን አጥበን አልያም ደግሞ ተቻችለን የምንዘልቅባት አንድ ሆነን የምናድርባት ከተፋቀርን ለሁላች የምትበቃ ውብ አገር አለችን። ሁሌም ትኩረታችን ሊሆን የሚገባው ልዩነቶችን በምን መልክ ማቻቻል ወይም ማቀራረብና አብሮ ማስኬድ ይቻላል የሚለው ላይ ነው። በእርግጥ ልዩነትን አጥብቦና መነቃቀፎችን ቀንሶ፤ ሰላማዊ የሆነ አካታች ውይይት ማድረግ አን ድአይነት መሆን ሳይሆን አንድ አድርጎ የሚያኖር መቻቻል መላበስ ይቻላል።

ቸር ያሰማን።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የ2014 ዓ.ም የኢኮኖሚው ዘርፍ አንኳር ስኬቶች

ኃይሉ ሣህለድንግል

ሀገራችን ያለፉትን ዓመታት በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ አሳልፋለች:: ሉዓላዊነቷን የተፈታተኑ ሁለት ታላላቅ ጦርነቶች በአሸባሪው ሕወሓት ተከፍተውባታል፤ ~~የአሸባሪው ተላላኪ~~ዎች በተለያዩ አካባቢዎች ያደረሷቸው ውድመቶች እና ጦርነቶቹን ተከትለው የመጡ ዓለም አቀፍ ጫናዎች፣ የኮቪድ ወረርሽኝና የኑሮ ውድነት ሌሎች ተግዳሮቶች ነበሩ:: ጦርነቶቹ የቱንም ያህል ፈታኝ ቢሆኑም፣ ኢትዮጵያውያን በመንግሥታቸው በሳል አመራር በመታገዝ በድል ተወጥተዋቸዋል::

በ2014 ዓመት አሸባሪው ሕወሓት የፈጸመውን ወረራ በመመከት፣ ጦርነቱን ተከትሎ በኢትዮጵያ ላይ የተደረጉ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጫናዎችን በመቋቋም፣ የሀገር ሉዓላዊነትን ከማረጋገጥ በተጨማሪ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በተለያዩ መስኮች ጣፋጭ ስኬቶች ተመዝግበዋል:: ከእነዚህ ስኬቶች መካከልም ዛሬ በሚጠናቀቀው የ2014 ዓ.ም በፈተናዎች ውስጥ በኢኮኖሚው መስክ ከተመዘገቡ ስኬቶች ዋና ዋና ያልናቸውን በዛሬው የስኬት አምዳችን ይዘን ቀርበናልን::


በአባይ ግድብ ሦስት ስኬቶች ተመዝግበዋል

## የዓባይ ግድብ

ግንባታው በ2003 ዓ.ም የተጀመረው የአባይ ግድብ እየተገነባ ያለው በኢትዮጵያውያን አንጡራ ሀብት ነው:: ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ግንባታው ከተጀመረ አንስቶ እስከ አሁንም ድረስ በተለያየ መልኩ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል:: የኢትዮጵያውያን የአንድነታቸው መገለጫ የሆነው ይህ ግድብ ዜጎች ድጋፎችን በማድረግ ብቻ አይደለም ግንባታው እንዲካሄድ እያደረጉ ያሉት:: ግንባታው ላይ ጫና ለማሳደር ግብጽን ጨምሮ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎችን በዲፕሎማሲው መስክ በመዋጋትም ጭምር ነው:: ግንባታው ኢትዮጵያውያን በአንድነት ሆነው የሚገነቡት ግድብ እንደመሆኑም ግድቡን ዛሬ ከሚከበረው የአንድነት ቀን ጋር አስተሳስሮም ማየት ይቻላል::

ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ በአጠቃላይ 5 ሺህ 150 ሜጋ ዋት የአሌክትሪክ ሃይል ያመነጫል:: 13 የሃይል ማመንጫ ዩኒቶች (ተርባይኖች) ይኖሩታል:: በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አባወራዎችን የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ እንደሚያደርግ የሚጠበቀው የዚህ ግድብ ግንባታ፣ ባጋጠመው መጓተት የተነሳ መጠናቀቅ ከነበረበት ጊዜ መዘግየቱ ይታወቃል::

የለውጡ መንግሥት ከሞት የታደገው የዚህ ግድብ ግንባታ ታዲያ የዘገየውን ያህል፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ድሎች በአናት በአናቱ እየተመዘገበበት ይገኛል፤ በ2014 ዓ.ም በተለይ ከየካቲት ወር አንስቶ ግድቡ ሶስት ስኬቶች ተመዝግበውበታል::

ግድቡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ለሁለት ዙር የውሃ ሙሌት ተደርጎለታል፤ እነዚያ የውሃ ሙሌቱ መካሄዱ ይፋ የተደረገባቸው ቀናት ለኢትዮጵያውያን ታላቅ የተባሉ እንደነበሩ ይታወሳል:: ኢትዮጵያውያን በሙሉ በውሃ ሙሌቶቹ መጠናቀቅ የተሰማቸውን ደስታ አደባባይ ወጥተው ጭምር ነበር የገለጹት:: በዚህ ባጠናቀቅነው ዓመት ደግሞ ሦስተኛ ዙር ውሃ መሙላትና ሁለተኛውን ዩኒት ኃይል እንዲያመነጭ በማድረግ ደስታውን ከፍ ማድረግ ተችሏል:: በዚህም በዓመቱ በሁለት ዩኒቶች ማለትም ዩኒት አስር በየካቲት ወር ዩኒት ዘጠኝ ደግሞ በዚህ የክረምት ወቅት ሃይል ማመንጨት ተችሏል::

የዩኒቶቹ ወደ ስራ መግባትን ተከትሎ በሁለቱ ዩኒቶቹ ብቻ ግድቡን ከጊቤ ሶስት የሃይል ማመንጫ ቀጥሎ የሀገሪቱ ሁለተኛው ግዙፍ ኃይል ያመነጨ ግድብ እንዲሆን አድርገውታል:: እነዚህ እያንዳንዳቸው 375 ሜጋ ዋት ሃይል የሚያመነጩ ዩኒቶች፣ አሁን ባለው የግድቡ ከፍታ ከ550 ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ሃይል እያመነጩ ናቸው:: በሙሉ አቅማቸው ሃይል ማመንጨት ሲጀምሩ ደግሞ 750 ሜጋ ዋት ማመንጨት ይችላሉ:: ግድቡ ገና እሸቱን ባቋደሰባቸው በእነዚህ ሁለት ዩኒቶች ለሀገሪቱ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚችል ይገመታል::

ግድቡ በእነዚህ ዩኒቶቹ የኢትዮጵያውያንን በአባይ ወንዝ የመልማት ራእይ እውን መሆን እንዲሁም አባይ ሙብራትም ራትም መሆኑን መጀመሩን አብስሯል:: የአባይ ግድብ ሶስተኛውን ዙር የውሃ ሙሌት ያደረገውም በእዚሁ ክረምት ነው:: ይህም ሌላው የዓመቱ ታላቅ ስኬት ተደርጎ ይወሰዳል:: ግድቡ በአሁኑ ወቅት ከ22 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በላይ ውሃ መያዝ ችሏል:: ገና ከአሁኑ በጉባ አንድ ትልቅ ሃይቅ ተፈጥሯል::

## የገቢ አሰባሰብ

ሀገሪቱ ወጪዋን በራሷ ገቢ ለመሸፈን የምታደርገውን ጥረት ተከትሎ የምትሰበስበው ገቢም እያደገ መጥቷል:: ለእዚህም ማሳያ ከሆኑት መካከል የገቢዎች ሚኒስቴር በተጠናቀቀው (በ2014) በጀት ዓመት 360 ቢሊየን ብር ሊሰብስብ አቅዶ ፣ 336 ቢሊዮን 710 ሚሊዮን 021 ሺ 930 ብር መሰብሰብ መቻሉ ይጠቀሳል፤ በዚህም የእቅዱን 93 ነጥብ 53 በመቶ ማሳካት ችሏል:: አፈጻጸሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የብር 57 ቢሊዮን 494 ሚሊየን 923 ሺ 697 ወይም የ20 ነጥብ 59 በመቶ እድገት አለው::

ገቢው በአገሪቱ በተፈጠረው ጦርነት ብዙ ገቢ ሰብሳቢ ተቋሞች ከስራ ውጪ በሆኑበት ፣ በጦርነቱ ምክንያት የንግዱ አንቅስቃሴ በተቀዛቀዘበት ፣ በተለያዩ አካባቢዎች በሚፈጠሩ ግጭቶች ገቢ ሰብሳቢ ተቋሞች በአግባቡ ስራቸውን እንዳይሰሩ በተቸገሩበት እንዲሁም የንግዱ ማሕበረሰብ ስራውን ተረጋግቶ ባልሰራበት ሁኔታ ውስጥ የተሰበሰበ በመሆኑ የተሻለ አፈጻጸም ሊያስበለው የሚችል መሆኑን ከገቢዎች ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

ተቋሙ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት በገቢ አሰባሰብ ያስመዘገባቸው ውጤቶችም የሚሰበሰበው ገቢ እየጨመረ መምጣቱን ያስገነዝባሉ:: በ2010 በጀት ዓመት 152 ቢሊዮን ብር፣ በ2011 በጀት ዓመት 198 ቢሊዮን፣ በ2012 በጀት ዓመት 233 ቢሊዮን ብር፣ በ2013 በጀት 279 ቢሊዮን ብር፣ እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት 336 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፤ ይህም የገቢውን እድገት ቀጣይነት እንደሚጠቁም የሚኒስቴሩ መረጃ ይጠቁማል::

## የወጪ ንግድ

ሀገሪቱ ከወጪ ንግድ ይበልጥ ተጠቃሚ እንድትሆን ከመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን አቅድ አንስቶ ብዙ ለመስራት ታቅዶ ነበር፤ ይሁንና ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ መጨመር ሲገባው በየዓመቱ ከእቅድ በታች ይሰበሰብ እንደነበርና ጉዳዩ አሳሳቢ መሆኑ በወቅቱ ሲገለጽ እንደነበርም ይታወቃል:: ሀገሪቱ በወጪ ንግድ ለማግኘት ያቀደችውን ገቢ ለማግኘት እንዲቻላት ብዙ ምርት የመላክ፣ የወጪ ምርት አይነቶችንና መዳረሻዎችን የማስፋት አቅጣጫዎችን በመከተል ብዙ ብትሰራም የሚፈለገውን ያህል ገቢ ማግኘት አልተቻለም ነበር::

ይህ ታሪክ ግን በ2014 በጀት ዓመት ተቀይሯል፤ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረመስቀል ጫላ ኢትዮጵያ በተጠናቀቀው 2014 በጀት ዓመት በወጪ ንግድ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንደቻለች አስታውቀዋል:: ለተገኘው ውጤትም የተጀመሩ ሁለንተናዊ የሪፎርም ሥራዎች ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ጠቁመዋል::

በ2014 በጀት ዓመት ከወጪ ንግድ ከ4 ነጥብ 12 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉን የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መረጃዎች ያመለክታሉ:: አፈጻጸሙም በወጪ ንግድ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመዘገበ ነው ተብሏል:: ይህ አፈፃፀም ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀርም የ 13 በመቶ ብልጫ እንዳለው ተጠቁሟል:: በአጠቃላይ ለወጪ ንግዱ ገቢ የግብርናው ዘርፍ 72 በመቶ፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍ 12 በመቶ እንዲሁም የማዕድን ዘርፉ 14 በመቶ አስተዋጽኦ ማበርከት ችለዋል:: ለተመዘገበው ውጤት ሁሉም ዘርፎች ከፍተኛ ርብርብ አድርገዋል::

የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ቀን “የኢትዮጵያን ባለ ልዩ ጣዕም ምርት ይግዙ” በሚል መሪ ሃሳብ በፓናል ውይይት፣ የእውቅናና ሽልማት መርሐ ግብር በተካሄደበት ወቅት የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረመስቀል ጫላ ለተመዘገበው ከፍተኛ የወጪ ንግድ ገቢ የመንግሥት ተቋማት እና የግሉ ዘርፍ የበኩላቸውን ሚና እንደተወጡ ጠቅሰው፣ በቀጣይም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በትብብር እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ በ2014 በጀት ዓመት በወጪ ንግድ የተገኘው ገቢ ችግሮች ውስጥ ሆነን ጠንካራ ኢኮኖሚ እየገነባን መሆናችንን ያሳየንበት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

## የበጋ መስኖ የስንዴ ልማት

ዛሬ የሚሰናበተው የ2014 ዓ.ም ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ታምር የሰራችበት መሆን ችሏል:: ሀገሪቱ ከጥቂት ዓመታት በፊት በበጋ መስኖ የጀመረችው የስንዴ ልማት ፍሬያማ እየሆነ መጥቶ በ2014 ዓ.ም ስኬታማ መሆን ችሏል:: መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ በተጠናቀቀው የ2014 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ዙር ስንዴ በበጋ መስኖ ለማልማት ከ405 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር በመሸፈን 16 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ በመስኖ ማምረት ተችሏል። በሁለተኛው ዙር ደግሞ ከ208 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በስንዴ ዘር በመሸፈን ስምንት ነጥብ 35 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ተመርቷል::

የቆላና የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በአፋር፣ አሮሚያ፣ ሶማሌና በሌሎች ክልሎች እየተስፋፋ መጥቷል፤ ለብዙ የኢትዮጵያውያን አርሶና አርብቶ አደሮች እንግዳ፤ ለቆላማ አካባቢዎች ባዳ የነበረው የቆላ ስንዴ ምርት ዛሬ ላይ በሺዎች የሚቆጠሩ አምራቾች እየተሳተፉበት ይገኛሉ:: በደጋና ወይና ደጋ ላይም አርሶ አደሩ በኩታ ገጠም ማሳ ወንዞችን በመጠቀም በበጋው ወቅት ስንዴ በመስኖ ማልማቱን ተያይዞታል::

በግብርና ሴክተሩ ላይ ተግባራዊ የተደረገው ተሃድሶ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ጉልህ ሚና ማበርከቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታውቋል። ሚኒስቴሩ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚያስፈልግ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚያወጣ የስንዴ ግዥን በመስኖ ስንዴ ልማቱ ማዳን መቻሉንም ነው ያመለከተው።

በዘርፉ በተገኘው ውጤት ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚያስፈልገውን የስንዴ ምርት ፍላጎት በመሸፈን በሚቀጥለው ዓመት ስንዴን ወደ ውጭ አገር ለመላክ የሚያስችል ቁመና ላይም መደረሱንም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድም በተለያዩ ጊዜያት አስታውቀዋል።

ሀገሪቱ በተያዘው በጀት ዓመት የስንዴ ልማቱንም ወደ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ከፍ ለማድረግ ውጥን እንዳላትም ተጠቁሟል። ከዚህ የሚገኘው የስንዴ ምርት ከመኸር ወቅቱ የስንዴ ምርት ጋር ሲዳመር ሀገሪቱ ከሚያስፈልጋት በላይ 10 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ማምረት እንደምትችልም የግብርና ምርምርን ዋቢ ያደረገ ዘገባ አመልክቷል::

የሀገሪቱ የስንዴ ልማት የዓለም አቀፍና የአፍሪካ ተቋማትን እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት በእጅጉ መሳብ ችሏል:: ኢትዮጵያ እስከ ሁለት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ስንዴ ለጎረቤት ሀገራት የማቅረብ አቅም ያላት ሀገር ነች ሲሉ የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንትም አስታውቀዋል:: በጋና አክራ ባለፈው ግንቦት በተካሄደ የቡድን ሰባት ሀገሮች የልማት ሚኒስትሮች ዓመታዊ ስብሰባ መዝጊያ ላይ ባደረጉት ንግግር፣ ኢትዮጵያ በ650ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ሰንዴ ማምረት በሚያስችል ደረጃ ላይ መገኘቷን ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መስማታቸውን ገልጸዋል።

ብሉምበርግ፣ የኬንያው ኔሽን ጋዜጣም እንዲሁ የስንዴ ልማቱን በስፋት ዘግበውታል:: ብሉምበርግ ባለፈው ሰኔ ወር በሰራው ዘገባ ሀገሪቱ በፈረንጆቹ በ2021 አንድ ነጥብ 42 ሚሊዮን ቶን ስንዴ ማምረቷን አስታውሶ፣ በ2022 ደግሞ 2 ነጥብ 4 ሚሊዮን ቶን ስንዴ ለማምረት ማቀዷን በዘገባው አመልክቷል:: ሀገሪቱ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ከሕወሓት ጋር እየተዋጋች ብሄራዊ የስንዴ ልማት በማካሄድ ከውጭ የምታስገባውን ስንዴ በሀገር ውስጥ ለመተካት እየሰራች ነው ሲልም ዘግቧል::

የኬንያው ኔሽን ጋዜጣም እንዲሁ ኢትዮጵያ በስንዴ ምርት ስለምን ተሳካላት? በሚል ርዕስ ሰፋ ያለ ሀተታ አስነብቧል። ቀደም ባሉት ዓመታት የአገሪቷ የግብርና ፖሊሲ በመኸር እና በበልግ ወቅት እርሻ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑን ጠቅሶ፣ ባለፉት ሶስት ዓመታት ግን የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መንግስት ስንዴን በበጋ ወራት መስኖ በክላስተር ማምረት እንደሚቻል በማመን ሶስተኛ የእርሻ ወቅትን አስተዋውቋል ሲል አትቷል::

ሲኤን ኤን በበኩሉ የፕላን ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋን ዋቢ አድርጎ በሰራው ዘገባ ሀገሪቱ የበጋ የስንዴ መርሐ ግብርን በመጠቀም የዝናብ ወቅትን ብቻ በመጠበቅ ይከናወን ከነበረው የግብርና ሥርዓት በመውጣት በመስኖ የታገዘ የስንዴ ልማት እያከሄደች መሆኗን፣ በተሰራው ስራም 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ቶን ስንዴ ማምረት መቻሉን መግለጻቸውን ዘግቧል:: ይህ የተቀናጀ ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ሥርዓትም የተዳከመውን ኢኮኖሚ እንዲያንሰራራ ያግዛል ማለታቸውንም ጠቅሷል::

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## በአዲስ ዓመት - ቤት ለእምቦሳ

መልካምሥራ አፈወርቅ

ጠዋት ማታ በጭንቀት ስትብሰለሰል የከረመችው ወይዘሮ አሁንም ማሰብ መተከዟ አልቀረም። ካረፈችበት መጠለያ እንደመሰሎቿ ተኝታ መነሳትን ለምዳለች። ይህ ብቻ ግን እፎይታ ሰጥቷት አያውቅም። ሁሌም ከዛሬ ባሻገር የሚመጣው ነገ ሕልም መስሎ ይታያታል።

በየቀኑ ልቧ ስለነገ መልካምነት ሳይነግራት አይውልም። ያም ሆኖ ውስጧ እረፍት የለውም። በነገ ውስጥ ያለው ዕድል ዕውን ሆኖ እስኪታየው ለራሷ ፊት አትሰጥም። ሁሌም በመሆን አለመሆን ውስጥ እንደሆነች ቀኑ መሽቶ ይነጋል ። ወጣቷ ወይዘሮ እንዲህ እየተጨነቀች አራት ልጇቿንና ባለቤቷን ደጋግማ ታስባለች።

ባለቤቷ ለፍቶ አዳሪ ባተሌ ነው። ልጆቿ ደግሞ ለዓይን የሚያሳሱ እንቦቃቅላዎች። እሷ ለነዚህ ዓለሞቿ የዓመታትን ዋጋ ከፍላለች። ሁሌም ሰላም አድረው መነሳታቸው የተለየ ትርጉም ይሰጣታል። የእነሱ ቤት ዕንቅልፍ ደግሞ እንደሌሎቹ አይደለም። ስጋት እንደሞላው፣ ፍርሃት እንደሸበበው ሌሊቱ በጭንቅ ይነጋል።

እስከዛሬ የት እንደነበረች ፈጽሞ አትዘነጋም። ከባድ ክረምቶችና የጭንቅ ሌሊቶች እንደዋዛ አልፈዋል። አስራ አምስት ዓመታትን በትዳር ስትኖር ሕይወቷ አልጋ በአልጋ አልነበረም። በመኖሪያ ቤት ችግር ብዙ ተፈትናለች፣ ልጆች በማሳደግ፣ ስድስት ቤተሰብን በወጉ ይዞ መምራት ቀላል አልነበረም። ጥቂት የማይባሉ ፈተናዎችን፣ ሸካራማ የሕይወት መንገዶችን በጽናት መሻገር ግድ ነበር።

ወይዘሮ ዳግማዊት ተስፋዬ ያለፈችውን ጠመዝማዛ መንገድ እያስታወሰች ከዛሬ ባሻገር ስለሚመጣው አዲስ ነገ ታስባለች። አዎ! ነገ ከትናንትናው የበለጠ መልካም እንደሆነ ልቧ ሹክ ይላታል። ነገ ብሩህ ተስፋ ይዞ ብቅ እንደሚል ውስጧ ይነግራታል። ያም ሆኖ ቀኑ ደርሶ በአይኗ እስኪታየው ራሷን አታምንም። ጥርጣሬና ስጋት እየተመላለሱ ይፈትኗታል።

ዳግማዊት እስከዛሬ የቤት እመቤት ነበረች። ባለቤቷ ሰርቶ በሚያመጣው ገቢ እሷንና ቤተሰቦቿን የምታስተዳድር ወይዘሮ። አሁን ደግሞ ውላ የምትገባበት የስራ ዕድል በእጇ ሆኗል። ይህ ዕድል ነገ ከምትናፍቀው ቀን ጋር የተቸራት ስጦታ መሆኑን ታውቀዋለች። ያም ሆኖ ውስጧ በጥርጣሬ እንደተሞላ ቀኑ መሽቶ ይነጋል።

ዳግማዊት ይህን ማሰቧ ያለምክንያት እንዳልሆነ ለራሷ ትነግራዋለች። ማግኘት እንዳለ ሁሉ ከእጅ የገባ ዕድልን መነጠቅ እንደሚኖር ከሕይወት ተምራለች። አሁን የምትጠብቀው ተስፋ ፈልጓት እንጂ ፈልጋ አላገኘችውም። እንዲህ መሆኑ ስጋቷን እየጨመረ ዕንቅልፍ ይነሳት ከያዘ ቀናት ተቆጥረዋል። እሷንና ቤተሰቦቿን ሰብስቦ ከያዘው ጊዜያዊ መጠለያ ወጥታ እስክትመለስ ጆሮዎቿ ክፉ ዜና እንዳያሰሟት ፈጣሪዋን ትማጸናለች።

**ከዓመታት በፊት ...**

ጥንዶቹ ትዳር መስርተው ጎጆን ለማቅናት መነሻ ምክንያታቸው ጽኑ ፍቅር ነበር። ፍቅር ያጸናው ጥምረት ከቁም ነገር ደርሶ አብሮነቱ ሲሰምር በአንድ ጣራ ይኖሩ ዘንድ ግድ ሆነ። ትዳር እንደቃሉ ማነስ ቀላል አይደለም። ሶስት ጉልቻ ጠንቶ ቁምነገር ሲታሰብ ልጆች መወለዳቸው፣ ቤተሰብ መበራከቱ አይቀሬ ይሆናል።

ይህን ተከትሎ የሚመጣ የኑሮ ለውጥም ማንነትን ሊፈትን፣ ከባድ ሀላፊነትን ሊያሸክም የግድ ነው። በወይዘሮዋና በባለቤቷ ሕይወት የሆነውም እንዲሁ ነው። አዲሱ ጎጆ በልጆች በረከት አማረ። ቤታቸው በህጻናት ለቅሶና ሳቅ ደመቀ። ይህ ብቻ ግን ኑሯቸውን ሞልቶ እፎይታን አልሰጠም። በዓመታት ልዩነት የተወለዱ አራት ልጆች ምቹ መኖሪያ፣ የተሻለ ማረፊያ ያስፈልጋቸዋል።

በወቅቱ ወላጆች ይህን አላጡትም። ልጆቻቸው የተሻለው ሁሉ ይገባቸዋል። ያም ሆኖ ካሰቡት የሚያደርስ በቂ ገቢ የለም። ባለቤቷ በጋራዥ ጥቂት መኪኖችን ይጠግናል። ወይዘሮዋ የአባዋራዋን እጅ የምትጠብቅ የቤት እመቤት ነች። ልጆች የመንከባከብ ፤ቤት ጓዳዋን የመምራት ጫናው ለእሷ ተጥሏል። ጥንዶቹ ስለመኖሪያ ቤት ይበጃል ያሉትን ወሰኑ። ኑሮ ሕይወታቸው በአንዳቸው ቤተሰብ ግቢ እንዲሆን ተስማሙ።

**ትዳርና ፈተናው**

እንደታሰበው ሆኖ ሕይወት በቤተሰብ ግቢ ‹‹ ሀ...›› ብሎ ጀመረ። ባልና ሚስት ከህጻናት ልጆቻቸው ጋር ማድቤቱን ቤት አድርገው መኖርን ቀጠሉ። በኪራይ ቤት ልጆች ከስቃይ መዳናቸው መልካም ሆነ። ውሎ አድሮ ዓመታት ከነችግራቸው እንደዋዛ ነጎዱ።

ልጆች ሲጨመሩ፣ ኑሮ ሲወደድ፣ ነገሮች በነበሩበት አልዘለቁም። ዓመል ተለወጠ፤ የቀድሞ ፍቅር ቀዘቀዘ። እግር ከእግር እንደሚጋጭ ሁሉ ሀሳብ ከሀሳብ ተቃረነ። ዛሬ እንደትናንቱ አልሆነም። ለሚመጣው ነገ አብሮነት ሻክሮ ፍቅር ተፈተነ።

በቤተሰብ ግቢ የተጀመረው ሕይወት ከዚህ እውነታ አልራቀም። እንዲህ መሆኑ የ‹‹እኔ›› ይሉት ቤት ለሌላቸው ጥንዶች ከማንም በላይ ሆድ ያስብሳል። ሌት ተቀን በሀሳብ ያስተክዛል። ስለልጆች ዕጣ ፈንታ፣ ስለነገው የሕይወት መንገድ ከልብ ያስጨንቃል።

አንዳንዴ ሕይወት ሁኔታዎችን እንዳላየ፣ እንዳልሰማ፣ ማለፍን ታስተምራለች። አንዳንዴ ደግሞ ለሰላም ሲባል ሁሉን ትቶ ፣ በራስ ላይ መፍረድን ታሳያለች። የነዳግማዊት የመጨረሻ ውሳኔም በአንደኛው ላይ ሆነ። ለሰላም ሲባል ሁሉን መተው።

**አሻጋሪው ቶማስ ...**

የዳግማዊት ባለቤት የጋራዥ ባለሙያ ነው። እጆቹ አሮጌን ይጠግናሉ። መኪኖች ፈተው ይገጥማሉ። ይህን የሚያውቁ አንዳንዶች ፈልገው ያገኙታል። ሙያውን የሚሹም ካለበት ይደርሳሉ። ከምንም በላይ ግን ስለእሱ የሚጨነቅ አንድ ሰው ስለስራው አጥብቆ ያስባል። ቋሚ ቦታ ያለማግኘቱ ያሳስበዋል። የባልንጀራው የቤት ችግር ያስጨንቀዋል፣

አንድ ቀን ቅን አሳቢው ቶማስ ሁሉን አመቻችቶ ባልንጀራውን አስገረመ። እሱ ከሚኖርበት የቀበሌ ቤት ግርጌ ጠጋ ብሎ እንዲሰራ ቦታ ጠቆመው። የጨለማ ብርሃን በሆነው ሰው ምሪት ደጁ የደረሰው ባለሙያ ከቀናት በኋላ ሙሉ ስራውን ጀመረ። ውሎው በቋሚነት ያለእንግልት መሆኑ ውጤታማ አደረገው። እሱን ተከትለው ባለቤቱ ዳግማዊትና አራት ልጆቹ ሰፍራውን ተቀላቀሉ። አመጣጣቸው ሊጠይቁት አልያም ሊጎበኙት፣ አልነበረም። እንደ ሙሴ የሚያሻግራቸው ቶማስ ለመኖሪያቸው መፍትሄ በማምጣቱ እንጂ።

በወቅቱ የተገኘው መኖሪያ የኪራይ አልያም የቀበሌ ቤት አልነበረም። የቤተሰቡ ብቸኛ አማራጭ በስፍራው የላስቲክ ቤት ወጥሮ መስራት ብቻ ነው። ዳግማዊትና ባለቤቷ አራት ልጆቻቸውን ይዘው በአዲሱ የላስቲክ ጎጆ ኑሮን ጀመሩ። አካባቢው ከስራ ቦታ ባለፈ ሌሎች ሰዎች ጭምር ላስቲክ ከሽራ ወጥረው ይኖሩበታል።

**ኑሮ በላስቲክ ቤት...**

በእነዚህ ቤቶች ያሉ በርካታ ቤተሰቦች፣ ችግር ከመከራ ይገፋሉ፣ ደስታና ሳቅን ይጋራሉ። ስጋት ፍርሃትን ይቀባበላሉ። በቤቶቹ ያሉ ነፍሶች በአብዛኛው በቂ ዕንቅልፍ ይሉትን አያውቁም። ሁሌም ከሰውና ከተፈጥሮ አደጋዎች ራሳቸውን ለመታደግ በተጠንቅቅ ቆመው ያድራሉ። ዳግማዊትና ቤተሰቦቿ ይህ አይነቱን የላስቲክ ቤት ሕይወት በየቀኑ ይኖሩታል። ቤታቸው ያረፈበት ቦታ ቀድሞ የጣሊያኖች እንደነበር ይነገርለታል። ይህ በሰፈረ ልደታ ወረዳ ዘጠኝ ክልል የሚገኝ ስፍራ ለዓመታት ታጥሮ የቆየና የማንንም እይታ ያልሳበ ነው። አሁን ግን ነባሮቹን አሮጌ ቤቶች ባጀቡ ጥቂት የላስቲክ ጎጆዎች ደምቆ ይውላል። እንዲያም ሆኖ ለኑሮ ፍጹም አመቺ አይደለም።

የክረምቱ ዶፍና ጎርፍ፣ የሌሊቱ ብርድና ቆፈን፣ የንፋስ ፀሀዩ ግለት ሁሉ በቤቶቹ ላሉ ነፍሶች የየዕለት ሰቀቀን ነው። ምናልባት ድንገቴ እሳት ቢነሳ ይሉት ስጋትም የሁሉም ነዋሪ የጋራ ፍርሃት እንደሆነ ዘልቋል።

ዳግማዊት ለአራት የደረሱ ተማሪ ልጆቿ በዕድሜያቸው የሚያስፈልገውን ታውቃለች፡፤ በየቀኑ ከእኩዮቻቸው ጋር የሚኖር ፉክክር አይጠፋትም። እሷ እንደ እናት ያሰበችውን፣ ካሰቡት ብትሞላ ትወዳለች። ይህ እንዳይሆን ብዙ ብዙ ጎዶሎዎች ይቀድሟታል። የቤት ፍላጎት፣ የኑሮ ጫና፣ የትምህርት ወጪና ሌላም።

በላስቲኳ ጎጆ ቤተሰቡ በአንድ ተኝቶ፣ በእኩል ይነሳል። እንግዳ፣ ዘመድ ወዳጅ የሚያርፍበት ሌላ ክፍል አይታሰብም። ምግብ ለማብሰል፣ አቅርቦ ለመጉረስ፣ ታሞ ለመተኛት መልከ ብዙ የምትሆነው ጠባቧ የላስቲክ ቤት ነች። ‹‹ኑሮ ካሉት›› እንዲሉ ሆኖ ቤተሰቡ አያልፉ ይመስሉ ችግሮች እንደዋዛ ተሻግሯል።

ሁሌም በወይዘሮዋ ቤተሰብ፣ በጠባቧ ጎጆ ፍቅር ነግሶ ያድራል። አባወራው ለሚስቱ፣ ልጆች - ለእህት ወንድሞቻቸው መተሳሰብን አስተምረዋል። እስከዛሬ በዚህች ቤት ሳቅና ደስታ ሲመረት ቆይቷል። እንዲህ በመሆኑ አስፈሪ የጨለማ ጊዜያት፣ ነጎድጓዳማ የክረምት ወራት፣ ቀዝቃዛዎቹ የውድቅት ሌሊቶች ድል ተነስተዋል።

በመንደሩ እነሱን መሰል ጥቂት ቤቶች ተመሳሳይ ችግርን ይጋራሉ። በነዋሪዎች ዘንድ የጉርብትናው ትርጉም ከሌሎች ዓለም ይለያል። ሁሉም ስሜታቸው አንድ ነው፣ ክፉ ቀናትን፣ የደስታ ጊዜያትን፣ በእኩል ተሻግረዋል። ጨለማውን፣ ያውቁታል። የችግርን ጥግ እስከጫፍ ተጉዘውታል። ሀዘንና ደስታ፣ ይሏቸው እውነቶች ለእነሱ ትርጉማቸው ልዩ ነው። አንዳንዴ እንደሰው ይጋጫሉ፣ ይኳረፋሉ። ጠብ ቅያሜቸው ግን ስር አይሰድም። ተመልሰው እንደቀድሞው ሊሆኑ ሕይወት ግድ ይላቸዋል። ባሉበት፣ ኑሯቸውን ባዋቀሩበት ጎስቋላ መንደር ነገ ማለት ለእነሱ በ‹‹ይሆናል›› የሚናፍቁት ተስፋ ነው።

**የድንገት እንግዳ...**

ከዕለታት በአንዱ ቀን በነዳግማዊት የላስቲክ መንደር የደረሱ እንግዶች በድንገት አካባቢውን ተዟዙረው ይጎበኙ ያዙ። ከዚህ በፊት እነሱን መሰል ፀጉረ ልውጦች በስፍራው ታይተው አያውቁም። ነዋሪው የከተማዋን ከንቲባ ጨምሮ ሌሎችን ባየ ጊዜ ስሜቱ ተከፈለ፣ ውስጡ በጉራማይሌ ሀሳብ ታመሰ፤ አንዳንዱ አሻግሮ በጎውን ተመኘ፣ ሌላው ደግሞ የሚባለውን ሊያደምጥ ራሱን አዘጋጀ።

አዲስ አበባ በርካታ ነዋሪዎቿ በቤት እጦት ይፈተናሉ። አብዛኞቹ ከከተማ ርቀው ጎጆ ይቀልሳሉ። የበርካቶቹ መኖሪያ በህገወጥነት ተፈርጆ ጎጇቸው ይፈርሳል፣ ኑሯቸው ይበተናል። እነዳግማዊትን የመሰሉት ደግሞ በመሀል ከተማ ኑሮን ለማሸነፍ በላስቲክ ቤት ሕይወትን ይገፋሉ። አሁን እንግዶቹ ያዩትን አይተው ከስፍራው ሄደዋል። ከጉብኝቱ በኋላም አካባቢው እንዲፈርስ መወሰኑ ተሰምቷል። ይሄኔ ነዋሪዎቹ በድንጋጤ ይይዙትን አጡ። ቤቶቹ ማለት ለእነሱ መኖሪያዎች ብቻ አይደሉም፣ የዕለት ገቢያቸውን የሚያፈሩበት እንጀራቸው ጭምር እንጂ።

አጋጣሚ ሆነና በመንደሩ ነዋሪ ዘንድ መልካም ተስፋ ፈነጠቀ። የጉብኝቱ ውጤት ቤትን በማፍረስ ብቻ አልተወሰነም። አካባቢው በዘመናዊ ቤቶች እንዲተኩ ተወስኗል። ለጎስቋላ ቤቶቹ ነዋሪዎች በድንገት ይህን እውነት መስማት በቀላሉ የሚታመን አልሆነም። አስደንጋጩ የምስራች ዕንባና ሳቅ በወረሰው ስሜት ሲቀባበል ከረመ።

**አይቀሬው ጭንቀት**

አሁን ዳግማዊት እነዛ ፈታኝ የመከራ ጊዜያት እንደክረምቱ ዝናብ ሊያልፉ እንደሆነ አውቃለች። ከሰማይ እንደወረደ መና የመጣላትን ድንቅ ስጦታ ግን አምና መቀበል ተስኗታል። አሁንም ፈልጋው ሳይሆን ፈልጓት በመጣው አስገራሚ ዕድል እየተገረመች ነው። እንዲህ መሆኑ በብዙዎች ሕይወት አልተለመደም። እሷም ፍርሀትና ጥርጣሬ እየፈተኗት ነው። ቤቶቹ ተገንብተው እስኪጠናቀቁ ነዋሪዎቹ በተዘጋጀላቸው መጠለያ እንዲቆዩ ሆኗል።

ዳግማዊት ግን ጭንቀቷ በርትቷል። የቤተሰቧ ህልውና የቆመው በባለቤቷ ገቢ መሆኑን ታውቃለች። አሁን ቤቱ አስኪገነባ፣ የእሱ ስራ ሊቆም ነው። ስድስት ቤተሰብ ምን ይበላል? ኑሮና ሕይወትስ እንዴት ይቀጥላል? እነዚህ ጥያቄዎች ለወይዘሮዋ በእጅጉ አስጨናቂ ናቸው።

ጊዜያዊው መጠለያው ይሰጣል የተባለውን ቤት የሚተካ ባይመስላት ወይዘሮዋ ጠዋት ማታ ጭንቀቷ አይሏል። እስካሁን እንደምታውቀው ቤትን ያህል ወሳኝ ጉዳይ በቀላሉ አይገኝም። ብዙዎች ስለቤት ሲሉ ዓመታትን ተግተዋል። ሁሉም ግን የሀሳባቸው አይሞላም። እሷና መሰሎቿ ደግሞ በድንገት ቤት ‹‹ይሰራላችሁ›› ተብለዋል። ዳግማዊት ሁሉን እያየች የሚሆነውን አላመነችም። ነገ ደርሶ የተባለው ዕውን እስኪሆን በጥርጣሬ ዋተተች።

የመጠለያው ኑሮ ቀጥሏል። የአዲስ ቤቶቹ ግንባታም እንዲሁ። ዳግማዊት ግን እንደሌሎች በስፍራው ዝር አላለችም። ‹‹ካልታዘልኩ አላምንም›› እንዳለችው ሙሽራ የተባለው ተስፋ ከእሷ ደርሶ እስኪታየው በዝምታ ከረመች።

**ደማቁ ቀን...**

እነሆ! የጭንቅ ቀናት ታለፉ። የሀሳብ ጊዜያት ተረሱ። ክረምት አልፎ መስከረም እንዲመጣ ጨለማው ጠፍቶ ብርሃን ፈነጠቀ። አሁን ስጋት ተወግዷል። ‹‹የት እደርስ›› ይሉት ሀሳብ፣ ታሪኩን ቀይሯል። የላስቲክ መንደሮቹ አጸድ በዘመናዊ ቤቶች አምሮ አካባቢው ተውቧል። ‹‹ይገባናል›› ሳይሉ ‹‹ይገባችኋል›› የተባሉት ነዋሪዎች ደስታቸው ወደር አጥቷል። ይህ ቀን ደርሶ፣ የተባለው ዕውን እስኪሆን የብዙዎች ጭንቀት ነበር። አሁን ግን ያለፈው ‹‹ነበር›› ሊባል ዕድል ከዕድለኞች ፊት ቀርባለች።

ለነዋሪዎች ቤቱን ተከትሎ መልካም አጋጣሚዎች ደርሰዋል። በአካባቢው የአዋቂዎች የምገባ ማዕከል ተገንብቷል፤ ለበርካታ ሙያዎች የሚሆኑ ሱቆች ተሰርተዋል። ዳግማዊትን ጨምሮ በምገባ ማዕከሉ የስራ ዕድል ያገኙ ጥቂቶች አይደሉም። አሁን በጌጃ ሰፈርና አካባቢው የቀድሞ ታሪኮች የሉም። በአዲሱ ቤት የእፎይታ ዕንቅልፍ ጀምሯል፣ ሁሉም ለመልካም ሕይወት፣ ለጠንካራ ስራ ዝግጁ ሆኗል። ቤቶቹ ሲመረቁ ከብርት ከንቲባ አዳነች አበቤ በስፍራው ተገኝተው ለነዋሪዎች ስጦታ አበርክተዋል።

**ቤት -ለእምቦሳ**

ዛሬ በአዲሱ የወይዘሮ ዳግማዊት መኖሪያ ቤት በእንግድነት ተገኝቻለሁ። መልከ መልካሟ ወይዘሮ በተለየ ፈገግታና አክብሮት ተቀብላ እያስተገደችኝ ነው። ከሰፊው የሳሎን ዕልፍኝ አረፍ ብዬ ቤቱን መቃኘት ጀመርኩ። ሁለት መኝታ ቤቶች፣ የማብሰያ ክፍልና ዘመናዊ መታጠቢያ ከመጸዳጃ ቤት ተሟልቶለታል። ከአዲሱ ቤት ጋር የስራ ዕድልን ያገኘችው ዳግማዊት ከውሎዋ መልስ የሆነውን ሁሉ እያወጋችኝ ጨዋታችን ቀጥሏል።


አሁን መላው ቤተሰብ ከስጋት ርቋል። ልጆች እንደእኩዮቻቸው በወጉ ይማራሉ። ዳግማዊት ዕንባዋ ታብሷል። ሕይወቷ ተቀይሯል፣ የሆነላትን ሁሉ ስታስብ ሁኔታዎች ከቃላት በላይ ሆነው መናገር ይሳናታል። ከምንም በላይ ባገኘችው የስራ ዕድል አቅመ ደካሞችን መመገብ መቻሏ ደግሞ ለሕይወቷ ምላሽ ነው።

አመስግና አትረካም፣ የእሷና የመሰሎቿ ታሪክ ለሌሎች ወገኖች ጭምር ታላቅ ተስፋ እንደሚሆን ታምናለች። አዲሱን ዓመት በአዲስ ሕይወት፣ በአዲስ ተስፋ፣ በአዲስ ቤት ሆና ስትቀበለው ደስታዋ ወደር የለውም። እኛም ደማቅ ፈገግታዋን ተጋርተን፣ አዲስ ተስፋዋን ተመኝተን ቤቷን ‹‹ቤት ለእምቦሳ›› ብለናል።

**‹‹መልካም አዲስ ዓመት››**



# ስፖርት



## የኢትዮጵያን አንድነት ያጎሉ ድሎች

**ቦጋስ አበበ**



ኔልሰን ማንዴላ እንዲህ ብለው ነበር ‹‹ስፖርት ዓለምን የመለወጥ ኃይል አለው ፡፡ ሰዎችን የማስተባበር ፣ የማነቃቃት ኃይል አለው ... የዘር መሰናክሎችን ለማፍረስ ከመንግስታት የበለጠ አቅም አለው››፡፡ እናም የቀድሞውን የደቡብ አፍሪካ መሪና የነፃነት ታጋይ ቃል በመቀላቀል የተባበሩት መንግስታትም የ2030 ዘላቂ ልማት አጀንዳ መግለጫ ስፖርት ለልማት፣ ለሰላምና አንድነት ግቦች ለሚጫወተው ሚና ልዩ ቦታና እውቅና ይሰጣል፡፡

ስፖርት በተመሰረተባቸው አዎንታዊ እሴቶች የተነሳ ለአንድነት፣ ለሰላምና ለልማት ሁነኛ መሳሪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በርካታ አገራትም ይህን የስፖርት ትሩፋት በአግባቡ የተጠቀሙበት ብዙ አጋጣሚዎች በታሪክ ይታወቃሉ።

አገራት ብቻም ሳይሆኑ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ተቋማትም ስፖርትን ለአንድነት ይጠቀሙበታል። የደቡብ ሱዳን የእርስ በእርስ ግጭትን ለመፍታት ተመድ ከተጠቀመባቸው ዋነኛ መንገዶች ስፖርት አንዱ ነበር። ስፖርቱን እንደ መፍትሄ ለመጠቀም ምክንያት የነበረው አጋጣሚ ከጥቂት ዓመታት በፊት ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ በደቡብ ሱዳንና በጋቦን መካከል የተደረገው ጨዋታ እንደነበር ብዙዎች አሁንም ድረስ አይረሱትም። ደቡብ ሱዳን ተጋጣሚዋን 1ለ0 ባሸነፈችበት ጨዋታ ውጤቱ በአገሪቱ የእርስ በእርስ ጦርነት የቆሸሸው የአንድነት ስሜት ከተቀበረበት ገንፍሎ እንዲወጣ አደረገ። የአገሪቱ ህዝቦች በብሔር፣ በጎሳ ተመዳድበውና በጠላትነት ተፈራርጀው እርስ በእርስ ከመጋደል በአንድነት ስለ አገራቸው እንዲያዜሙ ያደረገ ክስተት ተፈጠረ። የልዩነት ቀለም ደብዝዞ የአንድነትና የወንድማማችነት ስሜቱን ከፍታ ያስመለከተ ክስተት በተግባር ተገለጸ።

ከስፖርታዊ ድሎች የሚቀዳ ድብቅ የብሔራዊ ስሜት ሲፍለቀለቅ ማየት አዲስ አይደለም። ዛሬ የአንድነት ቀን ነውና የሩቁን ትተን በዚህ ዓመት ብቻ ኢትዮጵያ በተለያዩ ዓለም አቀፍ የስፖርት መድረኮች ባገኘቻቸው ድሎች በፖለቲካ፣ በዘውግና በተሳሳተ ትርክት ተከፋፍለው በማህበራዊ የትስስር ገጾች ዘወትር ሲቆራቆዙ የሚስተዋሉ አካላት ሳይቀሩ ስፖርታዊ ድሎች በፈጠራቸው ስሜቶች እንዴት ወደ አንድነት እንደመጡ አስተውለናል። በነዚህ ድሎች እየተሸረሸረ የመጣው አገራዊ ስሜት እንዴት ገንፍሎ እንደወጣም አንዘነጋውም።

እንዳጋጣሚ ሆኑ ዛሬ የምንሸኘው የ2014 ዓ.ም ኢትዮጵያ ካለፉት በርካታ ዓመታት በተለየ በዓለም አቀፍ የተለያዩ ስፖርት መድረኮች ጣፋጭ ድሎችን ያገኘችበት ነው። ኢትዮጵያ እንዲህ በጦርነት ፈተና ውስጥ በገባችበት ወቅት፣ ሕዝቦቿም በመፈናቀል፣ በንጹሃን ዜጎች ግድያ፣ በኑሮ ውድነትና በፖለቲካ ውጥረት አንድነታቸውን ለመሸርሸር ፈተናዎችን በሚጋፈጡበት ወቅት በስፖርት ያገኘችው ያልተለመደ ስኬት ብዙ ትርጉም አለው። እነዚህ ድሎች በኢትዮጵያ ተስፋ የቆረጡ ተስፋቸው እንዲለመልም ሆኗል፣ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም የሚሉ ሳይቀሩ ወደ ኢትዮጵያዊነት ለመመለስ ሲቀምጡ ታይተዋል፣ ክፉዋን የሚመኙም በነዚህ ድሎች አንገታቸውን ደፍተዋል፡፡

ባለፈው መጋቢት በሰርቢያ ቤልግሬድ በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ አሜሪካንን አስከትላ አንደኛ ሆና ስታጠናቅቅ የሁልጊዜም የኩራት ምንጭ በሆኑት ብርቅዬ አትሌቶቿ ድል ያልፈነጠዘ የለም። በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ዋልያዎቹ ግብጽን ከ60 ዓመት በኋላ ሲያሸንፉ ስለ ኢትዮጵያ ጮቤ ያልረገጠ፣ ብሔራዊ መዝሙሯ የተለየ ስሜት ያልፈጠረበት የለም። ከወራት በፊት በኦሪገን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና እንዲሁም በኮሎምቢያ ካሊ የወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ብርቅዬዎቹ አትሌቶች የወርቅ ሜዳሊያ አፍሰው የኢትዮጵያን ስም በዓለም አደባባይ ደጋግመው ሲያስጠሩ በአገሩ ያኮረፈ ሳይቀር ውድድሮችን በጥፍሩ ቆሞ ተመልክቷል። እነዚህ ድሎች ለወትሮው በፖለቲካና ሌሎች ጉዳዮች ተወጥረው የከረሙ መገናኛ ብዙሃን ሳይቀሩ አጀንዳቸው ስፖርትና ስፖርት ብቻ እንዲሆን አድርገዋል። ዘር፣ ሃይማኖት፣ ፖለቲካ፣ አመለካከት፣ ጾታና እድሜ ሳይለይ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል አንድ የሆነበት አጀንዳ ቢኖር እነዚህ ድሎች ናቸው።

እነዚህ ድሎች ኢትዮጵያውያንን በአንድ ያስደሰቱ ብቻ አይደሉም። ድሎቹ በራሳቸው በአንድነት የተገኙ ናቸው። ለነዚህ ድሎች የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የትኛውም ብሔር፣ የትኛውም ወገን ተጠሪ አይደለም። እነዚህ ድሎች ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ እንቁ ስፖርተኞቿ በአንድነት ያስመዘገቧቸው ናቸው። ውጤቶቹም በየትኛውም መንገድ ከመለያየት ይልቅ እንደ አገር አንድ ሆኖ የመቆም ሚስጥሮች ነበሩ።

ከብዙ በጥቂቱ የተጠቀሱት ማሳያዎች ስፖርት አገራዊ አንድነትን ለመፍጠር፣ ሰላምን ለማስፈን ያለውን ጉልህ ድርሻ ለመጠቆም ያህል እንጂ ብዙ መናገርና ብዙ መጻፍ ይቻላል። ስፖርትን ለአንድነትና ለሰላም አሳንስር አድርጎ መጠቀም ኢትዮጵያን ካለችበት በርካታ ችግሮች ለማውጣት የሚደረገው ጥረት በእጅጉ እንደሚረዳ ተገንዝቦ መንግስትም በአግባቡ ሊጠቀምበት እንደሚገባ በዚህ አጋጣሚ ማስታወስም ተገቢ ነው። በተለይም ኢትዮጵያ በዚህ ወቅት ከገጠሟት ፈተናዎች አኳያ በህዝብ ዘንድ ያለውን መተማመን ለማጠንከር፣ ብሔርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች አንድነትን እንዳይሸረሽሩ ድልድይ እንዲሆን የስፖርት ዘርፍን እንደ ቁልፍ መፍትሄ የመጠቀም ጥረት በአዲሱ ዓመት እንደ አዲስ ልንጠቀምበት ይገባል። በተለይም በህዝቦች መካከል መቻቻልን፣ አንድነትን፣ ወንድማማችነትን... የሚሰብኩ የውድድር መድረኮችን ቀርጾ ወደ ተግባር መግባት ቢቻል የሸፈተውን ብሄራዊ ስሜት መመለስ እንደሚቻል በአንድነት ቀን ላይ ልናስብና ልንተገብረው እንደሚገባ ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

---


# የተተዉ ዕቃዎች ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር ግ12/2015

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አስመጪዎችን በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ 1160/2011 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1መሰረት ዕቃቸውን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፈጽመው ባለመውሰዳቸው ዕቃዎቻቸው እንደተተዉ ተቆጥረዋል፡፡ ስለሆነም በገቢዎች ሚኒስቴር ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ንብረቶች ስለሚወገዱበት ሥርዓት በአወጣው መመሪያ ቁጥር 167/2012 አንቀጽ 9 መሠረት የተወረሱ ንብረቶችን ማለትም ኮፒር መስታወት፤ የመዝናኛ ጥላ፤ ጫማ፤ እስቶቭ እና የቴክኒክ መሣሪያ፤ ዕቃዎችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለመጫረት የሚፈልጉና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1. ተጫራቾች የዕቃዎቹን ዝርዝር፣ ዓይነት፣ ብዛት፣ የጨረታ ሠነድ እና መመሪያ መግለጫ እንዲሁም የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ዘወትር ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 6፡00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10፡30 ሰዓት እና ዓርብ ከጠዋት 2፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 5:00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7፡30 ሰዓት እስከ ቀኑ 10፡30 ሰዓት እንዲሁም ቅዳሜ ከጠዋት 2፡00 ሰዓት እስከ ረፋዱ 5:30 ሰዓት የማይመለስ ብር 100 (አንድመቶ) በመክፈል ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ሂሳቦች ቡድን መውሰድ ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች በጨረታ ከሚሸጠው ዕቃ ጋር በዘርፉ የፀና ንግድ ፈቃድ ያላቸው፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤ 15% የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈለ ለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ሆኖም ግምታዊ ዋጋቸው ከብር 500,000.00 በታች የሆኑ ማንኛውንም ዕቃ ለመግዛት የ15% የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሠርተፍኬት ማቅረብ ሳያስፈልግ መወዳደር ይችላሉ፡፡
3. ማንኛውም ተጫራች ለጨረታው ማስከበሪያ የሚሆን የሚጫረትበትን ጠቅላላ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ጨረታ ከመከፈቱ በፊት በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ አሸናፊው እንደታወቀ በ3 (ሶስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የሚመለስላቸው ሲሆን አሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ከአሸነፈበት ዋጋ ላይ የሚታሰብላቸው ይሆናል፡ ተጫራቾች የሚያስይዙት CPO በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስም ETHIOPIAN CUSTOMS COMMISSION MODJO BRANCH OFFCE በሚል ሲሆን የግል ባንክ ከሆነ ከአዲስ አበባ አስተዳደር ቅርጫፎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሆነ ደግሞ ከአዲስ አበባ አዳማና ሞጆ ቅርጫፎች መዘጋጀት አለበት፡፡ ተሳታፊዎች ዋጋ መሙላት የሚችሉት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተዘጋጅተው ማህተም ያረፈበት ሠነድ ላይ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ በመግዛት የሚወዳደሩበትን ዕቃ አስቀድሞ ማየት ያለባቸው ዕቃውን ሳያዩ ለሚሞሉት ዋጋ ቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊነቱን አይወስድም፡፡
5. የግልፅ ጨረታ ተሳታፊ ተጫራቾች እያንዳንዱን ዕቃዎች ለመግዛት የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋ፤ የሞሉበት ሠነድ፤ በተራ ቁጥር 2 የተገለፁትን ማስረጃዎች ኮፒ እና ያቀረቡት የመጫረቻ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO በኤንቬሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ8 ተከታታይ ቀናት ጠዋት 4፡45 ሰዓት ድረስ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይቻላል፡፡
6. የጨረታ ሣጥኑ ከታሸገ በኋላ የሚመጡ የመጫረቻ ሰነዶች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡
7. የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣበት ቀንን ጨምሮ በ8ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4፡45 ሰዓት ታሽጐ በዚሁ ዕለት ጠዋቱ 5፡00 ሰዓት ላይ ተጫራቾቹ ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ በአዘጋጀው ቢሮ ውስጥ ይከፈታል፡፡
8. ማንኛውም በግልጽ ጨረታ የሚሳተፍ ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ዋጋ መቀየር ወይንም የሌላ ተጫራቾችን ዋጋ ተንተርሶ ዋጋ አሻሽሎ ማቅረብ አይችልም፡፡
9. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ጨረታውን ለማሸነፍ ሲል መደለያ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ ማንኛውም ተጫራች ከጨረታው ይወገዳል፡፡ ጨረታው ከተካሄደ በኋላም ቢሆን ጨረታ አሸናፊው ጨረታውን ያሸነፈው በህገ-ወጥ መንገድ መሆኑ ከተረጋገጠ የጨረታው ውጤት ይሰረዛል፡፡
10. ማንኛውም የጨረታ ሽያጭ የዕቃው አስመጪ ወይም ባለቤት እና ቤተሰብ የነበሩ ሰዎች በጨረታው መሳተፍ አይችሉም፡፡
11. ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ እራሱን ከጨረታው ውድድር ማግለል አይቻልም፡፡
12. ማንኛውም ተጫራች የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ የጨረታው ግምገማ ተጠናቆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የጨረታውን ውጤት እስከሚያሳውቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡
13. የግልጽ ጨረታው አሸናፊ ጨረታውን ስለማሸነፋቸው ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ5(አምስት) ቀናት ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ በማድረግ ዕቃውን መረከብ አለበት፡፡ በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ ገንዘቡ ገቢ ካልተደረገ ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ያስያዙት ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡ ያሸነፉት ዕቃም በድጋሚ ለጨረታ ሽያጭ ይቀርባል፡፡
14. በተራ ቁጥር 12 በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ አድርጎ ዕቃውን ያላነሳ/ያልተረከበ እንደሆነ ለሚቆይበት ለተጨማሪ ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ይከፍላል፡፡ ሆኖም ዕቃው በ2 (ሁለት) ወራት ውስጥ ካልወጣ እንደተተወ ተቆጥሮ በጨረታ ሽያጭ ይወገዳል፡፡
15. አሸናፊው ተጫራች ዕቃዎችን ለመረከብና ለማጓጓዝ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ሁሉ ራሱ ይሸፍናል፡፡
16. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ የአቀረበውን ዕቃ ብዛት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ ሙሉ መብት አለው፡፡
17. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዕቃዎቹን ለመሸጥ የተሻለ አማራጭ ወይም ዘዴ ከአገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
18. ለተጨማሪ ማብራሪያ በሥልክ ቁጥር 022-236-90-94 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

# በገቢዎች ሚኒስቴር ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት